# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት




## በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለአካል ጉዳተኞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2009 ዓ.ም

ማውጫ ገጽ


**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ** ........ i

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ........ i

**በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር** ........ i

**የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ /ድርሞ/** ........ i

Executive Summery / ........ i

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ ........ 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ ........ 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ........ 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት ........ 5

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ሀይል ........ 6

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 6

የማህበራዊ ደህንነት ዳይሬክቶሬት የአሰራር ስርዓት መግለጫ ........ 6

የኦዲቱ ዓላማ ........ 8

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 9

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 9

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 10

ክፍል ሁለት ........ 11

የኦዲት ግኝቶችን ........ 11

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለውን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም ........ 11

የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም እና በክልል ክልላዊ አተገባበር ኮሚቴ እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፣ ........ 11

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አገሪቷ የፈረመችውን ኮንቬንሽን እና ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለማስፈፀም በሚያስችል መልኩ በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት መደራጀቱን በተመለከተ ........ 15

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች የአካል ጉዳተኞች መብቶች የሚከበሩና የሚተገበሩ መሆናቸው በተመለከተ፣ ... 16

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ማንኛውም መ/ቤት የሚሠሩ አካል ጉዳተኞች በሥራ ቦታ እና በዕለት እንቅስቃሴያቸው ወቅት ጥቃት የመከላከልና ተፈፅሞ ሲገኝ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣ ... 19

ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል እርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረጋቸውን በተመለከተ ... 21

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአካላዊ ተሀድሶ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ለማስፋፋት የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ ... 22

የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካላዊ ተሀድሶ ማዕከላት  እንዲስፋፉ እና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ  የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ ... 24

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራም ስራዎች ተደራሽ እንዲሆኑ  ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ ... 29

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚያገኙ ስለመሆኑ የሚደረግ ድጋፍና ክትትል በተመለከተ ... 31

አካል ጉዳተኞች በሚገነቡ ሕንፃዎች እና ለህዝብ አገልግሎት ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና መገልገያ ተቋማት ተደራሽ መሆናቸውን  በተመለከተ ... 38

አካል ጉዳተኞች ለማንኛውም ለሕዝብ አገልግሎት  ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና  መገልገያ ተቋማት ውስጥ ተደራሽ በሆነ መልኩ መረጃ የሚገልፁ ወይም የሚያስተላልፉ መሆናቸውን በተመለከተ ... 41

አካል ጉዳተኞች የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ማንኛውም ተሽከርካሪዎችና መገልገያዎች ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ ... 44

የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ በሁሉም የሚዲያ አካላት መካተቱን፣ በባህል፣  በስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ በመዝናኛ ዝግጅቶች የሚሳተፉ መሆናቸውን በተመለከተ ... 49

ሚኒስቴር መ/ቤቱ  አካል ጉዳተኞች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ ... 54

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል ጉዳተኞችን ኮንቬንሽን፣ በሥራ ስምሪት አዋጅና በሌሎች አዋጆች ማስተዋወቃቸውን  በተመለከተ ... 55

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ለአካል ጉዳተኞች መረጃዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና  የመረጃ በዳታቤዝ ያደራጀ መሆኑን በተመለከተ ... 60

ክፍል ሶስት ... 61

መደምደሚያ ....61
ክፍል አራት ....75
የማሻሻያ ሃሣቦች ....75
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት.... i
የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫ .... i
የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችለውን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፤ .... i
ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች በቅንጅት የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ለመስራት፣ ስለአካል ጉዳተኞች መረጃዎችን ለመያዝ እና በመረጃ መሳሪያዎችና እኩል እድል ተጠቃሚና ተሳታፊ መሆን የሚያስችል የተቀናጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለመስራት፤ በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ .... iv
የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ድርጅታዊ መዋቅር .... vi
አባሪ 3 ....vii

# የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ /ድርሞ/

## /Executive Summery /

<u>የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ</u>

1. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞችን እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑ፣ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ከሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ከክልል አካላት፣ ከመንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ውጤታማ የሆነ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በአካል ጉዳተኞች ህይወት ላይ ለውጥ የሚያመጣ ሥራዎችን ማከናወኑን በመገምገም በአግባቡ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት የሚመለከታቸው የመንግስት ኃላፊዎች ትኩረት እንዲሰጣቸው በማድረግ እና ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

<u>**በኦዲቱ ወቅት የተገኙት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡**</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማስፈፀም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመራ ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን፣ የኮሚቴው አባል መ/ቤቶች ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ መሰረት በሚመለከታቸው ጉዳይ ለመፈፀም ኃላፊነት የወሰዱ ቢሆንም ይህን ስለመተግበራቸው በተደራጀ ሁኔታ በዓመታዊ ዕቅዳቸው አካትተው ማቀዳቸውን እንዲሁም በዕቅዱ መሰረት ስለመተግበራቸው የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በማድረግ በቅንጅት ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው ክትትልና ድጋፍ ስራ በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑ፣ እንዲሁም ይህን በማይፈፅሙ ተቋሚት የሚጠየቁበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዘጠኝ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ በጋራ በመሥራት የአካል ጉዳተኞች እኩል እድል

ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ሠነድ የተፈራረሙ ቢሆንም በሰነዱ መሰረት ለመፈፀም የጋራ ዕቅድ በማውጣት እና በመተግበር አፈፃፀሙን በመገምገም ጥልቀት ያለው ተግባር እየተከናወነ አለመሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን አተገባበር ለመከታተል እንዲቻል የክልል ቢሮዎችና በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ ክልላዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ በተጨማሪም በክልል ይህን ጉዳይ የሚከታተል አካል በስራ ላይ ያልተገኙ መሆኑ፤
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የአካል ጉዳተኞችን በኮንቬንሽኑ የተቀመጡ መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ ለማድረግና በማህበራዊ ዘርፍ የተቀመጡ መብቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ያላወጣ መሆኑ፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላትም በኃላፊነታቸው መሰረት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያወጡ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በጁን በ2010 ያፀደቀችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን፣ ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለመተግበርና ለማስፈፀም በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንዲደራጅ ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና በማስፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን በቂ ስራ እንዳልተሰራ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት የወጣው አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና የአዋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት ስለመተግበሩ የሚረጋገጥበት እና አፈፃፀሙንም የሚገመገምበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች በስራ ላይ መድልዎ ደርሶባቸው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲያመለክቱ የሥራ ሥምሪት አዋጅ ቁጥር 568/2002ን ጠቅሰው የድጋፍ ደብዳቤ ከመጻፍ ባለፈ በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት ድጋፍና ክትትል የሚያደርጉ አለመሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች በቅጥር፣ በምልመላ እንዲሁም ቁልፍ ቦታዎችን በኃላፊነት ለመያዝ በሚያደረጉት እንቅስቃሴ ውስጥ መድሎ ደረሰባቸው ሲያመለክቱ ጉዳያቸው በህግ

አግባብ ታይቶ የሚሰጡ ውሳኔዎች በተለይም መስማት ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች በምልክት ቋንቋ እንዲረዱ የማይደረግ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችለው መልኩ ነቅሶ በማውጣት የሚመለከታቸው አካላትን እና አካል ጉዳተኞች ማህበራትን አወያይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችል ሥራዎችን ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ በገኘው የገንዘብና የሙያ ድጋፍ፣ ከተባበሩት መንግስታት የጤና ድርጅት፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ተሀድሶ ሠራተኞችን ለማሰልጠንና ለመደገፍ የሚያስችል ብሔራዊ አካላዊ ተሃድሶ ስትራቴጂ በ2003 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም ተግባራዊ ለማድረግ በተፈለገው መጠን ስራ ያልተሰራና በስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ፣ ከክልል አካላት ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በስራ ላይ ከሚገኙ ኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት የኦርቶፔዲክ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን ያልተቀረፀ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ ስር የሚገኘው የብሄራዊ ተሀድሶ ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በማስተባበርና በመቀናጀት በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስ ቴክኒሽኖች፣ ኦክዪፔሽናል ቴራፒስቶችና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት በጠቅላላ ስልጠና፣ ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያና የተግባር ስልጠና እንዲያገኙና በስራ ላይ እንዲሰማሩ ጥረት ቢደረግም በሀገሪቱ ያለውን የባለሞያ ፍላጎት ለመሙላት የሚያስችል አለመሆኑ፤
- እንዲሁም የተሃድሶ ማዕከላት ምርቶችና ግብዓቶች የሚያመርቱበት መሳሪያዎቹና በመሳሪያዎቹ የሚመረቱ ምርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ስለመሆኑ በየጊዜው የሚፈተሸበት አግባብ ወይም የተቀመጠ ስታንዳርድ የሌለ መሆኑ፤

- የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት የተቋቋመባቸው ክልሎች እንዲጠናከሩ ባልተቋቋመባቸው ክልሎች እንዲቋቋም በቂ የሆነ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ባለው የመንግስት ጤና መዋቅር ማለትም (ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች) ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች(rehabilitation center) በማደራጀትና የሪፈራል (የቅብብሎሽ) ስርዓቶችን በመዘርጋት ተደራሽ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑ፤
- እንዲሁም የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት፣ ግብዓቶች እና ድጋፎች እንደ የሰው ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ፣ የእንቅስቃሴ መርጃዎች እና የፊዚዮቴራፒ አገልግሎቶችን ውጤታማና ተደራሽ የሆነ የምርትና ስርጭት ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ 16 አካላዊ የተሃድሶ ማዕከላት በከተሞች አካባቢ ብቻ የሚገኙ በመሆናቸው በሀገሪቷ ገጠራማ ክፍል የሚኖሩ የአካል ጉዳተኞች ማዕከላቱ ለሚሰጡት አገልግሎት ተደራሽ አለመሆናቸው እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚተገበር ዕቅድ የሌለ መሆኑ፣
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤና አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችን የሚቀርብ ስለመሆኑ በእስትራቴጂክ ሆነ በአመታዊ ዕቅድ በማቀድ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች እንደ ጉዳታቸው ዓይነት ተስማሚ በሆነ መልኩ ማለትም መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/ በማዘጋጀት በአካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤናና የግንዛቤ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግና በሽታውን ለመከላከል ስለሚያስችሉ ሁኔታዎች፣ የመተላለፊያ

መንገዶችና የመከላከያ ዘዴዎች ተዘጋጅቶ እንዲገነዘቡት የሚያስችል ሁኔታ እየተሠራ ስለመሆኑ በዕቅድ ይዘው ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶን በተመለከተ ተቀናጅቶ የመስራት ክፍተቶች መኖራቸው፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ የድርጊት መርሀ ግብሩ የተገለፀው የብሬል ትምህርትን የአማራጭ የፅሑፍና እያደጉ የሚሄዱ አማራጭ የመገናኛ ስልቶች፣ ዘዴዎችና ቅርፆችን የማስተዋወቂያ ገለፃና የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እንዲሁም የአቻ ለአቻ እገዛ እና የሥራ ላይ አስተምህሮትን ተግባራዊ እንዲሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ በመሥራት እንዲመቻችላቸው ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሐ/ ላይ አካል ጉዳተኞች እንደጉዳታቸው አይነት መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/፣ ለሕፃናትና ለሴት አካል ጉዳተኞች ትምህርትን ይበልጥ ተስማሚነት ባለው ቋንቋ፣ የግንኙነት ዓይነትና ዘዴ አማካኝነት የቀለም ትምህርትንና ማህበራዊ እድገትን ከፍ በሚያደርግ ሁኔታ ስለመሰጠቱ በበቂ ሁኔታ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፤
- እንዲሁም ማየትና መስማት በጣምራ ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሚያደርግ ካሪኩለም ያልተቀረፀ መሆኑ፤ አካል ጉዳተኞች ወደ ትምህርት በመግባት መማር እንዲችሉ በአስገዳጅ ሁኔታ ወደ ትምህርት ገበታ መምጣት የሚችሉበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፣ በተጨማሪም የመጣውን የለውጥ ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን በመያዝ የድጋፍና የክትትል ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑ፤
- በተጨማሪም አካል ጉዳተኞች የሚማሩበት ትምህርት ቤት በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት ምቹ የመማሪያ ህንፃዎችና ክፍሎች፣ የመዝናኛና መፀዳጃ ስፍራዎች፣ ቤተ መፃሕፍት፣ የውሃ መጠጫ ቦታዎች፣ ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ--ተደራሽ አለመሆናቸው፤ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከትምህርት

ሚኒስቴር ጋር አካል ጉዳተኞችን በትምህርት አሰጣጥ ተደራሽነት ላይ በቅንጅት ለመስራት የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሠነድ የተፈራረሙ ቢሆንም በሰነዱ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን በአመታዊ በዕቅድ ቢያካትቱም በዕቅዳቸው መሠረት ያልሰሩ መሆኑ፤

- የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. በተቀመጠው መሰረት የሚገነቡ ህንጻዎች ከዲዛይን ጀምሮ፣ በትግበራ ላይ ክትትል በማድረግ እና በርክክብ ወቅት አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ባደረገ መልኩ እየተገነቡ ስለመሆኑ እና ተግባራዊ ስለመደረጉ ቅንጅታዊ የክትትል ስራ የሚከናወንበት ስርዓት ተዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- በህንፃ አዋጁና መመሪያው ላይ በሚፈለገው ደረጃ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎች በሰፊውና በበቂ ሁኔታ አለመሰራታቸው፣
- በግንባታ ዙሪያ የተሰማሩ ባለሞያዎች ሁሉም በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መገንባታቸውን ለመከታተልና አዋጁንም ለማስፈፀም የተዘረጋ ስርዓት አለመኖሩ፣ ትኩረት አለመሰጠቱ እና በአዋጁ መሰረት ላልገነቡት ባለቤቶችም ሆነ ለማይተገብሩ ባለሞያዎች ተጠያቂ በማድረግ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ የማያስደርግ መሆኑ፤
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽን አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሰረት ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ድርጅቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብተው ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚከታተልበት ሥርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል በቂና ውጤት የሚያመጣ የግንዛቤ ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችና መገልገያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሆነ መልኩ መዘጋጀታቸው እና አገልግሎት መስጠታቸው ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ እንዲሆን እንዲሁም ተደራሽ ባልሆኑት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ በቂ የሆነ ድጋፍና ክትትል አለመኖሩ፤

- የትራንስፖርት ባለስልጣን የህዝብ ትራንስፖርት ለሚሰጡ ተሸከርካሪዎች የደረጃ መስፈርት ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም የደረጃ መስፈርቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው መዘጋጀታቸው እንደ ደረጃ መስጫ መስፈርት ያልተካተተ መሆኑ እንዲሁም አብዛኛው የትራንስፖርት አቅርቦቶች አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ አለመሆናቸውን፤
- የአዲስ አበባ ቀላል የከተማ ባቡር አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች በሁሉም ተርሚናሎች አሳንሰር ለመግጠሚያ የሚውሉ ግንባታዎች የተዘጋጁ ቢሆኑም እስከ ጥር 2009 ዓ.ም. ድረስ አሳንሰሮቹ ተገጥመው አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ አለመሆናቸው፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር ውስጥ የቃልና የፅሁፍ መልክት የሚተላለፍ ሲሆን የፅሁፍ መልዕክቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ የሚፃፍ በመሆኑ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆን ላይ ክፍተት መኖሩ፣
- በተጨማሪም በሀገር ደረጃ የሚገኙ የሀገር አቋራጭ መናኸሪያ ቦታዎች ከትኬት መቁረጫ ጀምሮ አገልግሎት የሚሰጡ የሀገር አቋራጭ የትራንስፖርት ስምሪት ቦታዎችና እና አውቶቡሶቹ ለአካል ጉዳተኞች በተሟላ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆናቸውን፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን፣ የእንቅስቃሴ መረጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ መገልገያዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የምርምርና የልማት ስራዎችን እንዲካሄዱ ድጋፍ እና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም የለሙ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ የማስተባበር፣ የማቀናጀት እና የመደገፍ ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞችን ከጉዳት አልባ ዜጎች እኩል በሁሉም የሚዲያ አካላት በማካተት የተለያዩ መረጃዎች በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ አለመሆናቸው እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በቂ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግልና የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ፕሮግራሞች ቢሰሩም ለየትኛው አይነት የአካል ጉዳት ምን አይነት አገልግሎት (ፕሮግራም) እንዳላቸው ለምን ያህል የአየር ሰዓት እንደሚሰጡና ያልተዳሰሱ አካባቢዎችን እንዲያካትቱ ስለመደረጉ እና ይህንም የሚገልፅ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲኖርና አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ እንዳላደረገ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እነማን እንደሆኑ ለየትኛው ችግር የት መሄድ እንዳለባቸው መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በሚያስችል

መልኩ የተቀረፀ አለመሆናቸው እና በሚዲያ  የሚነገሩ ማስታወቂያዎችም አካል ጉዳተኞች ሊረዱት በሚችል ቋንቋ በጉዳታቸው ዓይነት ተዘጋጅተው በመቅረብ ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችል የሚድያ ስርዓት የሌለ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህንን አስመልክቶ በሚድያ ተደራሽ መሆን እንዲችሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት  የድጋፍና ክትትል ስራዎች ያልተከናወነ መሆኑ፤

- በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኞች የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን፣ ፊልሞችንና ቲያትሮችንና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖችን በተመቻቸ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆኑ የክትትል ስራ አለመስራቱ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በመዝናኛ፣ በዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና በስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተዘረጋ ሥርዓት እና የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አካል ጉዳተኞች በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስፈላጊ ሙያዊና የቴክኒክ ድጋፍ ፍላጎት ጥናት በመተግበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም የልማቱ ተጠቃሚ ቤተሰቦች ቁጥር የማሣደግ ሥራ  እንዲሰራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ የማድረግ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የሚሰጠው ግንዛቤና ስልጠና በማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ውስጥ በጥቅል የተቀመጡ በመሆናቸው ስለአካል ጉዳተኞች የተሰጡ የግንዛቤ ማስጫበጫዎች፣ የተሰጠበት ርዕስ፣ ምን ያህል አካል ጉዳተኞች እንደተሳተፉ በዝርዝር የሚያሳይ አለመሆኑ፣
- የሚሰጡ ድጋፎች በጥቅል የሚቀመጡ በመሆኑ ለየትኛው ጉዳይ ምን አይነት ድጋፍ እንደተሰጠ እና ድጋፉ ማንን ተጠቃሚ እንዳደረገ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በሚሰጡ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ያስገኙት ውጤት ውጤታማነት ከግቡ አንፃር እየተመዘነ የማይቀመጥ መሆኑ፣
- በሴክተሩ የሚከናወኑ የግንዛቤና የስልጠና ሥራዎችን ስታንዳርድ አውጥቶ ያስገኙትን ውጤት እየመዘኑ የማህበራዊ ችግሮችን በመከላከልና ህብረተሰቡን በማሣተፍ የተፈለገውን ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ ተከታታይ ስራዎች አለመስራታቸው፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኮንቬንሽኑንና አዋጁን ለማስፈፀም በበቂ መጠን ውጤት ተኮር (focused) የሆነ ለውጥ የሚያመጣ ግንዛቤ በመፍጠር፣ በማስተባበርና ሥልጠና በመስጠት እንዲሁም ተፈፃሚነቱን በመከታተል በማይተገብሩት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ በሚያስችል መልኩ ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑን፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ዝርዝር ድጋፍ፣ ስለተቀመጡ መብቶችና አስገዳጅ ህጎች፣ ስለአካል ጉዳት አይነቶችና ተጠቂዎች በፆታና በዕድሜ በመለየት ወዘተ መረጃዎችን በማደራጀት በዳታቤዝ ሊይዝ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጋር በመሆን በህዝብ ቆጠራ ወቅት ስለአካል ጉዳተኞች ሙሉ መረጃ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃዎች እንዲያዙ ድጋፍና ክትትል በበቂ ሁኔታ ያላደረገ መሆኑ፤

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

2. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞች የሰብአዊ መብታቸው እንዲጠበቅ፣ በሃገሪቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እንዲሳተፉ እና በማንኛውም መልኩ በኅብረተሰቡ ውስጥ የእኩል እድል ተሳታፊነታቸውና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

3. በዚህ ኦዲት አካል ጉዳተኛ ማለት የተለያዩ መሰናክሎች ከሚያስከትሏቸው ተፅእኖዎች የተነሳ ከሌሎች አቻዎቹ/ቿ/ ጋር በእኩል ደረጃ በማህበረሰቡ ውስጥ ሙሉና ውጤታማ ተሳትፎ እንዳያደርግ/እንዳታደርግ ሊገድቡ ከሚችሉ የረዥም ጊዜ አካላዊ፣ አእምሮአዊ ፣ ሥነአእምሮአዊ ወይም የስሜት ህዋሳት እክል/እክሎች ያለበት ሰው ነው፡፡ (የተ.መ.ድ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች ድንጋጌ አንቀፅ 1)

4. ተመራማሪዎችና የአካል ጉዳተኝነት ባለሞያዎች እንደሚጠቁሙት የአካል ጉዳተኝነት የሚይዛቸው ትርጓሜዎች በበቂ ሁኔታ ያለመኖር፣ የተወሰኑ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች በትርጉም ውስጥ ለማካተት ግልጽነት ያለመኖርና የተሳሳተ ትርጉም መስጠት፣ ቀላል የአካል ጉዳት ያለባቸውን እንደአካል ጉዳተኛ አለመቁጠር፣ ወላጆች የአካል ጉዳተኛ ልጃቸውን ወይም ሌላ የቤተሰብ አባልን አለማስቆጠርና ከደህንነት ጋር በተያያዘ የአንዳንድ አካባቢዎች ከቆጠራው ውጪ መሆን በህዝብና ቤት ቆጠራው በአካል ጉዳተኝነት ላይ ትክክለኛና በቂ መረጃ እንዳይኖር አድርጓል፡፡

5. ሆኖም በአገራችን በ2007 እ.ኤ.አ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተደረገ የህዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት መሰረት የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 73,750,932 ሲሆን ከዚሁ ውስጥ 864,218 /1.17%/ አካል ጉዳተኞች ናቸው፡፡ ከነዚህም አካል ጉዳተኞች መካከል 464,202 ወንዶች ሲሆኑ፣ 400,016 ሴቶች ናቸው፡፡ ከዚህ አመት ጀምሮ ባለው አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት በ2010 አሃዙ 80 ሚሊዮን በላይ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ በዚህም መሰረት የአካል ጉዳተኞች ቁጥር ወደ 1 ሚሊዩን /1.25%/ እንደሚደርሱ ይገመታል፡፡

6. ቁጥሩ ምንም ይሁን ምን፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለአካል ጉዳተኝነት መንስኤው ከድህነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ድህነት የአካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቻቸው ዋነኛ መገለጫ ነው፡፡ ድህነት ለአካል ጉዳተኝነት መንስኤም ውጤትም ነው፡፡ ከአጠቃላይ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የአካል ጉዳተኞች ውስጥ 95% የሚሆኑት በድህነት ህይወት እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡ 84% የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በገጠር አካባቢ የሚኖር በመሆኑ አብዛኞች አካል ጉዳተኞችም መሰረታዊ አገልግሎቶች ባልተሟላበትና ለአካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቻቸው ተደራሽ ባልሆነው በዚሁ ገጠር አካባቢ የሚኖሩ በመሆኑ አብዛኞቹ አካል ጉዳተኞችም መሰረታዊ አገልግሎቶች ባልተሟላበትና ለአካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቸቸው ተደራሽ ባልሆነው በዚሁ ገጠር አካባቢ የሚኖሩ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም በሀገሪቱ ያሉት ጥቂት የተሃድሶ አገልግሎቶችም ሲሆኑ እነሱም በብዛት የሚገኙት በከተማ ማዕከላት ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ የአካል ጉዳተኞች ጥገኝነት በመቀነስ በዘላቂነት ራሣቸውን የሚችሉበት የመሰረታዊ ትምህርትና ጤና እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን የማግኝት ዕድል ዝቅተኛ ነው፡፡

7. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በጥር ወር 1949 ዓ.ም ህዝብ በኑሮው እድገት እንዲያገኝ በተለይም አርብቶ አደሩ ህዝብ በኑሮው እንዲሻሻል ለማድረግ፣ ከኃላ ቀር ባህል ወይም ልምድ እንዲላቀቅ ለማስቻል " የህዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር" በመባል ለመጀመሪያ ጊዜ በአዋጅ ተቋቋመ፡፡ ከ10 አመት በኃላ ደግሞ በትዕዛዝ ቁጥር 46/1958 አ.ም " የህዝባዊ ኑሮ እድገትና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር" በሚል በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር ተደራጅቶ የማህበራዊ ደህንነት፣የህዝብ ኑሮ እድገት፣ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን የሚያካትቱ ስራዎችን ያከናውን ነበር:: ከየኮቲት 1969 ዓ.ም አብዮት በኃላ በአዋጅ ቁጥር 127/1969 "የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር " በሚል ስም በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲሁም ስልጣን እና ኃላፊነት ተቋቋመ፡፡ ቀጥሎም በ1980 አ.ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 8/1980 የመ/ቤቱ ስልጣንና ኃላፊነት በድጋሚ ተለውጧል፡፡

8. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከተመሰረተ በኋላ የመ/ቤቱ ስም እና ዋና ዋና ዓላማዎቹ ሳይለወጥ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 4/1987 እንደገና ተመስርቷል፡፡ በመቀጠልም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ

ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 እንዲሁም በ2008 ዓ.ም አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 916/2008 ስሙ ሳይቀየር ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት መሃከል የዚህ ኦዲት ርዕስና አላማ የሆነውን የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል ኃላፊነት ተሰጥቶት/ተቀብሎ/ እየሰራ ይገኛል፡፡

9. በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽንን እ.ኤ.አ በዲሴንበር 13 ቀን 2006 የተቀበለው ሲሆን ይህንኑ ኮንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዬች ምክር ቤት በግንቦት 24 ቀን 2002 ( እ.ኤ.አ ጁን 1 ቀን 2010) ያፀደቀው ሲሆን ይህን ተከትሎ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 676/2010 የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኮንቬንሽኑ ስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 568/2000 ስለ አካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት መብት ተግባራዊነትንና እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አዋጅ መሰረት የማስተባበር፣ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ

10. የኢንዱስትሪ ሠላም እንዲሰፍን፣ የሠራተኛው ጤንነትና ደህንነት እንዲጠበቅ፣ የሥራ አካባቢዎች እንዲሻሻሉና የሥራ ስምሪት አገልግሎት እንዲስፋፋ የዜጐች ማህበራዊ ደህንነት እንዲጠበቅ በተለይም፡-

- የአካል ጉዳተኞች ዕኩል ዕድል ተጠቃሚነትና ሙሉ ተሳታፊነት እንዲረጋገጥ፣
- አረጋውያን እንክብካቤ እንዲያገኙና ተሳትፏቸው እንዲጐለብት፣
- የማህበራዊ ችግሮችን ስለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሀድሶ አገልግሎት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ያጠናል፣ ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

11. በ2017 ዓ.ም የሥራ ሥምሪት የተስፋፋባት፣ ምቹ የሥራ ሁኔታ የተረጋገጠባት እና የማህበራዊ ደህንነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ የሚል ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና  ተግባር ተሰጥቶታል፤ እነዚህም፡-

- ❖ የዜጐች ማህበራዊ ደህንነት የሚጠበቁባቸውንና የሚሻሻሉባቸውን ዘዴዎች በተለይም የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ ስለሚችሉበት አረጋዊያን እንክብካቤ ስለሚያገኙበትና ተሳትፎአቸው ሊጐለብት ስለሚችልበት፣ የማህበራዊ ችግሮችን ስለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የኀብረተሰብ ክፍሎች የተሐድሶ አገልግሎት ስለሚያገኙበት፣ ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ያጠናል፣ ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- ❖ የኢንድስትሪ ሠላም እንዲጠበቅ ሠራተኞችና አሠሪዎች በማህበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ እንዲሁም የመንግሥት ወገንንን ጨምሮ የሶስትዮሽ አሠራሮች እንዲለመዱ ያደርጋል፣ የሥራ ክርክሮች በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሔ እንዲያኙ የሚያስችሉ አሠራሮችን ይዘረጋል፡፡
- ❖ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ደረጃዎችን ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውንም ይከታተላል፣
- ❖ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ለውጭ አገር ሰዎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል ፈቃድ ይሰጣል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል፣ የኢትዮጵያዊያን የውጭ አገር የሥራ ሥምሪት አገልሎትን ይቆጣጠራል፣
- ❖ በሀገሪቱ ውስጥ መደበኛ ባልሆነ ሥራ ላይ ስለተሰማራውና በሥራ አጥነት ስለሚገኘው የሰው ኃይልና ስለ ሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣ የሥራ ገበያ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፣
- ❖ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማህበራትን ይመዘግባል፣

❖ ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማህበራትንና የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፣ በነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፣ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፣

የሚሉት ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት

13. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተዳድር ሚኒስትር ያለው ሲሆን በስሩ ሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች አሉት፡፡ እነርሱም የማህበራዊ ጉዳይ ዘረፍ ሚኒስትር ዴኤታ እና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ናቸው፡፡ በሚኒስትሩ ሥር አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ጽ/ቤት፣ የዲያስፖራ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፣ ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት፣ ዕቅድ ዝግጅት የለውጥና ትግበራ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት፣ የኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት፣ ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት እና ሥነ ምግባር መኮንን መከታተያ ጽ/ቤት ይገኛሉ፡፡ በማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሥር ማህበራዊ ደህንነት ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት፣ የሰው ሀብትና የአሠራር ማሻሻያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት፣ የሠላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ማስጠበቂያ ዳይሬክቶሬት እና ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ያሉት ሲሆን፣ በማህበራዊ ደህንነት ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ሥር አራት የሥራ ቡድን አስተባባሪዎች አሉት፡፡ እነርሱም የፖሊሲና ፕሮግራም ዝግጅት ቡድን፣ የግንዛቤ ትምህርትና አድቮኬሲ ማስፋፊያ ቡድን፣ የአቅም ግንባታና መረጃ አገልግሎት ማስፋፊያ ቡድን እና የተሀድሶ አገልግሎት ቡድን ናቸው፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ  የሰው ሀይል

14. ሚኒስቴር መ/ቤቱ  በመዋቅር የተፈቀደለት 676 ሠራተኛ ቢሆንም ታህሣሥ 19/2009 ዓ.ም  በሥራ ላይ ያሉ ወንድ 139 (21%) እና ሴት 174(26%) በጠቅላላው 313 (46%) ሲሆን ቀሪው 363 (54%) በሰው ኃይል አልተሞላም፡፡ በተጨማሪም ለማህበራዊ ደህንነት ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት የሰው ኃይል 57 ሲሆን 25ቱ በሰው ኃይል ሲሞላ 32ቱ በሰው ሀይል ያልተሞላ ነው ፡፡ የሠራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ በማስተርስ ደረጃ ያሉ 21(0.03%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 76(11%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ 52/0.07%/ ሠርተፊኬት ያላቸው 11(0.02% )፣ 10+1፣ 10+2፣ ሌቨል 1 እና 2 10 (0.01% ) እንዲሁም ከ9-12 የተማሩ ሰራተኞች 73 (22%)፣ ከ1-8 61(1%) እና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ 9(0.01%)  የሚይዝ መሆኑን  ከሰው ሀብት ልማትና አሠራር ማሻሻያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከተሰበሰበ መረጃ ለማውቅ ተችሏል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

15. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን የገቢ ምንጭ የሚያገኘው ከመንግሥት በሚገኝ በጀት ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት በ2006 በጀት ዓመት ብር 23,143,551.16፣ በ2007 በጀት ዓመት ብር 26,594,108.72፣ በ2008 በጀት ዓመት ብር 37,114,064.47 እና በ2009 በጀት ዓመት እስከ ጥቅምት 30 ድረስ ብር 40,105,253.60 በድምሩ ብር 126,956,977.95 ገቢ አግኝቷል፡፡  በሶስት  የበጀት ዓመቱ ለተለያዩ ወጪዎች ያወጣቸው በ2006 በጀት አመት ብር  20,433,090.61፣ በ2007 ዓ.ም ብር 25,515,327.67፣ በ2008  በጀት አመት ብር 33,917,511.47 እና በ2009 በጀት ዓመት እስከ ጥቅምት 30 ድረስ ብር 13,957,302.54  በጠቅላላ ብር 93,823,232.29 ለተለያዩ ወጪዎች አውጥቷል፡፡

## የማህበራዊ ደህንነት ዳይሬክቶሬት የአሰራር ስርዓት መግለጫ

16. ዳይሬክቶሬቱ አካል ጉዳተኞች የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊነታቸው ተረጋግጦ የልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና የማህበራዊ ችግሮች እንዳይከሰቱ መከላከልና

በችግሩ ውስጥ ለሚገኙት የሕብረተሰብ ክፍሎችም ተገቢውን የተሃድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል እንዲሁም የማህበራዊ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ የህብረተሰቡ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ዋስትና ዘላቂነት ባለው መልኩ እንዲጠበቅና የኑሮ ደረጃው እንዲሻሻል የተገልጋዩን ፍላጐት ለማሟላት የሚከተሉትን የአሰራር ስርዓት ዘርግቷል፡፡

- *የተቋሙን ስትራቴጂካዊ ዓላማና ግብ እንዲሁም የውጤት ተኮር ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ስለአፈጻጸማቸውም ወቅታዊ /የሩብ፣ የመንፈቅና ዓመታዊ ወዘተ…ሪፖርት/ አዘጋጅቶ ለማህበራዊ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ያቀርባል፡፡ ከዘርፉ ስትራቴጂክ ዕቅድና ኘሮግራም በመነሳት ለባለሙያዎች ዕቅድ ያወርዳል፣ ያስተባብራል አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣*
- *በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋውያን እና በማህበራዊ ችግሮች ዘርፍ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፣ በዘርፉ ተግባራዊ እንዲደረጉ አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽኖችና ስምምነቶችን ያስፈጽማል፣ ይከታተላል፣ አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ወቅታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣*
- *የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት የተቋቋመባቸውን ክልሎች የሚጠናከሩበት፣ ባልተቋቋመባቸው ደግሞ ማዕከላቱ እንዲቋቋሙ የማስተባበር ሥራዎችን ይሠራል፣ የቴክኒክና ሙያ ድጋፍም ይሰጣል፣*
- *በአገሪቱ የሚታየውን የኦርቶፔዲክስና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን እጥረት ለመቅረፍ በዘርፉ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ሙያተኞች እንዲሰለጥኑና ሥራ ላይ እንዲሠማሩ ያደርጋል፣ በዘርፉ ሥልጠና የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ባለድርሻ አካላትን የማስተባበርና ድጋፍ የሚያደርጉትን እውቅና የመስጠት ተግባር ያከናውናል፣*
- *በሠው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ እንዲሁም የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት ለመስጠት የተማሩ ባለሙያዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣*

- በአገሪቱ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ተደራሽ እንዲሆን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ከልማት አጋሮች በመተበበርና በመቀናጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣
- አካል ጉዳተኞች ፍትሃዊ የሙያ ሥልጠናና የሥራ ስምሪት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፣
- የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው በለድርሻ አካላት ቅንጅታዊና የትብብር ሥራዎች እንዲጠናከሩና እንዲጐለብቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር እንዲሁም በመስኩ ከተሠማሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ከማህበራት ጋር የቅንጅትና የትብብር መድረኮችን ይፈጥራል፣ የማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከልና የተሐድሶ አገልገሎችን ለተጠቃሚዎች ለማድረስ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ኘሮግራሞችንና ኘሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ ያበለጽጋል፣ ውጤታማ እንዲሆኑም ከክልሎች አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

17. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞችን እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑ፣ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ከሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ከክልል አካላት፣ ከመንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ውጤታማ የሆነ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በአካል ጉዳተኞች ህይወት ላይ ለውጥ የሚያመጣ ሥራዎችን ማከናወኑን በመገምገም በአግባቡ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት የሚመለከታቸው የመንግስት ኃላፊዎች ትኩረት እንዲሰጣቸው በማድረግ እና ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

18. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት አላማ ለማሳካት ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፡-

    1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለውን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፡፡
    2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ ከክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ ከተሀድሶ ማዕከላት፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራትና ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ለመሥራት እንዲሁም ቋሚ የሆነ የመወያያ መድረክ ፈጥሮ ሊያወያይ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፡፡
    3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ አሰጣጥና ክትትል ዙሪያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ወቅታዊና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት እና ልውውጥ፣ የሪፖርት አቀራረብ እንደሁም የግብረመልስ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፤

    የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

19. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 46 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ቀርበው አስተያት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

20. ኦዲቱ የተከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2006 በጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ ለአካል ጉዳተኞች የተደረገ ድጋፍና ክትትል አፈፃፀም ዙሪያ የተሠሩትን ሥራዎች ላይ ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲሆን፣ በናሙና መርጦ ባያቸው 3 በክልል ካሉት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ 3 የአካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከላትን፣ 5 የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራትን እንዲሁም 5 የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችንና 2 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ የተለያዩ ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመከለስ፣ በመተንተን ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና በአካል በማየት ነው፡፡

21. በዚህም መሠረት በናሙና ለተመረጡ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች (ትምህርት ሚኒስቴር፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር)፣ የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት (የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበር፣ የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ማየትና መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር እና የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር)፣ የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች (የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ) እና የአካል ጉዳተኞች የተሃድሶ ማዕከላት (የዴሴ አካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከል፣ የመቐሌ አካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከል እና የአዲስ አበባ የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻና ማደራጃ ማዕከል) እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች (ቸሻየር ሰርቪስ ሆም ኢትዮጵያ እና የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር) በአካል በመሄድና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶችን

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለውን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም**

**የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም እና በክልል ክልላዊ አተገባበር ኮሚቴ እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤**

22. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማስፈፀም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰብሳቢነት የተዘጋጀውን የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም ለመከታተል የተቋቋመው ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ በመርሃ ግብሩ መሰረት ስለመፈፀሙ የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን እንዲልኩ በማድረግ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ በተጨማሪም ይህን በማይፈፅሙ ተቋማት ላይ የሚጠየቁበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በክልልም ክልላዊ አተገባበር ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ተግባር እንዲገባ በማስተባበር ድጋፍ ሊያደርግና አፈፃፀሙንም ሊከታተል ይገባል፡፡

23. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማስፈፀም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመራ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ በ2004 ዓ.ም. ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ በማፅደቅ በሚመለከታቸው ጉዳይ መሰረት ለመፈፀም የተለያዩ አካላት ኃላፊነት የወሰዱ ቢሆንም የኮሚቴው አባላት በተደራጅ ሁኔታ በዓመታዊ ዕቅዳቸው አካትተው ማቀዳቸውን እንዲሁም በዕቅዱ መሰረት ስለመተግበራቸው የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በማድረግ በቅንጅት ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው

ክትትልና ድጋፍ ስራ በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑ፣ እንዲሁም ይህን በማይፈፅሙ ተቋሟት የሚጠየቁበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡

24. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዘጠኝ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች ማለትም /ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና እክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጠን፣ ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ ከብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ ትምህርት ቤት/ ጋር በተደራሽነት ላይ በጋራ በመሥራት የአካል ጉዳተኞች እኩል እድል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ሠነድ የተፈራረሙ ቢሆንም በሰነዱ መሰረት ለመፈፀም የጋራ ዕቅድ በማውጣት እና በመተግበር አፈፃፀሙን በመገምገም ጥልቀት ያለው ተግባር እየተከናወነ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

25. በናሙና ተመርጠው በታዩ የኮሚቴ አባል በሆኑ መ/ቤቶች /የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት እና የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች/ እንደተገኘው፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደኮሚቴ ሰብሳቢነቱ ቋሚ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት በመወያየት አባል መ/ቤቶች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ድጋፍና ክትትል የማያደርግ መሆኑ፤
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ኮንቬንሽኑን መሰረት አድርገው በአፈፃፀሙ ላይ በጋራ የማይገመግሙ መሆኑን፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኮሚቴውን ከሚቋቋም በዘለለ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በኮንቬንሽኑ አፈፃፀም ዙሪያ ሥራዎችን ሠርተው በየሩብ ዓመቱ ወይም ዓመታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ የሪፖርት ግብረ መልስ በመስጠት ተጠያቂነት እንዲጠናከር ያላደረገ መሆኑ፤ በኮሚቴው አባላት ውስጥ በድርጊት መርሃግብሩ መሰረት በመተግበር ትብብር የማያደርገውን የኮሚቴ አባል መ/ቤቶችን በመለየት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ /በማሳወቅ/ የበኩሉን ኃላፊነት አለመወጣቱን፤

➢ በተመሳሳይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን አተገባበር ለመከታተል እንዲቻል የክልል ቢሮዎችና በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ ክልላዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ስለሁኔታው የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ተፈፃሚነት ለማሳደግ አጋዥ የሆነው የድርጊት መርሃ ግብር ማን ተቋም ምን መፈፀም እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠ መሆኑ፣ በተለይ ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ ተቋማት መደበኛ ዕቅድ በማቀድ እንዲፈፀሙ የክትትል ስራዎች የተሰሩ መሆኑ፤ እንዲሁም የኮንቬንሽኑን አፈፃፀም በተመለከተ ለተባበሩት መንግስታት በ2008 ዓ.ም የሚላከውን ሪፖርት ለማዘጋጀት ሲባል በኮንቬንሽኑ አፈፃፀም ላይ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ተቋማትና ማህበራት በማስሞላት የተሰሩ ስራዎችን አጠናክረናል በማለት ገልፀዋል፡፡

27. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ተቋማት በመደበኛ እቅዳቸው ኮንቬንሽኑን መሰረት አድርገው አቅደው መፈፀማቸውን ክትትል ስለማድረጋቸው ማስረጃውን ያላቀረቡ በመሆኑ፣ እንዲሁም ኮንቬንሽኑ ከተፈረመ በአራተኛ አመቱ ለተባበሩት መንግስታት በኮንቬንሽኑ መሰረት የተሰሩ ስራዎችን ሪፖርት ለማድረግ ሲባል የተሰበሰበ መረጃ የኮንቬንሽኑ አፈፃፀም ክትትል ለማድረግ ነው የሚለውን ለመቀበል አያስችልም፡፡

28. በሌላ በኩል ከዋና ተቋማትም ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲያከናወኑ በመደረጉ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሻለ አፈፃፀም የተመዘገበ መሆኑ እንዲሁም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በቅንጅትና በትብብር አካል ጉዳተኞችን የተመለከቱ ስራዎች ተከናውነዋል ተብለው የተገለፁት ከኮንቬንሽኑና ከድርጊት መርሃ ግብሩ ላይ የተመለከቱ ተግባራትን ናቸው በማለት መልሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ መግባቢያ ሰነድ ከመፈራረም በዘለለ ከእያንዳንዱ ተቋማት ጋር የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፤ በአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ በጥቅል የተቀመጡ ነገሮች በድርጊት መርሃ ግብሩ መሰረት እየተተገበሩ ናቸው ያሉ ቢሆንም በድርጊት መርሃ ግብሩ መሰረት በአመታዊ ዕቅዶች

ተለውጠውና በአፈፃፀሞች ላይ ከድርጊት መርሃ ግብሩ ጋር ተነፃፅረው ያልተቀመጡ እና ተግባሮቹም ተመሳሳይ ባለመሆናቸው የስራ ሀላፊዎች መልስ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

29. በተጨማሪም ክልሎች የራሳቸውን የአተገባበርና የክትትል ኮሚቴ እንዲያቋቁሙ ቦታው ድረስ በመሄድ የማስተባበር ስራ መስራታቸውን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በየትኛው እና በስንት ክልል የአተገባበር ኮሚቴ እንዲቋቋሙ እንዳደረጉ ዝርዝራቸውን እና ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፤ እንዲሁም በአካል በታዩ ሶስት ክልሎች (የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ) ውስጥ የክልል አተገባበር ኮሚቴ ሥራ ላይ ያልተገኘ በመሆኑ የሰጡትን መልስ ለመቀበል አያስችልም፡፡

30. በመሆኑም ሀገሪቱ ፈርማ የተቀበለችውን የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን፣ የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የተዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር እየተፈፀመ ባለመሆኑ አካል ጉዳተኞች የተሰጡ መብቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዳይቻል አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ የአካል ጉዳተኞች በአዋጆችና በኮንቬንሽን የተገለፁ መብቶች በስራ ላይ እንዲውሉ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲወጣ ማስተባበሩን በተመለከተ

31. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ ጁን 2010 የተፈረመውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በአዋጅ ቁጥር 676/2002 የተሰጠውን ሥልጣን በተቀላጠፈ፣ ተደራሽና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመወጣትና ለመተግበር የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ሊያዘጋጅ እንዲሁም ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን በማስተባበር ተቋማቱም በበኩላቸው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲወጡና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

32. ይሁን እንጂ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የአካል ጉዳተኞችን በኮንቬንሽኑ

የተቀመጡ መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ ለማድረግና በማህበራዊ ዘርፍ የተቀመጡ መብቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ያላወጣ መሆኑ፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላትም በኃላፊነታቸው መሰረት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያወጡ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

33. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት መልስ አገሪቷ ፈርማ የተቀበለችው ኮንቬንሽ ማስፈፀሚያ አዋጅ ቁጥር 676/2002 አብሮ በመሰጠቱ እንዲሁም ኮንቬንሽኑ እንዲፈጽም እያንዳንዱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩ ላይ ኃላፊነታቸው ተለይቶ በመሰጠቱ ሌላ የተለየ መመሪያ እንደማያስፈልገው ገልፀዋል፡፡ የሥራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለአካል ጉዳተኞች የተሰጡ መብቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊውን ጥናትና ዝግጅት በማድረግ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በመለየት ተፈፃሚ እንዲሆን ባለመደረጉ እና ሁሉም በኮንቬንሽኑ የተቀመጡ መብቶች በድርጊት መርሃ ግብሩ መሰረት ተፈፃሚ ለመሆን የሚያስችል ባለመሆኑ የተሰጠው መልስ አልተቀበልነውም፡፡

34. በመሆኑም አገሪቷ የፈረመችው ኮንቬንሽን አካል ጉዳተኞች እኩል እድል ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ በሚያስችል ደረጃ የተዘጋጀ እና የኮንቬንሽኑ ማስፈፀሚያ አዋጅ ቢወጣለትም መሬት ላይ ወርዶ ተግባራዊ መሆን እንዲችል ጥናት በማጥናት ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆና ባለመደረጉ አካል ጉዳተኞች በኮንቬንሽኑ መሰረት የተሰጣቸው መብት ወደ ተግባር ለመቀየር እንዳይቻል አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

## የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አገሪቷ የፈረመችውን ኮንቬንሽን እና ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለማስፈፀም በሚያስችል መልኩ በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት መደራጀቱን በተመለከተ

35. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በጁን በ2010 ያፀደቀችውን ኮንቬንሽን፣ ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለመተግበርና ለማስፈፀም በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ

የሚከታተል አካል እንዲደራጅና በመዋቅር እንዲካተት አስፈላጊውን ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና ተፈፃሚ እንዲሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

36. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በጁን በ2010 ያፀደቀችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን፣ ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለመተግበርና ለማስፈፀም በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንዲደራጅ ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና በማስፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን በቂ ስራ እንዳልተሰራ ታውቋል፡፡

37. ስለጉዳዩ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ አካትተው እንዲሰሩ ተቋማትን በማሳመን የማስተባበር ሃላፊነት የተጣለበት ስለሆነ ይህንን ሃላፊነቱን ለመወጣት ለፈፃሚውና አስፈፃሚ ተቋማት ባለሙያዎችና የስራ ሃላፊዎች የተለያዩ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሰራዎችን ሲሰራ መቆየ ሲሆን፤ ነገር ግን በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንዲደራጅ ጥናት ያልተጠና መሆኑን ገልፀዋል፡፡

38. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘርፈ ብዙ የሆነውን የአካል ጉዳተኞች ችግሮችን ለመቅረፍ እና ተደራሽ እንዲሆኑ በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተልና ስለተሰሩ ስራዎች ሪፖርት የሚያደርግ አካል ባለመኖሩ በተቋማቱ ውስጥ አካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት እንዳይተገበር እና በየጊዜውም አፈፃፀሙ እንዳይለካ በማድረግ የአካል ጉዳተኞች እኩል መብት ተጠቃሚና ተሳታፊ መሆናቸውን እንዳይረጋገጥ አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች የአካል ጉዳተኞች መብቶች የሚከበሩና የሚተገበሩ መሆናቸው በተመለከተ፣

39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት የወጣው አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና የአዋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች አካል ጉዳተኞች በቅጥር ምልመላ፣ ጊዜያዊና ቋሚ

ቅጥርን፣ በቋሚ ስራ ላይ መቀጠልን፣ የሙያ እድገትና፤እኩል ዋጋ ላለው ስራ እኩል ዕድሎች ሆነ እኩል ክፍያ የማግኘት፣ ለቅሬታዎች የመፍትሄ ምላሽ ማግኘት፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የስራ ሁኔታዎች መኖሩን፣ ማንኛውም ረዳት ለሚያስፈልገው አካል ጉዳተኛ ሥራውን ለመሥራት ወይም ሥልጠናውን ለመከታተል እንዲችል ረዳት የተመደበለት መሆኑን እና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ከጉዳት አልባዎች ጋር በእኩል ደረጃ ምቹ የስራ ሁኔታ የማግኘት መብት መኖሩን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ እና በአዋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስለመከበራቸው የሚረጋገጥበት እና አፈፃፀሙንም የሚገመገምበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ በኦዲት ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. እንዲሁም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ 5 የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት፣ 3 የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ 3 የአካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከላት፣ 5 የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣

- አብዛኛው በመንግሥትና በግል ተቀጥረው የሚሠሩ አካል ጉደተኞች ረዳት የሌላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ረዳት የሥራ መደብ የለንም በማለት አካል ጉዳተኞችን በቅጥር ላይ እያከተቷቸው አለመሆኑ፣
- አካል ጉዳተኞች ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው ሲወጡ በእኩል ደረጃ ከጉዳት አልባ ጓደኞቻቸው ተወዳድረው የመቀጠር ችግር እንደሚገጥማቸው፣
- አካል ጉዳተኛ ከጉዳት አልባ ተመራቂ ጋር ተወዳድሮ እኩል ነጥብ አምጥቶ ጉዳተኛውን ጥለው ጉዳት አልባውን አሳልፈው የሚቀጥሩ ተቋማት ያሉ መሆኑ፡
- ለቅጥር በወጣ ማስታወቂያ ለክፍት ሥራ መደቡ የሚጠይቀውን ተፈላጊ ችሎታ ያሚሉ አካል ጉዳተኞች ማጣሪያ ምርጫ ውስጥ ሳይገቡ ወደ ፈተና መቅረብ እንደሚችሉ ህግ ቢፈቅድላአቸውም ጉዳተኝነታቸው በቀጣሪው መ/ቤት ከታወቀ በአብዛኛው ለፈተና የማይጠሩ መሆኑ፣

- በተመሳሳይም የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አራት ዓይነ ሥውራን ሠራተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ቢሆንም ነገር ግን ለአካል ጉዳተኞቹ በህጉ መሠረት ረዳት አለመመደቡና የረዳት የሥራ መደብ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡
- በተጨማሪም አንዳንድ ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ድርጅቶች አካል ጉዳተኞችን ተሳታፊ የሚያደርግ ስብሰባዎችና ወርክ ሾፖችን ሲያዘጋጁ አካል ጉዳተኞች እንደ ጉዳት አይነታቸው ለዓይነ ሥውራን መሪ፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው የንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /ታክታይልስ/ እና መስማት ለተሳናቸው የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ የማይመድቡ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለሁኔታው የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዩ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ከአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት ጋር የወጡ መመሪያዎችና ደንቦች ስራ ላይ ስለመዋላቸው ማለትም በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚደረግ ቅጥር፣ ዝውውር፣ ደረጃ እድገትና የመሳሰሉት አካል ጉዳተኞችን ሳያገሉ እንዲፈፀሙ ለማድረግ በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር አማካኝነት መመሪያዎችና ደንቦች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ከፌዴራል እስከ ክልል ድረስ የኢንስፔክሽን ስራ እየተሰራ መሆኑንና በኦዲት ቡድኑ በዝርዝር የቀረቡ ጉዳዮች እንደሚፈፀሙ መስሪያ ቤታቸው የተገነዘበ መሆኑ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በስብሰባዎችና ወርክሾፖች ላይ አካል ጉዳተኞችን ተካታች የማያደርጉ ጉዳዮችን የተመለከቱ ሃሳቦች እውነትነት ያላቸው በመሆኑ መ/ቤቱ በጀመረው የግንዛቤ ማሳደግ ስራ በማጠናከር የምንቀጥልበት ይሆናል ብለዋል፡፡ የሥራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ለኦዲት ቡድኑ የክትትል /የኢንስፔክሽን/ ስራ ስለመስራታቸው የክትትል ሪፖርትም ሆነ ሌላ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

43. በመሆኑም አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባ ወገኖቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለአካል ጉዳተኞች ብቻ የሚያገለግል በቅጥርና በስራ ቦታዎች ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ አዋጅ የፀደቀ ቢሆንም በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመሆኑና እንዲሁም በቂ ክትትል አለመኖሩ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና

ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት በአፈፃፀሙ ላይ በቅንጅት እንዲተገበር ባለማድረጋቸው ምክንያት አካል ጉዳተኛ ዜጎች በጉዳታቸው ምክንያት መገለል ሳይደርስባቸው መቀጠር የሚያስችላቸው መብት ተፈፃሚ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ አካል ጉዳተኞች ተምረውና ተቀጥረው ህይወታቸውን ባግባቡ መምራት እንዳይችሉ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ማንኛውም መ/ቤት የሚሠሩ አካል ጉዳተኞች በሥራ ቦታ እና በዕለት እንቅስቃሴያቸው ወቅት ጥቃት የመከላከልና ተፈፅሞ ሲገኝ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣**

44. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት፣ የክልል ቢሮዎችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በማንኛውም መ/ቤት የሚሠሩ አካል ጉዳተኞች በሥራ ቦታ እንዲሁም ከዕለት ዕለት እንቅስቃሴያቸው ወቅት የሚደርስባቸውን ጥቃት የመከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ በፈጻሚው ላይ እርምጃ የተወሰደበት መሆኑን ሊከታተል እና ተፈጻሚነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 በማንኛውም መ/ቤት ተቀጥረው የሚሠሩ አካል ጉዳተኞች በሥራ ቦታ የሚደርስባቸውን ጥቃት የመከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ በፈጻሚው ላይ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ የተቀመጠ ቢሆንም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከማህበራት፣ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርና ከክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ አካል ጉዳተኞች ጥቃት ሲደርስባቸው፣ ፍትህ እንዲያገኙ ጥቃት ያደረሰውን አካል ተከታትለው ወደ ህግ በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስችል ምቹ ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም ባለው ሥርዓት መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በግልም ሆነ በቅንጅት ጉዳት ለደረሰባቸው አካል ጉዳተኞች ድጋፍ ስለማድረጉ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሌሉ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ 3 የክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች 4 የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት እና የማህበራት ፌዴሬሽን

- አካል ጉዳተኞች በስራ ላይ መድልዎ ደርሶባቸው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲያመለክቱ የሥራ ሥምሪት አዋጅ ቁጥር 568/2002ን ጠቅሰው የድጋፍ ደብዳቤ ከመጻፍ ባለፈ በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት ድጋፍና ክትትል የሚያደርጉ አለመሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች በደል ወይም ጥቃት ደርሶባቸው ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲመጡ ወደ አካል ጉዳተኞች ማህበር እንዲሄዱ የሚያደረጉ መሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች በቅጥር፣ በምልመላ እንዲሁም ቁልፍ ቦታዎችን በኃላፊነት ለመያዝ በሚያደረጉት እንቅስቃሴ ውስጥ መድሎ ደረሰባቸው ሲያመለክቱ ጉዳያቸው በህግ አግባብ ታይቶ የሚሰጡ ውሳኔዎች በተለይም መስማት ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች በምልክት ቋንቋ እንዲረዱ የማይደረግ መሆኑ፤
- ሴት የአካል ጉዳተኞች የመደፈር አደጋ ሲገጥማቸው በግንዛቤ ማነስ ምክንያት ወደህግ አለመሄዳቸው እና የህግ ከላለ አለማግኘታቸው፣
- በአንቦ አከባቢ አንድ ወንድ 7 መስማት የተሳናቸው ሴቶችን አስገድዶ መድፈሩንና የክስ ሂደቱ መስማት በተሳናቸው ብሔራዊ ማህበርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ክፍል ቢያዝም ውሳኔ ስለመሰጠቱ ማስረጃ ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

47. ስለጉዳዩ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አካል ጉዳተኞች በደል ሲደርስባቸው ወደ ህግ እንዲቀርቡ በማህበሩ ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፍትህን መጠየቅ የሚቻልበት ስርዓት መኖሩን ጠቅሰው በተለይም ሴት አካል ጉዳተኞች በሴትነታቸው ጥቃት ሲደርስባቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተከታትሎ ወደ ህግ የማቅረብ ሥራ እንደማይሠራና ለመስራትም ቢፈለግ መዋቅሩ በፌዴራል፣ በክልል እና በዞን ብቻ ስለሆነና አካል ጉዳተኞች በብዛት የሚገኙት በወረዳና በቀበሌ አከባቢ በመሆኑ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ የግንዛቤ መፍጠርና የመረጃ መለዋወጥ ችግሮች መኖራቸውን ገልፀው የተጠቀሰው ችግር በየተኛውም አከባቢ ተፈጻሚ እንዲሆን ወደፊት የፈጻሚውን፣

የአካል ጉዳተኞችንና የማህበረሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ስራ ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶት መከናወን እንደሚገባው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግንዛቤ መወሰዱን ገልፀዋል፡፡

48. በመሆኑም የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ለመከላከል፣ ከደረሰም በኋላ የሚመለከታቸውን አካላት በመደገፍ፣ የተከሰቱ በደሎችን በማሳወቅና ከአካል ጉዳተኞች ጎን በመቆም የሚጠብቃቸው ህብረተሰብ እንዲፈጠር በማድረግ የአካል ጉዳተኞች ደህንነት ተጠብቆ የመኖርና በመንግስት የመጠበቅ መብት እንዲረጋገጥ ተገቢውን ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል እርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረጋቸውን በተመለከተ

49. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ሊሰራ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችለው መልኩ ነቅሶ በማውጣት የሚመለከታቸው አካላትን እና አካል ጉዳተኞች ማህበራትን አወያይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችል ሥራዎችን አለመሰራቱ ታውቋል፡፡

51. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ አካል ጉዳተኞችን አግላይ የሆኑ ህግጋት ደንቦችና የቆዩ ልማዶችን እና አሰራሮችን በአግባቡ በመፈተሽ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ተገቢነት ያለው ጉዳይ ስለሆነ ወደፊት ዕቅድ በመያዝ የሚፈፀም መሆኑ ገልፀዋለው፡፡

52. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ላይ አድልኦ የሚያስከትሉ ህግጋትና ደንቦች እንዲሆኑ የቆዩ ልማዶችና አሰራሮች እንዲስተካከሉ ባለመደረጉ የአካል

ጉዳተኞች ችግር ዘርፈ ብዙና ስር የሰደደ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ የመሳሰሉት ችግሮች እንዲቀረፉ አድርጓል፡፡

## የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአካላዊ ተሀድሶ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ለማስፋፋት የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ

53. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ፣ ከክልል አካላት ከአለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በስራ ላይ ከሚገኙ ኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት የኦርቶፔዲክ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን፣ የማስፋፊያና የማጠናከሪያ ስትራቴጂ ሊቀርፅና ተግባራዊ ሊያደርግ፤ እንዲሁም በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲያገኙና በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

54. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ በገኘው የገንዘብና የሙያ ድጋፍ፣ ከተባበሩት መንግስታት የጤና ድርጅት፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ተሀድሶ ሠራተኞችን ለማሰልጠንና ለመደገፍ የሚያስችል ብሔራዊ አካላዊ ተሃድሶ ስትራቴጂ በ2003 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም ተግባራዊ ለማድረግ በተፈለገው መጠን ስራ ያልተሰራና በስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፤ የኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን ያልተቀረፀ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

55. በተጨማሪም የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ ስር የሚገኘው የብሄራዊ ተሀድሶ ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በማስተባበርና በመቀናጀት በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስ ቴክኒሽኖች፣ ኦክዩፔሽናል ቴራፒስቶችና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት በጠቅላላ ስልጠና፣ ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያና የተግባር ስልጠና እንዲያገኙና በስራ ላይ እንዲሰማሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2006-2008 ዓ.ም. በየዓመቱ 24 በለሞያዎች በጠቅላላው 72 ባለሞያዎች ለማሰልጠን አቅደው 48 ባለሙያዎች ያሰለጠኑ ሲሆን የ2008 ዓ.ም ምን ያህል ባለሞያ ሰልጥነው በሥራ ላይ

ስለመሰማራታቸው ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ነገር ግን በአመት 24 ባለሞያዎችን ብቻ በማሰልጠን በሀገሪቱ ያለውን የባለሞያ ፍላጎት ለመሙላት የሚያስችል አለመሆኑ በተጨማሪም በሀገሪቱ ያሉ 16 ማዕከላት የባለሞያ ችግር ያለባቸው መሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰለጥኑ ባለሞያዎችን ቁጥር በማሳደግ ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችል በቂ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

56. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና የተሃድሶ ማዕከላት በተገኙ ማስረጃዎች መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አሰልጠኖ ለማዕከላት የሚልካቸው ባለሙያዎች ብዛት ከ2 ሰው የማይበልጥ በመሆኑ በሀገሪቷ ያሉ 16 መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የአካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከላት ያለባቸውን የባለሙያ እጥረት መቀረፍ አለመቻላቸውን እንዲሁም በኦክዬፔሽናል ቴራፒስት የሰለጠነ ሙያተኛ የሌለ መሆኑና ችግሩን ለመፍታት ከማዕከላት እና ከክልል ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት ውጤታማ ስራ አለመሥራታቸውን፤ እንዲሁም እንዲሁም አንዳንድ ማዕከላት ምርቶችና ግብዓቶች የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የሚያወጣውን ስታንዳርድ የሚጠቀሙ ቢሆንም መሳሪያዎቹና በመሳሪያዎቹ የሚመረቱ ምርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ስለመሆኑ በየጊዜው የሚፈተሸበት አግባብ /ስታንዳርድ/ አለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ይህም በመሆኑ የትግራይ፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ሕዝቦች፣ የጋምቤላ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት ለመሥጠት ከ2006-2008 በጀት ዓመት ባቀዱት መሠረት ባለመሥራታቸው አብዛኛው የአካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት ተጠቃሚዎት አለመሆናቸውን ለኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተገኘ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ዝርዝር መረጃውን በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

58. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የአካላዊ ተሃድሶ ስትራቴጂ ማስተዋወቅ ስራ መስራታቸውን፤ ክልሎችን በማስተባበር የተሃድሶ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ማድረጋቸውን፣ የአካል ድጋፍ ምርቶቹን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የሚደገፉ ማዕከላት የኮሚቴውን ስታንዳርዳይዜሽን የሚከተሉ ሲሆን፣

የአገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ ግን እስታንዳርዳይዜሽን የሌለው መሆኑ፤ እንዲሁም የሚሰጠው አገልግሎት ሁሉም በሀገሪቷ ያሉ 16 ተሀድሶ ማዕከላት ተደራሽነት ላይ የሚጠበቀውን ያህል አለመሆኑን፤ በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥቁር አምበሳ ሆስፒታል ግቢ ለአካል ጉዳተኖች ተደራሽ በማድረግ ሞዴል መሆን የሚችል ህንፃ በመስራት ለዚሁ ተግባር እንዲውል ለትምህርት ሚኒስቴር ያስተላለፈ ቢሆንም ህንፃው በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለተፈለገው ዓላማ ሳይውል በፓርትሽን ከፋፍለው ለዶክተሮች ቢሮ እንዲውል እንደተደረገ ገልፀዋል፡፡

59. በመሆኑም ማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ተሀድሶ ሠራተኞችን ለማሰልጠንና ለመደገፍ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ቢቀረፅም ተግባራዊ ባለመሆኑ በዘርፉ የማደግ ለውጥ እንዲመጣ ያላስቻለ መሆኑ፤ እንዲሁም የኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን ባለመኖሩ የሚሰጡ አገልግሎቶች በመመዘን መሻሻል ያለባቸውን በማውጣት እንዲሻሻል እና የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር በሀገሪቱ የኦርቶፐዲክስ ቴክኒሻኖች፣ ኦኮፔሽናል ቴራፒስቶችና የፊዚዮቴራፒስት ሙያተኞች ቁጥር ከፍላጎት ጋር ለማመጣጠንና ለማብዛት ባለመቻሉ የአካል ጉዳተኞችን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ብቃት ያለው ድጋፍ እንዳያገኙ እና አካል ጉዳተኛ ዜጎችን አምራች ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ የሚያጠብ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካላዊ ተሀድሶ ማዕከላት እንዲስፋፉ እና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት በተቋቋመባቸው ክልሎች የሚጠናከሩበት፣ ባልተቋመባቸው ደግሞ እንዲቋቋሙ የረጅም እና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን በማውጣት እንዲተገበሩ የማስተባበር ስራዎችን ሊሰራና የቴክኒክና ሙያ ድጋፍ ሊያደርግ፤ በተመሳሳይም ባለው የመንግስት ጤና መዋቅር አገልግሎቱ ተደራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን ሊከታተል

ይገባል፡፡ እንዲሁም የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት ማለትም የአካል ጉዳተኞችን የመንቀሳቀስ ችሎታ ለማሻሻል የሚደረጉ ግብዓቶች እና ድጋፎች እንደ የሰው ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ፣ የእንቅስቃሴ መርጃዎች (ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ ዊልቸሮችና የመሳሰሉት) እና የፊዚዮቴራፒ አገልግሎቶችን ውጤታማና ተደራሽ የሆነ የምርትና ስርጭት ስትራቴጂ ሊቀርፅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት የተቋቋመባቸው ክልሎች ሁለቱም ከተማ መስተዳድር ጨምሮ በ5 ክልሎች (ትግራይ፣አማራ፣ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ሐረሪ) የተቋቋመ ሲሆኑ በማቋቋም ላይ ያሉ አዲስ ማዕከላት በ3 ክልሎች (በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በሶማሌ)፤ በ1 ክልል (በአፋር) ደግሞ በግንባታ ላይ ያለ ሲሆን ማዕከላቱ በተለያየ አቅምና ደረጃ ያሉት ሲሆን በከተማ አካባቢ ላይ የሚገኙ በመሆኑ በገጠር የሚኖሩ ዜጎች አገልግሎቱ ተደራሽ አለመሆኑ፤እና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት በቀቋቋመባቸው ክልሎች እንዲጠናከሩ ባልተቋቋመባቸው ክልሎች እንዲቋቋሙ በቂ የሆነ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም ባለው የመንግስት ጤና መዋቅር ማለትም (ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች) ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች(rehabilitation center) በማደራጀትና የሪፈራል (የቅብብሎሽ) ስርዓቶችን በመዘርጋት ተደራሽ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑ፤

62. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም ከክልል አካላት ጋር በመተባበር የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት ማለትም የአካል ጉዳተኞችን የመንቀሳቀስ ችሎታ ለማሻሻል የሚደረጉ ድጋፎች እንደ የሰው ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ፣ የእንቅስቃሴ መርጃዎች (ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ ዊልቸሮችና የመሳሰሉት) እና የፊዚዮቴራፒ አገልግሎቶችን ለማጠናከር፣ ለማስፋፋት፣ እና ተደራሽነት እንዲኖራቸው እንዲሁም በዘላቂነት አገልግሎት እንዲሰጥ በጋራ አቅደው ያልሰሩ መሆኑ፣ እንዲሁም የምርትና ስርጭት እስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፎች የተወሰነ ጊዜ ካገለገሉ በኋላ የሚያረጁና ለአጠቃቀም የማያመቹ በመሆናቸው ዕድሳት ወይም መተካት የሚያስፈልጋቸው ሲሆን በሃገሪቱ ያሉ ማዕከላት አቅማቸው ውስን በመሆኑ የሰው ሰራሽ አካል ድጋፎችን በበቂ ሁኔታ የማምረት እና የመጠገን ብቃታቸው ካለው ፍላጎት ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

63. በተጨማሪም የአካላዊ ተሀድሶ አገልግሎት ጥራት፣ የመግዛት አቅምን ያገናዘበ፣ ብቃት፣ ምቾት፣ ረጅም አገልግሎት የሚሰጥ ስለመሆኑ እንዲሁም የዕድሳትና ጥገና በተመለከተ የጥራት ቁጥጥር ስርዓት የሌለ በመሆኑ የሚሰጡ አገልግሎቶች ለመገምገም ያልተቻለ መሆኑ፤ ለአካል ጉዳተኞች በሃገር ውስጥ ተመርቶ ወይም በሃገር ውስጥ ገበያ የማይገኙ ቁሳቁሶች በዕርዳታና በግዥ ለሚሟላት የአካል ድጋፍ፣ ተያያዥ ምርት እና መድሃኒቶች የአቅርቦት ችግር መኖሩን በኦዲት ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና የአካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከላት የሚከተሉት ተገኝተዋል፤

- በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ 16 አካላዊ የተሃድሶ ማዕከላት በከተሞች አካባቢ ብቻ የሚገኙ በመሆናቸው በሀገሪቷ ገጠራማ ክፍል የሚኖሩ የአካል ጉዳተኞች ማዕከላቱ ለሚሰጡት አገልግሎት ተደራሽ አለመሆናቸው እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚተገበር ዕቅድ የሌለ መሆኑ፣
- የተሃድሶ ማዕከላትን ለማስፋፋት ባለው የመንግስት ስርዓትና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመጠቀም ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ እና የተጠናከረ የሪፈራል ቅብብሎሽ ስርዓት በመዘርጋት ችግሮችን ለመቅረፍ ያልቻለ መሆኑ፤
- በሀገሪቱ ያሉ 16 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ማዕከላት ባላቸው ውስን አቅም ሠው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፎችን በበቂ ሁኔታ የማምረት እና የመጠገን ብቃታቸው ካለው ፍላጎት ጋር ሲነፃፃር እጅግ አነስተኛ መሆኑ፤
- በመላ አገሪቱ ተመጣጣኝ የሆነ ዊልቸር /የአካል ድጋፍ/ አቅርቦትና ጥገና አለመኖሩ፤ የውጭ አገር ስሪት የሆነ አንድ ዊልቸር ዋጋው አሥር ሺህ ብር በመሆኑ የአካል ጉዳተኛውን አቅም ያገናዘበ አለመሆኑ ጉዳዩን አስመልክቶ በተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሃገር ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ወጭ ቆጣቢና ዘላቂ አገልግሎት የሚሰጡ የሠው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፎችን (ኮምፖነንቶችን)፣ ለእንቅስቃሴ አጋዥ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች /የአውቶማቲክ መኪና፣ ባለሶስት እግር ሞተር ብስክሌት፣ ባለሶስት እግር ብስክሌት

/በካቴና/ ዊልቸር፣ ክራንች፣ ነጭ ብትር/ ወዘተ.. በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ መጋቢት/2007 ዓ.ም. ከብረታብረት ኢንጂነሪንግ ጋር የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሰነድ ቢፈራረምም ወደ ሥራ በመግባት ምርትና ስርጭት ስትራቴጂ ቀርጾ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆኑ፡፡

- በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የአቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ በ2007 ዓ.ም ለአካልና የአካል ድጋፍ ማደራጃ ድርጅት (ክልል ቅርንጫፎችን ጨምሮ)፣ ለቸሻየር ሰርቪስ ኢትዮጵያ የተሃድሶ ማዕከላት አገልግሎት የሚውሉ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች፣ ጥሬ እቃዎችና ማሽነሪዎች ከውጭ አገር በማዕከል ግዥ እንዲፈፀም ከተሀድሶ ማዕከላት ፍላጎት በማሰባሰብ ከመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ ጋር በተገባው ውል ግምታዊ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ መሰረት ከ 1.6 ሚሊዮን ብር በላይ ወደ ኤጀንሲው ሂሳብ ቁጥር ቢገባም ከአንድ አመት በላይ ግዥው ተፈፅሞ ዕቃዎቹን ያልተረከቡ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ የሚገኘው የአዲስ አበባ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከል በሠራተኛና ማህበራዊ ጉደይ ሚኒስቴር በቦርድ ሰብሳቢነት የሚመራ ሲሆን የማምረቻ ማዕከሉ ህጋዊ አቋም የሌለው ማለትም መንግሥታዊም ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ መሆኑን የሚገልፅ አደረጃጀት የሌለው በመሆኑ፣ በዚህም ምክንያት ቀደም ሲል ሲደግፉት የነበሩ እንደ አለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር ከማዕከሉ ጋር አብሮ በመስራት ድጋፍ መስጠት አለመቻሉን ከማዕከሉ ስራ አስከያጅ በቀረበ ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚኒስቴር ዴኤታ ልዩ አማካሪ የሆኑ ቋሚ ሰራተኛ በመሆናቸው በማዕከሉ የግማሽ ቀን ስራ የሚሰሩ ሲሆን ሙሉ ጊዜያቸውን ለማዕከሉ ስራዎች የማያውሉ በመሆኑ ከማዕከሉ ከተቋቋመ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ቢሆንም ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣት አለመቻሉ፤
- ከዚህ ጋር ተያይዞ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ክልሎች ውስጥ የትግራይ ክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የአካል ጉዳተኞች ብዛትና የሚሰጠው የአካል ድጋፍ መጠን የተመጣጠነ ባለመሆኑ እንዲሁም የሰው ኃይል እጥረት፣ የበጀት

ማነስ፣ የአቅም ውስንነት ምክንያት በየበጀት ዓመቱ የሚታቀደው የአካል እና የአካል ድጋፍ አገልግሎት ተግባራዊ አለመሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 2 ተያይዟል፤

65. ይህን በተመለከተ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የተሀድሶ አካላትን በሁሉም ክልሎች እንዲቋቋሙ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን እቅድ ተይዞ ችግሩን ለመፍታት በአጭርና በረዥም ጊዜ መከናወን ያለባቸው ተግባራት ተለይተው እየተሰራ መሆኑ፤ የተሃድሶ ማዕከላት በተቋቋባቸው የሚሰጡት አገልግሎት ውስን መሆኑ በተለይም የባለሞያ እጥረት ችግር በመቅረፍ የማዕከላቱን አቅም ለማሳደግ በዕቅድ የተያዘ መሆኑን፤

66. እንዲሁም የአዲስ አበባ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከል በተመለከተ የአደረጃጀት ችግሩ ለመፍታት ሁለት ጊዜ ጥናት አጥንተው ለጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በድጋሜ ለሶስተኛ ጊዜ ጥናት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው እያጠኑ መሆኑና ችግሩ እስካሁን እልባት ያልተሰጠው መሆኑ፤ የማዕከሉ የሥራ አስኪያጁ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በውክልና የተመደቡ መሆኑ፤ የምርቶቹን ጥራት በተመለከተ ጥሬ ዕቃዎቹ ጥራት የሚፈተሸው በማሽን ውስጥ በመክተት እና ተጠቃሚው ምቾት እንዳለው በሚያረጋግጥላቸው መሰረት ሲሆን፤ ያሉት ባለሞያዎች በደረጃ 3 እና 4 የሰለጠኑ ባለሞያዎች በመሆናቸውና በዲግሪ ደረጃ ባለሙያ ስለሌለ የዕውቀት ክፍተት ምክንያት የጥራት ችግር ሊከሰት እንደሚችል፤ እንዲሁም ከብረታብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሲፈረም በቀጥታ ወደ ሥራ እንደሚገባ ታሳቢ ተደርጐ የነበረ ቢሆንም አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ወደ ሥራ መግባት አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

67. በመሆኑም የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት በሁሉም ክልሎች እንዲቋቋሙና በተቋቋመበትም እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ በቂ የሆነ ድጋፍ ባለመደረጉ፤ ባለው የመንግስት ጤና ተቋማትና ሆስፒታሎች ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች(rehabilitation center) በማደራጀትና የሪፈራል (የቅብብሎሽ) ስርዓቶችን በመዘርጋት ተደራሽ እንዲሆኑ ባለመደረጉ፤ እና የአካል ድጋፍ ምርትና ስርጭት ስትራቴጂ አውጥተው ተግባራዊ እንዲሆን በቂ የሆነ

ክትትልና ድጋፍ ባለመደረጉ ምክንያት አካል ጉዳተኞች የአካል ድጋፍ ምርት አቅርቦት እጥረት በመፈጠሩ አካል ጉዳተኞች ችግሮቻቸውን ሊያቀል የሚችል ኢኮኖሚያዊ፣ ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራም ስራዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል መደረጉን በተመለከተ

68. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅና ህዝቦችን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ ተደራሽ የሆነ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞች በስትራቴጂክና በአመታዊ ዕቅድ በማካተት የሚተገበር መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡

69. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤና አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችን የሚቀርብ ስለመሆኑ በእስትራቴጂክ ሆነ በአመታዊ ዕቅድ በማቀድ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

70. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የተሀድሶ ማዕከላትና የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆችና በተከለሱ ማስረጃዎች መሠረት፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች እንደ ጉዳታቸው ዓይነት ተስማሚ በሆነ መልኩ ማለትም መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/ በማዘጋጀት በአካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤናና የግንዛቤ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግና በሽታውን ለመከላከል ስለሚያስችሉ ሁኔታዎች፣ የመተላለፊያ መንገዶችና የመከላከያ ዘዴዎች ተዘጋጅቶ እንዲገነዘቡት የሚያስችል ሁኔታ እየተሠራ ስለመሆኑ በዕቅድ ይዘው ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶን በተመለከተ ተቀናጅቶ የመስራት ክፍተቶች መኖራቸው፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት፣ ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፣
    - የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ፌዴሬሽን በፌዴሬሽኑም ሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶን በተመለከተ የተሠራ ሥራ አለመኖሩን፤
    - የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበር ሚኒስቴር መ/ቤቱ በማህበሩ በዓመት አንድ ቀን በመገኘት ስልጠና ከመስጠት ባለፈ ጉዳዩን አስተመልክቶ በእቅዱ ይዞ የግንዛቤ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን አለማድረጉና ማህበሩም በዚህ ዙሪያ በማህበራቸው ለታቀፉት አካል ጉዳተኞች በዕቅድ ይዘው ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የማይሰሩ መሆኑን፤
    - የኢትዮትያ ዓይነ ሥውራን ማህበር ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ጋር ግንኙነት በማድረግ የተሰሩ ሥራዎች ቢኖሩም በቂ አለመሆኑን እንዲሁም፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርም በዚህ ዙሪያ ግንዛቤዎችን በመፍጠር ስለመፈፀሙ ድጋፍና ክትትል የማያደርግ መሆኑን፤
    - በተመሳሳይ ማየትና መስማት በጣምራ የተሳናቸው የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበር በማህበሩ የታቀፉ አካል ጉዳተኞች ጉዳታቸው ከሌላው

አካል ጉዳተኞች ይልቅ ውስብስብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚህ ዙሪያ ሙሉ በሙሉ ተደራሽ አለመሆናቸውን የማህበሩ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

71. ይህን በተመለከተ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የስነተዋልዶና የአካቶ ኤች አይቪ ኤድስ በዕቅድ ተካቶ እንዲተገበር ከፌደራል ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ተደጋጋሚ ውይይቶች ተካሂዷል፤ ይህም ተፈፃሚ እንዲሆን የአስፈፃሚ አካላትን ተግባርና ሃላፊነት ለመወሰን የወጣው አዋጅ 916/2008 ዓ.ም. በተደነገገው መሰረት ተቋማት ኃላፊነታቸውን መወጣት ያልቻሉ መሆኑ፤ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞች አካል ጉዳተኞችን ያካተተ እንዲሆን መስሪያ ቤቱ በተደጋጋሚ ለጤና ጥበቃ ባስገነዘበው መሠረት በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ስራዎችን እንዲሰሩ በመደረግ ላይ ቢሆንም በቂ አለመሆኑ፤ የአካል ጉዳተኞችን የሚሰጡ አገልግሎቶች ተደራሽ ለማድረግ ማለትም / የምልክት ቋንቋ፣ ብሬል፣ የንክኪ ቋንቋ… ወዘተ/ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች በቂ አለመሆናቸው ግንዛቤ የተወሰደ ስለሆነ ተቋማቸው በይበልጥ ጠንካራ ስራዎች ማከናወን የሚገባው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

72. በመሆኑም የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ እና የስነተዋልዶ የጤናና የግንዛቤ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመስራት በስትራቴጂክና በዓመታዊ ዕቅድ በማቀድ ውጤታማ የሆነ አፈፃፀም ለማምጣት በትብብርና በቅንጅት አለመስራቱ፤ አካል ጉዳተኞች በሚረዱትና በሽታውን ለመከላከል በሚያስችል ሁኔታ ለጉዳት አልባ ሰዎች የሚቀርቡ የመተላለፊያ መንገዶችና የመከላከያ ዘዴዎች ለጉዳተኞቹ በጉዳት ዓይነታቸው በሚመች መልኩ እንዲገነዘቡት የሚያስችል በቂ ሥራ እየተሠራ ባለመሆኑ ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው የጤና አገልግሎት አካል ጉዳተኞችን በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚያገኙ ስለመሆኑ የሚደረግ ድጋፍና ክትትል በተመለከተ

73. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ለአካል ጉዳተኞች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚያገኙ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም ትምህርት ቤቶችን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው ከመዘጋጀት ጀምሮ

እንደጉዳታቸው አይነት ተስማሚ የሆነ ማለትም ለዓይን ሥውራን ብሬል፣ መስማት የተሳናቸው የምልክት ቋንቋ እንዲሁም መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/ የተሟላ ተደራሽ የሆነ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች፣ የሰለጠኑ መምህራን ወዘተ ዝግጅትና አቅርቦት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የአማራጭ የፅሑፍና እያደጉ የሚሄዱ አማራጭ የመገናኛ ስልቶች፣ ዘዴዎችና ቅርፆችን የማስተዋወቂያ ገለፃና የእንቅስቃሴ ክህሎቶች፣ የአቻ ለአቻ እገዛ እና የሥራ ላይ አስተምህሮትን እንዲመቻቹ ሊደረግ፤ እንዲሁም ለሕፃናትና ለሴት አካል ጉዳተኞች ትምህርትን በተመለከተ ይበልጥ ተስማሚነት ባለው ቋንቋ፣ የግንኙነት ዓይነትና ዘዴ አማካኝነት የቀለም ትምህርትንና ማህበራዊ እድገትን ከፍ በሚያደርግ ሁኔታ መሰጠቱን የሚረጋግጥበት ስርዓት እንዲዘረጋ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

74. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ የድርጊት መርሀ ግብሩ የተገለፀው የብሬል ትምህርትን የአማራጭ የፅሑፍና እያደጉ የሚሄዱ አማራጭ የመገናኛ ስልቶች፣ ዘዴዎችና ቅርፆችን የማስተዋወቂያ ገለፃና የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እንዲሁም የአቻ ለአቻ እገዛ እና የሥራ ላይ አስተምህሮትን ተግባራዊ እንዲሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ በመሥራት እንዲመቻችላቸው ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

75. በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሐ/ ላይ አካል ጉዳተኞች እንደጉዳታቸው አይነት መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/፣ ለሕፃናትና ለሴት አካል ጉዳተኞች ትምህርትን ይበልጥ ተስማሚነት ባለው ቋንቋ፣ የግንኙነት ዓይነትና ዘዴ አማካኝነት የቀለም ትምህርትንና ማህበራዊ እድገትን ከፍ በሚያደርግ ሁኔታ መሰጠቱን መረጋገጥ እንዳለበት ቢገልጽም በበቂ ሁኔታ ድጋፍ እያገኙ ስለመሆኑ ክትትል ያልተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተካሄዱ የማስረጃ ክለሳዎች እና ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቶች፣

በናሙና ተመርጠው ከታዩ የክልል ቢሮዎችና የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

76. እንዲሁም ማየትና መስማት በጣምራ ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሚያደርግ ካሪኩለም ያልተቀረፀ መሆኑ፤ አካል ጉዳተኞች ወደ ትምህርት በመግባት መማር እንዲችሉ በአስገዳጅ ሁኔታ ወደ ትምህርት ገበታ መምጣት የሚችሉበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፣ በተጨማሪም የመጣውን የለውጥ ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን በመያዝ የድጋፍና የክትትል ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡

77. በተጨማሪም አካል ጉዳተኞች የሚማሩበት ትምህርት ቤት በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት ምቹ የመማሪያ ህንፃዎችና ክፍሎች፣ የመዝናኛና መፀዳጃ ስፍራዎች፣ ቤተ መፃሕፍት፣ የውሃ መጠጫ ቦታዎች፣ ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ--ተደራሽ አለመሆናቸው፤ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር አካል ጉዳተኞችን በትምህርት አሰጣጥ ተደራሽነት ላይ በቅንጅት ለመስራት የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሠነድ የተፈራረሙ ቢሆንም በሰነዱ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን በአመታዊ በዕቅድ ቢያካትቱም በዕቅዳቸው መሠረት ያልሰሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

78. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ 5 የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት፣ 5 የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ 3 የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ተማሪዎች በተለይም የመጀመሪያው የልዩ ፍላጎት አካቶ ትምህርት ላይ አገር አቀፍ ኮንፍረንስ በ2005 ዓ.ም ከተካሄደ ጊዜ ጀምሮ ተደራሽ የሆኑ የመማሪያ ክፍሎች፣ የመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች፣ በ12 ኮሌጆችና 8 ዩኒቨርስቲዎች የባለሞያና የመምህራን ስልጠናቸዎች እየተሰጠ ቢሆንም በሀገር ደረጃ ብዙ መስራት የሚጠበቅ መሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ከመሆኑ አንፃር ወደ መማሪያ ክፍል ለመግባት ራምፕ ያለመኖርና ምቹ እና ሊደረስበት የሚችል መፀዳጃ ቤት አለመዘጋጀቱ፤

- በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸው ትምህርት መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ባለሙያ ሳይሆን ጉዳት አልባ ተማሪዎችን በሚያስተምር መምህር መሆኑ፣
- በትምህርት ላይ ያሉ ዓይነሥውራን ተማሪዎች  የትምህርት መሣሪያዎቻቸው በብሬል የተዘጋጁ ባለመሆኑ ክፍል ገብተው አዳምጠው እንዲወጡ መገደዳቸው፣
- ለዓይነ ሥውራን በአገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ ማየት በሚችሉ ሰዎች እየተነበበላቸው እንዲመልሱ መደረጉ እና በእኩል ሰዓት ተፈትነው እንዲጨርሱ በመደረጉ ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የትምህርት መጽሐፍት ስርጭት ላይ የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽነት ያገናዘቡ አለመሆናቸው፣
- የተለያዩ አካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናትና ወጣቶች ትምህርት በአብዛኛው አለመጀመራቸውና የጀመሩትም በትምህርታችው አለመግፋታቸው፣
- የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ገብተው እንዲማሩ ድጋፍ ለማድረግ አቅጣጫ ቢያዝም ከሌሎች አካል ጉዳተኞች የተለየ ድጋፍ  የማይደረግላቸው መሆኑን፤
-  በሀገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ከሚሠጡ ተቋምት ከ36 ኮሌጆች ውስጥ 12ቱ (33 በመቶ)፣ ከ33 ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ 5ቱ (15 በመቶ) በጠቅላላው ከ69 የትምህርት ተቋማት ውስጥ 17ቱ (24.6 በመቶ)  ብቻ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸው፣
- በሀገሪቱ ካሉ የአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ሁለት ትምህርት ቤቶች /ተፈሪ መኮነን እና ዳግማዊ ሚሊኒክ / ብቻ ሲሆኑ እነርሱም ሁሉንም የአካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሚያደርጉ አለመሆኑ፤
- የትምህርት ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞችን በትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በጋራ በማቀድ አካል ጉዳተኞችን በትምህርት ዙሪያ ተደራሽ የማድረግ ሥራ አለመሥራቱ፣

- ትምህርት ሚኒስቴር ለአካል ጉዳተኞች በጉዳት ዓይነታቸው የትምህርት መርጃዎችን አዘጋጅቶ ለትምህርት ተደራሽ የማድረግ ሥራ ከ4% ማለፍ አለመቻሉ፣ የተለያዩ የአካል ጉዳት ያለባቸው አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባ ወገኖቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ ማንኛውንም የትምህርት ዓይነት በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ገብተው ለመማር እድላቸው የጠበበ መሆኑ፣
- የሀገሪቱ መደበኛ የትምህርት አሰጣጥ ካሪኩለም ማየትና መስማት በጣምራ የተሳናቸው ዜጎችን በአግባቡ ያካተተ አለመሆኑ፤
- በተመሳሳይም መስማትና ማየት በጣምራ የተሳናቸው ከሌላው የአካል ጉዳተኞች ይበልጥ ጉዳታቸው ውስብስብ በመሆኑና የፌዴራል መንግሥትም ሆነ የክልል መንግሥት ትኩረት በመስጠት በጉዳታቸው ዓይነት ማለትም በከፊል ለሚሠሙ በጆሮ ላይ የሚገጠም ድምጽ ማጉያ ማሽን እና በከፊል ለሚያዩ አጉይ መንጽር እንዲሁም ሙሉ በሙሉ መስማትና ማየት ለማይችሉ የንኪኪ /የታክታይልስ/ ቋንቋ ድጋፍ የማይደረግላቸው መሆኑ፤ ለመረዳት ተችሏል፡፡

79. ስለሁኔታውም የትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለአካል ጉዳተኞች ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ከ1-8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ለዓይነ ሥውራን የብሬል መማሪያ መጽሐፍ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በአማራና በትግራይ ክልል መዘጋጀቱን፣ መስማት ለተሳናቸው የምልክት ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መዘጋጀቱን እና በደቡብ ህዝቦች በመዘጋጀት ላይ መሆኑን ቢገልጹም ለኦዲት ቡድኑ የተጠቀሰውን ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ እንዲሁም መስማትና ማየት በጣምራ የተሳናቸውን በተመለከተ ህይወታቸውን መምራት እንዲችሉ የሚያግዝ የትምህርት ማበልፀጊያ ተቋም ድጋፍ መስጫ ቦታ በኦሮሚያ፣ በደቡብና አዲስ አበባ በማቋቋም ስልጠና የሚሰጥ ቢሆንም ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው የሚማሩበት ሁኔታ እስከአሁን የተሠራ ሥራ አለመኖሩን የሥራ ኃላፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

80. ከዚህ በተጨማሪ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር አካል ጉዳተኞችን በትምህርት አሰጣጥ ተደራሽነት ላይ በተፈራረሙት የመግባቢያ ስምምነት ሠነድ መሠረት በዕቅድ ቢካተትም በተሟላ ሁኔታ በቅንጅት የመስራት ክፍተቶች መኖራቸውን፤እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫዎች እየተሰጡ ቢሆንም በህብረተሰቡ

ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ ችግሩንም ለመቅረፍ በሚያስችል ደረጃ አለመሆኑን የሥራ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

81. በተጨማሪም ከክልሎች ጋር ፖሊሲዎችን መቅረጽ፣ የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ማውጣት፣ ሥልጠናዎችን አዘጋጅቶ መስጠት፣ የአተገባበር መመሪያዎችን እና የትምህርት ካሪኩለም ሥርዓት አዘጋጅቶ ወደ ክልሎች ከማሠራጨት ባለፈ ሥራው የሚሠራው በክልል በመሆኑ የአካል ጉዳተኞች ትምህርታቸውን ለመማር ምን ያህል ድጋፍ እንዳገኙ ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ሴት አካል ጉደተኛ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ገብተው እንዲማሩ አቅጣጫ ቢያዝም ከሌሎች ጉዳት አልባ መደበኛ ሴት ተማሪዎች በተለየ መልኩ አወንታዊ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ቢጠበቅም ድጋፍ አለመደረጉን የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

82. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች ለአይነ ስውራን አካል ጉዳተኞች የብሬል ድጋፍ ዕቅድ ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ 2007 ዓ.ም ለ80 ዓይነሥውራን የብሬል ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ ለ35 ብቻ ድጋፍ በማድረጉ 45ቱ የድጋፉ ተጠቃሚዎች አለመሆናቸው ሲታወቅ በ2006 ዓ.ም. እና በ2008 ዓ.ም ቢሮው ስራው ቢያቅድም በዕቅዱ መሠረት ድጋፍ እንዳላደረገ ታውቋል፡፡
- በኦሮሚያ ክልል  የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በ2006 ዓ.ም. ለአይነስውራን የብሬል ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ ያላከናወነ ሲሆን፣ በ2007 ዓ.ም ለ322 ድጋፍ ለማድረግ ቢያቅድም ሙሉ በሙሉ አለመከናወኑ፣ እንዲሁም በ2008 ዓ.ም ለ1530 ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ ለ73 ብቻ ድጋፍ በማድረጉ 1457 ዓይነ ሥውራን የብሬል ድጋፍ አለማግኘታቸው ታውቋል፡፡
- በትግራይ እና በጋምቤላ ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ከ2006-2008 በጀት ዓመት ለዓይነ ሥውራን የብሬል ድጋፍ ለማድረግ ቢያቅድም ዕቅዳቸው ተግባራዊ እንዳላደረጉ ታውቋል፡፡
- በተመሳሳይም ከላይ የተገለፁት የክልል ቢሮዎች ከ2006-2008 በጀት ዓመት የምልክት ቋንቋ መጽሐፍ ድጋፍ ለማድረግ አቅደው አለማከናወናቸውን በኦዲቱ

ወቅት ቀርበው ከተከለሱት ማስረጃዎች ማለትም ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በላኩት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርታቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. ስለሁኔታው የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የተጠቀሱት ችግሮቹ ትክክል መሆናቸውን ገልፀው ችግሮቹን ለመፍታት በቅንጅት ሥራዎችን በማጠናከር መቀጠል የሚገባ መሆኑን፤ የአካል ጉዳተኞችን በትምህርት ተደራሽነት ከፍ ለማድረግ እንዲቻል ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሞ በየጊዜው ስለአፈፃፀሙ ክትትል እየተደረገ በመሆኑ የመከታተያ ስርዓት እንዳልተዘረጋ ሊቆጠር አይገባም ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በመግባቢያ ሰነዱ መሰረት ስለአፈፃፀሙ ክትትል ስለማድረጋቸው ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የተገለፀውን መልስ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

84. በሌላ መልኩ በትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ውጤታማ እንዲሆኑና አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች እንዲሟሉ የማድረግ ኃላፊነት የትምህርት ሚኒስቴር መሆኑን እና ይህንን ኃላፊነቱን በተገቢው መንገድ መወጣት እንዲችል በተለያዩ ጊዜያት ለትምህርት ባለሙያዎችና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና ከመስጠት ውጭ ተቆጣጣሪ በመሆን በኦዲት ቡድኑ የተጠቀሱ ጉዳዮች እንዲሟሉ የማድረግ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በጣምራ ማየትና መስማት ስለተሳናቸው ዜጎች የክልል ባለሙያዎችና የሚመለከታቸው አካላት እንዲገነዘቡ በተከታታይ ሁለት ዓመት በዕቅድ ተይዞ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጣና የተሰጠ መሆኑ፤ መስማት የተሳናቸው ዜጎች በተቋማት ተገቢ የተግባቦት አገልግሎት እንዲያገኙ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለ3 ተከታታይ ዓመታት የምልክት ቋንቋ ስልጠና ለተለያዩ ተቋማት የመረጃ ዴስክ ሰራተኞች፣ ፖሊስ፣ የፍትህ አካላት… ወዘተ ስልጠና ተሰጥቷል፤ሲሉ ገልፀዋል፡፡

85. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ብቻ ችግሮቹን ለመፍታት በቂ ባለመሆኑ እና የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተሰጠው ድርብ ኃላፊነት ማለትም ድጋፍና ክትትል በማድረግ ያሉ ችግሮች እንዲቀረፉ ለውጥ የሚያመጡ ስራዎቸን በመስራት አስተዋፅኦ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ በሥራ ኃላፊዎቹ የተሰጠው መልስ ተገቢና በቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡

86. በመሆኑም የአካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች በትምህርት ስርዓት፣ በመማሪያ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ፣ በትምህርት ዘዴ፣ ምቹ የመማሪያ አካባቢዎች ወዘተ ከጉዳት አልባ ወገኖቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ ገብተው ለመማር ያልቻሉ መሆኑ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ማየትና መስማት በጣምራ የተሳናቸው ዜጎች በሀገሪቱ የመደበኛ የትምህርት አሰጣጥ ካሪኩለም ተደራሽ ባለመሆናቸው የመማር እድል ያላገኙ በመሆኑ ከጉዳት አልባ ወገኖቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ ማንኛውንም የትምህርት ዓይነት በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ገብተው ለመማር እድላቸው የጠበበ ከመሆኑም ባሻገር ተገቢ ትምህርት በተገቢው ጥራት በማቅረብ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች እኩል ተደራሽ እንዳይሆን በማድረግ በትምህርት ዙሪያ ሀገሪቱ የፈረመችው ኮንቬንሽንም ሆነ አስገዳጅ ህጎች እንዳይተገበሩ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## አካል ጉዳተኞች በሚገነቡ ሕንፃዎች እና ለህዝብ አገልግሎት ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና መገልገያ ተቋማት ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ

87. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚገነቡ ህንፃዎች ከዲዛይን ጀምሮ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ መሆኑን፤ ማንኛውም የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና ሌሎች መገልገያ ተቋማት ውስጥ በተሽከርካሪ ወንበር ለመንቀሳቀስ የሚገደዱትንና መራመድ የሚችሉ ሆኖ ደረጃ መውጣት የሚሳናቸውን ጨምሮ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች በሚመች መልኩ የተዘጋጁ ስለመሆኑ፣ ሊደርሱባቸው የሚችሉ በቂ መጠን ያላቸው መፀዳጃ ቤቶች መዘጋጀቱን እንዲሁም በህንፃዎች ውስጥ የሚገጠም አሳንሰር ማየት ለተሳናቸው የአካል ጉዳተኞች አመች በሆነ መልኩ የበር መዘጋትና መከፈት እና የወለል ከፍታን በድምፅ የሚገልፅ መሳሪያ የተገጠመለት እና የውስጥና የውጭ መጥሪያ ደወል የብሬል ፅሁፍ ያለበት ስለመሆኑ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ተደራሽ ስለመሆናቸው በቅንጅት ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. በተቀመጠው መሰረት የሚገነቡ ህንጻዎች ከዲዛይን ጀምሮ፣ በትግበራ ላይ ክትትል በማድረግ እና በርክክብ ወቅት አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ

ባደረገ መልኩ እየተገነቡ ስለመሆኑ እና ተግባራዊ ስለመደረጉ ቅንጅታዊ የክትትል ስራ የሚከናወንበት ስርዓት ተዘርግቶ ክትትል እያደረገ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

89. በኦዲት ቡድኑ ጉዳዩ አስመልክቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና፤ በናሙና በታዩ በክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችና በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ መሠረት፤

- ከህንፃ ዲዛይን ጀምሮ በግንባታ ወቅት እንዲሁም የግንባታ ስራው አካል ጉዳተኞችን ባማከለ መሰረት ስለመገንባቱ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣
- በክልሎች የሚገነቡ ህንፃዎች ለምሳሌ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኢትዮጵያ ሱማሌ፣ በኦሮሚያ በህንፃ አዋጅ ቁጥር624/2001 መሰረት አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ አድርገው የሚገነቡ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤
- በህንፃ አዋጁና መመሪያው ላይ በሚፈለገው ደረጃ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በሰፊው አለመሰራታቸው፣
- የህንፃ አዋጅ ቁጥር.624/2001ን ለማስፈፀም በየክልሉ የተቋቋሙ ህንጻ ሹም ጽ/ቤት የህንጻ መመሪያውን ወደ አፈጻጸም ለማምጣት በሚደረግ ጥረት በአፈጻጸም መመሪያ ላይ የታዩ ክፍተቶች መኖራቸው፣
- በህንጻ አዋጁ አደረጃጀት ውስጥ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ባለሙያ ባለመካቱቱ ምክንያት ሙያውን የሚጠይቁ ስራዎች ለምሳሌ፡- ሊፈት የመሳሰሉትን በሙሉ በአንድ ባለሙያ የሚሰራበት አግባብ ያለ በመሆኑ በአፈጻጸም ላይ ችግር መኖሩ፣ በክልል መንግስታት በጀት የሚሰሩ የግንባታ ስራዎች በአዋጁ መሠረት አለመገንባታቸው የደረጃ ሐ ህንጻዎችን (የህዝብ መገልገያ ተቋማት) ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ከማደረግ አኳያ የተለየ እንቅስቃሴ እየተደረገ አለመሆኑ፣
- የኮንዶሚኒየም ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ተደርገው ስለመገንባታቸው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን የማይከታተል መሆኑ፣
- በተጨማሪም አካል ጉዳተኞችን በህንፃ ግንባታ ዙሪያ ተደራሽነት ላይ የሚሠሩ ፈፃሚ አካላት በህንፃ አዋጁ መሠረት ስለመተግበሩ በቂ ዕውቀት አለመኖር፤

- በግንባታ ዙሪያ የተሰማሩ ባለሞያዎች ሁሉም በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መገንባታቸውን ለመከታተልና አዋጁንም ለማስፈፀም የተዘረጋ ስርዓት አለመኖሩ፣ ትኩረት አለመሰጠቱ እና በአዋጁ መሰረት ላልገነቡት ባለቤቶችም ሆነ ለማይተገብሩ ባለሞያዎች ተጠያቂ በማድረግ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ የማያስደርግ መሆኑ፤

- የመፀዳጃ ቤት ሊሰራበት በሚገባ በማንኛውም ህንፃ ውስጥ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የሚመቹና ሊደረሱባቸው የሚችሉ በቂ መጠን ያላቸው መፀዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ሆነው አለመገንባታቸውን እንዲሁም በዚህ ዙሪያ በቂ የሆነ የክትትል ስራዎች የማይደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

90. ጉዳዩን አስመልክቶ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ  በየክልል ከተሞች የተዋቀሩት የህንፃ ጽ/ቤቶች የግንባታ ፈቃድ ከመስጠት በዘለለ በጽ/ቤቱ በቂ የሰው ኃይል የማይመደብ መሆኑ፤ በሚፈለገው ደረጃ የቁጥጥር ሥራ አለመሠራቱ፣ ፈፃሚዎቹ ትኩረት ሠጥተው አለመሥራታቸውና በሙያ ስብጥር እንዲሁም በሎጂስቲክ ተሟልተው አለመገኘታቸው፣ በኮንስትራክሽን ሚኒስቴርም ሆነ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር  በሚፈለገው ደረጃ በህንጻ አዋጅና መመሪያው ላይ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎች በሰፊው ባለመሥራታቸው በከተማ ህንጻ ሹም  በኩል የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው እየተገነቡ ያሉ ግንባታዎች  በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. እና በህንፃ መመሪያው መሠረት የሚከናወኑ ስለመሆኑ በቂ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ያልተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

91. ጉዳዩን በተመለከተ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የሚገነቡ ህንጻዎች የአካል ጉዳተኞችን ተካታችነት በሚያረጋግጥ መልኩ እየተገነቡ እንዳልሆነ በቀድሞ ለሚመለከታቸው የኮንስትራክሽንና ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በተደጋጋሚ ለማሳሰብ የተሞከረ መሆኑን እና ከዚህ ባለፈ ለህንጻ ተቆጣጣሪዎችና ዲዛይነሮች በኮንቬንሽኑ ላይ የተቀመጠውን የህንጻ ተደራሽትና ተያያዥ ህጎችን ለማስገንዘብ ስልጠና የተሰጠ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ የተጠቀሰው መስሪያ ቤት በየክልሉ

የህንጻ ሹም የመደበ ቢሆንም እየተገነቡ ያሉ ህንጻዎች በሙሉ የግንባታ ፈቃድ በሚያዘው መሠረት ስለመፈፀማቸው እና በቂ ቁጥጥር ካለመደረጉ ባሻገር ግንባታቸው ያለቁ ህንጻዎች ርክክብ ሲፈጸም ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸው ሳይረጋገጥ የሚቀር መሆኑ፣ በዘርፉ የታዩ ጉድለቶች ሰፊ በመሆናቸው ችግሮቹን ለመቅረፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀትና በመተባበር ተገቢ ሚናውን መወጣት እንደሚገባው ግንዛቤ ወስደናል ብለዋል፡፡

92. በመሆኑም በሀገሪቱ የሚገነቡ ህንፃዎች ከዲዛይን ጀምሮ እስከ ግንባታና ርክክብ ድረስ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ ስለመከናወናቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ክትትል የማይደረግ በመሆኑ በሀገሪቱ በተለያዩ አከባቢዎች የሚገነቡ ህንፃዎች አካል ጉዳተኞች ባግባቡ እንዳይጠቀሙና አካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች እንደሌሎቹ ጉዳት አልባ ዜጎች ተደራሽ እንዳይሆኑ እና ኑሮአቸውን፣ እንቅስቃሴአቸውንና ህይወታቸው እንዲከብድ በማድረግ እኩል ዕድል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## አካል ጉዳተኞች ለማንኛውም ለሕዝብ አገልግሎት ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና መገልገያ ተቋማት ውስጥ ተደራሽ በሆነ መልኩ መረጃ የሚገልፁ ወይም የሚያስተላልፉ መሆናቸውን በተመለከተ

93. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ድርጅቶች የሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብተው የተዘጋጁ መሆኑን ፣ በግልፅ የሚታዩ ምልክቶችን፣ ብሬሎችንና በቀላሉ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ቅፆችን፣ የቀጥታ ድጋፍ ዓይነቶችንና መሪዎችን፣ አንባቢያንንም ሆነ የምልክት ቋንቋ አጠቃቀም የሰለጠኑ አስተርጓሚዎችን፣ መሪ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የድምጽ መረጃ የሚሰጡ መሣሪያዎችን የሚያስቀምጡ ወይም የሚያቀርቡ ስለመሆኑ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን በመስጠት፣ ተግባራዊ መሆኑን የሚከታተልበት ሥርዓት በመዘርጋት ድጋፍ እና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽን አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሰረት ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ድርጅቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብተው ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚከታተልበት ሥርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል በቂና ውጤት የሚያመጣ የግንዛቤ ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡

95. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩ አስመልክቶ ባካሄደው የማስረጃዎች ክለሳ እና በናሙና መርጦ ባያቸው በክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ለአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት የሥራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቆች በሰጡት መልስ መሠረት፣

- በፌዴራልም ሆነ በክልሎች በግልና በመንግሥት የተሠሩ ለሕዝብ ክፍት የሆኑ የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ለምሳሌ ባንክ፣ የሕዝብ ማህበራዊ ጉዳዮች መስጫ ቦታዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የማምለኪያ ቦታዎች---ወዘተ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆናቸው እና ይህን ለማስተካከል ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተቋማቱ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮና ተቀናጅቶ የማይሰራ መሆኑ፣
- በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ሁሉም ፈፃሚ አካላት የግንዛቤ ክፍተት መኖሩ፣
- አገልግሎቱን ፈልገው ወደ ማንኛውም አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚመጡ አካል ጉዳተኞች ከመግቢያ በር ጀምሮ ለዊልቸር ምቹ ባለመሆናቸው አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ በሰው እርዳታ እንዲገቡ መደረጉ፣
- የክልል ቢሮዎች የሚሠሩባቸው ህንፃዎች ምቹ ሆነው የማይሰሩ መሆኑ በዚህም ምክንያት ለተለያዩ ጉዳዮች የሚመጡ የአካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች በሸክም ወደ ተለያዩ ቢሮዎች የሚወሰዱ መሆኑ፣

- እንዲሁም አገልግሎት ከሚሰጡት የግልና የመንግሥት ባንኮች አብዛኞቹ ከህንፃ አሠራራቸው ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞች እንደጉዳት አይነታቸው ተደራሽ ሆነው አለመዘጋጀታቸው ለምሳሌ ምቹ የዊልቸር መግቢያ ያለመኖሩ በሽክም የሚገቡ መሆኑ፣ ዓይነሥውራን ማንኛውም የጉዳቱ አልባ ተገልጋይ የሚጠቀምበት የኤቲኤም ማሽን አገልግሎት ለጉዳተኛው ተደራሽ አለመሆናቸው እና በባንክ ያለ ገንዘባቸውን ለመውሰድ የመታወቂያ ፎቶ ኮፒ ማሲያዝ የሚችል የጉዳቱ አልባ ዋስ የሚጠየቁ መሆኑ፣ እንዲሁም መስማትና ማየት በጣምራ ችግር ያለባቸው ሙሉ በሙሉ የባንክ አገልግሎት ለማግኘት ምቹ አለመሆኑ፤
- የክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሰው ኃይል እጥረት፣ የበጀት ማነስና የአቅም ውስንነት አለብን በሚል የክትትልና የድጋፍ ሥራ አለመሥራታቸውን ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

96. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀፅ 2/ለ/ መሠረት የተጠቀሱ ጉዳዮች ተግባራዊ እንዲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቻለው አቅም የተለያዩ መድረኮችን በማመቻቸት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች የተሰጠ መሆኑን፤ ነገር ግን የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆናቸው ግንዛቤ የተወሰደ ስለሆነ የሚመለከታቸው ተቋማት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበኩሉን ድርሻ የሚወጣ መሆኑ ግንዛቤ ይወሰድ ሲሉ መልሰዋል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ኮንቬንሽኑ ተግባራዊ እንዲሆን በየደረጃው እርምጃዎችን በመውሰድ ጠንካራ ሥራዎች ያልተሰሩ በመሆኑ፣ ይህም እንዲተገበር ሚኒስቴር መ/ቤቱ የበኩሉን ድጋፍና ክትትል ያደረገ ባለመሆኑ፣ እንዲሁም ችግሩ በግንዛቤ ማስጨበጫ ብቻ እንደማይፈታ እየታወቀ 'ግንዛቤ በማስጨበጥ የበኩሉን ድርሻ የሚወጣ መሆኑ ግንዛቤ ይወሰድ' ማለታቸው ተገቢነት ያለው መልስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

97. በመሆኑም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 2(ለ) መሠረት ለህዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶች በማመቻቸት እና በማቅረብ ሥራ ላይ

የተሰማሩ የግልና የመንግስት ድርጅቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመደረጋቸው አካል ጉዳተኞች በኮንቬንሽኑ የተቀመጡላቸው መብቶች እንዳይጠበቁና በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

## አካል ጉዳተኞች የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ማንኛውም ተሽከርካሪዎችና መገልገያዎች ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ

98. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችና መገልገያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሆነ መልኩ መዘጋጀታቸው እና አገልግሎት መስጠታቸው ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ እንዲሆን እንዲሁም ተደራሽ ባልሆኑት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

99. ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳዎች እና ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ ባካሄዳቸው ቃለመጠይቆች መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትራንስፖርት ሚኒሰቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኞች በህዝብ ትራንስፖርት እንደጉዳት አይነታቸው ተደራሽ በሆኑ አገልግሎቶች ያልተሟሉ መሆናቸውንና የትራንስፖርት ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተፈራረሙት የመግባቢያ ሠነድ መሠረት አካል ጉዳተኞችን በትራንስፖርት መሠረተ ልማት አገልግሎትና አቅርቦት ላይ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ ዕቅድ በማቀድ ተደራሽ እንዲሆኑ የተሰሩ ስራዎች አለመኖራቸው ታውቋል፡፡ የትራንስፖርት ባለስልጣን የህዝብ ትራንስፖርት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የደረጃ መስፈርት ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም የደረጃ መስፈርቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው መዘጋጀታቸው እንደ ደረጃ መስጫ መስፈርት ያልተካተተ መሆኑ እንዲሁም አብዛኛው የትራንስፖርት አቅርቦቶች አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ አለመሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

100. አንበሳ የከተማ አውቶቡስ ለሁሉም የአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ባደረገ መልኩ ባይሆንም በዊልቸርና በክራንቹ የሚንቀሳቀሱ አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ለማድረግ የሚችሉ ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው አውቶቢሶች በብረታብረት ኢንጅነሪንግ

ኮርፖሬሽን ተመርተው አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ ቢሆንም ሁሉም አውቶቢሶች የተገጠመላቸው ቴክኖሎጂዎች ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት ለመስጠት እንደማይጠቀሙበት እና ቴክኖሎጂውም ዝጐ ከጥቅም ውጭ መሆኑ፣ በዚህ ምክንያት አካል ጉዳተኞች በሰው ሸክም ወደ አውቶቡሶች የሚገቡ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

101. በትራንስፖርት ሚኒስቴር እና በብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን በአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አገልግሎት ከሚውሉ 410 አውቶቢሶች ውስጥ 15ቱን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ ተደርጐ እንዲሠሩ ከመጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም. የስምምነት ውል ቢፈራረሙም እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የተጠቀሱት አውቶቡሶች አገልግሎት ላይ ስለመዋላቸው እንዲሁም አውቶቢሶች ለሁሉም አካል ጉደተኞች እንደ ጉዳት ዓይነታቸው ተስማሚ በሆነ መልኩ እንዳልተዘጋጁ ታውቋል፡፡

102. በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ስር የሚገኙት የቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ኤርፖርቶች ማለትም/መቀሌ፣ ድሬዳዋ፣ ባህርዳር/ የመንገዶኞች ማስተናገጃ ተርሚናሎችም ሆነ ከመኪና ማቆሚያ ወደ ተርሚናሎች የሚያደርሱ መንገዶች ለባለ ዊልቸር አካል ጉዳተኞች ተደራሽነታቸው በከፊል ብቻ የተሟሉ መሆኑና በተለይም ዓይነ ሥውራን፣ መስማት የተሳናቸውና መስማትና ማየት በጣምራ የተሳቻውን ተደራሽ ያደረጉ አለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

103. የአዲስ አበባ ቀላል የከተማ ባቡር አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች በሁሉም ተርሚናሎች አሳንሰር ለመግጠሚያ የሚውሉ ግንባታዎች የተዘጋጁ ቢሆኑም እስከ ጥር 2009 ዓ.ም. ድረስ አሳንሰሮቹ ተገጥመው አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ አለመሆናቸው፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር ውስጥ የቃልና የፅሁፍ መልክት የሚተላለፍ ሲሆን የፅሁፍ መልዕክቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ የሚፃፍ በመሆኑ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆን ላይ ክፍተት መኖሩ ታውቋል፡፡

104. በተጨማሪም በሀገር ደረጃ የሚገኙ የሀገር አቋራጭ መናኸሪያ ቦታዎች ከትኬት መቁረጫ ጀምሮ አገልግሎት የሚሰጡ የሀገር አቋራጭ የትራንስፖርት ስምሪት ቦታዎችና እና አውቶቡሶቹ ለአካል ጉዳተኞች በተሟላ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆናቸውን በኦዲት ወቅት በተካሄደ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

105. ስለሁኔታው የትራንስፖርት ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በትራንስፖርት ተደራሽነት ላይ የጋራ መግባቢያ ሰነድ ቢኖራቸውም ሁሉም ክልሎች በሰነዱ ተፈጻሚ ለማደረግ ባሰቀመጧቸው ዝርዝር አቅጣጫዎች አካል ጉዳተኞች በትራንስፖርት መሰረተ ልማት ተደራሽ ለማደረግ፣ ስልጠና በመስጠት፣ በመስክ ጉብኝት፣ ክፍተቶቹን በመወያየት ለመቅረፍ የተቀመጠ ቢሆንም ሥራዎች አለመሰራታቸውን ገልፀዋል፡፡

106. ጉዳዩን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የትራንስፖርት ተደራሽትን ለማሻሻል አበረታች ጅምሮች ያሉ ቢሆንም በኦዲት ቡድኑ የተሰጡ አስተያየቶች ተገቢና እውነትነት ያላቸው በመሆናቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ይበልጥ በመተባበር የበኩሉን ድርሻ የሚወጣ ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡

107. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትራንስፖርት ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ፣ የሀገር አቋራጭ አውቶቢሶች፣ የከተማ አውቶቢሶች፣ የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር እንዲሁም የትራንስፖርት መናህሪያዎችና የትኬት መቁረጫዎች እና በሀገሪቱ የሚገኙ ኤርፖርቶች በአገልግሎት አሰጣጣቸው በአብዛኛው የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ አለመሆናቸውና ችግሩ እንዲፈታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቂ ውጤታማ ስራዎችና ክትትሎች አለመደረጋቸው የአካል ጉዳተኞች ከቦታ ወደ ቦታ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ያለችግር እንዲያካሂዱ ያላስቻለ እና በህግ የተሰጣቸው የዕኩል ተጠቃሚነት መብት እንዳይረጋገጥ አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲለሙ እና የለሙ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ

108. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/ሰ/ መሰረት የመረጃ መረብን ጨምሮ በአዳዲስ የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች፣ የእንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ

መገልገያዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የምርምርና የልማት ስራዎችን እንዲካሄዱ እና የለሙ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ተፈፃሚ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

109. ይሁን እንጂ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር ጉዳዩን አስመልክቶ የመግባቢያ ሠነድ የተፈራረመ ሲሆን በዚሁ መሠረት ዌብ ሳይቶችን የሚያለማ ሲሆን የለማው ዌብ ሳይት ለአካል ጉዳተኞች ስለመድረሱ ወይም አገልግሎት እየሰጠ ስለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን የማይከታተል መሆኑ ታውቋል፡፡

110. እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን፣ የእንቅስቃሴ መረጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ መገልገያዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የምርምርና የልማት ስራዎችን እንዲካሄዱ ድጋፍ እና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም የለሙ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ የማስተባበር፣ የማቀናጀት እና የመደገፍ ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑ፤

111. በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ በተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በታዩ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና የተሃድሶ ማዕከላት የሥራ ኃላፊዎች በተካሄዱ ቃለ መጠይቆች መሠረት፤

- አካል ጉዳተኞችን ተሳታፊ በሚያደርግ መልኩ በጉዳት ዓይነታቸው መረጃዎችን የማመቻቸት፣ የማሰራጨትና ተደራሽ ለማድረግ በትብብርና በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች ከሌሎች የጉዳት አልባ ወገኖቻቸው ጋር በእኩል ደረጃ የፈለጉትን የመረጃ መረብ የማህበራዊ ድህረገጾች እንዲሁም ሌሎች የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን መቀጠም እንዲችሉ በቂ ስራዎች አለመሰራታቸው፣

- ለአካል ጉዳተኞች የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን የእንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ መገልገያዎችን ጨምሮ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የምርምርና የልማት ሥራዎችን በማካሄድ ተደራሽ አለመሆኑ፣
- ዓይነ ሥውራን የድምጽ ሶፍት ዌር /ጃውስ ሶፍት ዌር/ ቴክኖሎጂ ተደራሽ በሆነ መልኩ አለመሰራጨቱ፣ በጽሑፍ የሚነገሩ/የሚገኙ/ መረጃዎች ወደ ብሬል ተለውጠው እንዲጠቀሙ ያለመደረጉ፣
- የአካል ጉዳተኞች ማህበራት የተለያዩ የልብ ወለድ መጽሐፍትን ወደ አውቶርኔት /የተለያዩ መጽሐፍትን ወደ ድምጽ መቀየር/፣ የአማርኛ ሶፍት ዌዩርን በማልማት እንዲጠቀሙ በሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እገዛና ድጋፍ የማይደረግለት መሆኑ እና ከአዲስ አበባ ውጭ ላሉ አይነ ስውራን ተደራሽ አለመሆኑ፤
- የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለመኖሩ የኢንፎርሜሽን አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ አለመቻሉ፣
- መስማትና ማየት በጣምራ የተሳናቸው ወገኖች እንደጉዳታቸው አይነት ሊረዳቸውና ህይወታቸውን ሊያቀሉ የሚችሉ የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ዕድል ተጠቃሚ የሚያደርጉ ቴክኖሎችዎች እንዲለሙ አለመደረጉ፤ እንዲሁም ለትምህርት መርጃ ድጋፍ ሊሆኑ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች እንዲለሙ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ አለመሆኑ፤
- ለአካል ጉዳተኞች ለመንቀሳቀሻ አገልግሎት የሚውሉ በባትሪ የሚሠራ ባለሁለት እግር እና ባለሶስት እግር ሞተር ብስክሌት እንዲጠቀሙ ድጋፍ የማይደረግላቸው መሆኑ፣ በአካል ጉዳተኞች ድጋፍ አሰጣጥ ዙርያ መረጃዎችን አሰባስቦ በማደራጀት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያደርግ ስራ አለመሰራቱን፣ ገልፀዋል፡፡

112. ስለጉዳዩ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ በኮንቬንሽን አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ የተገለፀውን ተፈጻሚ ለማድረግ ኃላፊነቱ እና ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ ቴክኖሎጂ የማልማት ስራ የመገናኛና ኢንፎርሜሽ ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መሆኑን ገልፀው በኦዲት ቡድኑ

የተጠቀሱ በመረጃና በኢንፎርሜሽን በኩል ያሉ የተደራሽነት ችግሮች ያሉ መሆኑንና ችግሮቹን ለመቅረፍና ተግባራዊ እንዲሆን የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተጠቀሰው ተቋም ጋር የስራ ግንኙነት በማድረግ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ጥረት ያደረገ ቢሆንም በተፈለገው ደረጃ ተፈጻሚ ባለመሆኑ ወደፊት የስራ ግንኙነቱን ይበልጥ በማሻሻል በመተባበርና በመቀናጀት መስራት እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

113. በመሆኑም አካል ጉዳተኞች በመረጃ መረብ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች እንዲለሙና ተደራሽ እንዲሆኑ ባለመደረጉ አካል ጉዳተኞች በቴክኖሎጂዎች በመታገዝ በጉዳታቸው ምክንያት የመጣውን ውስንነት ለመቀነስና ህይወታቸውን ለማቅለል የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎች እንዳይተዋወቁ፣ እንዳይስፋፉና እንዳይጠቀሙ በማድረግ የአካል ጉዳተኞች በቴክኖሎጂዎቹ ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ጥቅም እና ድጋፍ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

## የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ በሁሉም የሚዲያ አካላት መካተቱን፣ በባህል፣ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ በመዝናኛ ዝግጅቶች የሚሳተፉ መሆናቸውን በተመለከተ

114. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኞች በሁሉም የሚዲያ አካላት በማካተት የተለያዩ መረጃዎች በተለይም መስማት ለተሳናቸው የዕለቱ ዜና በቴሌብቪን ፕሮግራም በምልክት ቋንቋ ባለሙያ ተደራሽ መሆናቸው፤ እንዲሁም የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን፣ ፊልሞችንና ቲያትሮችን፣ ባህላዊ ክንውኖችን እንዲሁም ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በመዝናኛ፣ በዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና በስፖርት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል ተገቢ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚከታተልበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

115. ይሁን እንጂ የአካል ጉዳተኞችን ከጉዳት አልባ ዜጎች እኩል በሁሉም የሚዲያ አካላት በማካተት የተለያዩ መረጃዎች በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ አለመሆናቸው እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በቂ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

116. እንዲሁም በኦዲቱ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግልና የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ፕሮግራሞች ቢሰሩም ለየትኛው አይነት የአካል ጉዳት ምን አይነት አገልግሎት (ፕሮግራም) እንዳላቸው ለምን ያህል የአየር ሰዓት እንደሚሰጡና ያልተዳሰሱ አካባቢዮችን እንዲያካትቱ ስለመደረጉ እና ይህንም የሚገልፅ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲኖርና አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ እንዳላደረገ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እነማን እንደሆኑ ለየትኛው ችግር የት መሄድ እንዳለባቸው መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ የተቀረፁ አለመሆናቸው እና በሚዲያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችም አካል ጉዳተኞች ሊረዱት በሚችል ቋንቋ በጉዳታቸው ዓይነት ተዘጋጅተው በመቅረብ ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችል የሚድያ ስርዓት የሌለ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህንን አስመልክቶ በሚድያ ተደራሽ መሆን እንዲችሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የድጋፍና ክትትል ስራዎች እንዳላከናወነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

117. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኞች የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን፣ ፊልሞችንና ቲያትሮችንና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖችን በተመቻቸ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆኑ የክትትል ስራ አለመስራቱ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በመዝናኛ፣ በዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና በስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተዘረጋ ሥርዓት እና የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

118. በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተከለሱ ማስረጃዎችና እና በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል ቢሮዎች፣ የአካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ማህበራት እና በአካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ፌዴሬሽን የሥራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቆች በሰጡት መልስ መሠረት፤

- በሚዲያ ተቋማት በኩል አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ለማድረግ ቁርጠኝነት አለመኖር፣ በሚዲያ ተቋማት እና በክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አለመኖሩ፣
- የክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በሰው ኃይልና በፋይናንስ አቅም ውስንነት አለብን በሚል አለመስራታቸው፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ

ሚኒስቴርም የክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት በቂ ድጋፍ አለማድረጉ እና እስከ ወረዳና ዞን በመውረድ ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ሥራ አለመስራቱ፤

- በተለይም ማየትና መስማት በጣምራ የተሳናቸው አካል ጉዳተኞች ከችግሩ ውስብስብነት የተነሳ ተጠቃሚና ተደራሽ አለመሆናቸው ይህን ሁኔታ ለመቅረፍ ስለሚያስፈልጋቸው የድጋፍ ዓይነቶች በስፋት በሚዲያ ተካቶ ግንዛቤ በመፍጠር ለዚህ ችግር ድጋፍ ለማድረግ ፍላጎት፣ ዕውቀትና አቅም ያላቸው ዜጎችና በጐ አድራጐት ድርጅቶች እንዲፈጠሩ /እንዲስፋፉ/ እንዲሁም እንዲታወቁ በማድረግ የዚህ ችግር ተጠቂ ዜጎች ተገቢ ድጋፍ፣ ክብካቤና ግንዛቤ እንዲኀለብት አለመደረጉ፤
- ለዓይነ ሥውራንና መስማት ለተሳናቸው በተለያዩ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች ለህብረተሰቡ የሚደርሱ ማንኛውም መረጃዎች በብሬልና በምልክት ቋንቋ ተዘጋጅቶ በእኩል ደረጃ እንዲደርሳቸው እየተደረገ አለመሆኑን፤
- በቴለቪዥን የሚተላለፈው የመዝናኛ ኘሮግራሞች ላይ ገላጭ ጽሑፎችና የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች አለመኖር፣ ፊልሞች የግርጌ ጽሑፍ እንዲኖራቸው ተደርገው አለመሠራት፣
- ሁሉም ቴአትር ቤቶች፣ ሲኒማ ቤቶችና ሙዚየሞች የእንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ በሆነ መልኩ አለመዘጋጀታቸው፣
- ዋና ዋና ትርኢቶችና ክብረ በዓላት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሆኑ ቦታዎች እንዲዘጋዘጋጁ እንዲሁም የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ እንዲኖራቸው አለመደረጉ፣
- የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲሁም የቱሪዝም ቢሮዎች ለአካል ጉዳተኞተ ተደራሽ አለማድረጋቸው፣ እንዲሁም ባህላዊ ቁሳቁሶችንና ቅርጻችንና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖችን በተመቻቸ ሁኔታ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆኑ፣
- እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባ እኩዮቻቸው ጋር የእኩልነት ስሜት ተሰምቷቸው በቴሌቪዥን፣ በፊልሞችና በቲያትሮች ዝግጅቶች ላይ በእኩል ደረጃ የመሳተፍ እድላቸው ዝቅተኛ መሆኑ፤

➢ ለአካል ጉዳተኞች ፊልሞችንና ቲያትሮችንና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖችን እንደጉዳታቸው አይነት ለሁሉም አካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባለው መልኩ የሚዘጋጁ አለመሆኑ፤

➢ አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ከተለያዩ አለም አቀፍና ሀገራዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር እንደጉዳት አይነታቸው የሚያሳትፉ የስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉ በማድረግ እና አዳዲስ የስፖርቶች አይነቶችን እንዲለመዱ እና እንዲተዋወቁ በበቂ ሁኔታ የማስታወቅና የመደገፍ ሥራ እንደማይሰራ ገልፀዋል፡፡

119. በተጨማሪም ለአካል ጉዳተኞች ዜጎች የተለያዩ መረጃዎች ባሉ ሚዲያዎችና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ የድርጊት መርሀ ግብር /2004-2013/ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የሚሰጠው አንዱ መስፈርት ስለአካል ጉዳተኞች የሚያወሱ ፕሮግራም መያዛቸው መሰረት አድርጎ ቢሆንም ምን ያህል ሽፋን መስጠት እንዳለባቸው፣ የሚያነሱዋቸው ጉዳዮች ያልተዳሰሱና ትኩረት ያላገኙ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ የሚያስችል ስርዓት አለመቀመጡ፣ የተዘጋጁ ፕሮግራሞች በየትኛው ሚድያ፣ በየትኛው ሰዓት፣ በምን ርዕስ ወዘተ አስቀድሞ በማስተዋወቅ ተደራሽ እንዲሆኑ አለመደረጉ፣ የአካል ጉዳተኞች ፍላጎት ላይ ዳሰሳ በማድረግ እንደአንገብጋቢነታቸው ቅደም ተከተል በማስያዝ በመቀናጀት የማያቀርቡ መሆኑ፤ እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን መረጃ ተደራሽ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች እንደሌሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

120. ስለጉዳዩ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሬዲዮ ፕሮግራም፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ ፊልሞችና ቲያትሮች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመቀራረብ ስርዓት እንዲዘረጋ በመደረጉ በአሁኑ ሰዓት የሚወጡ ፊልሞች (የድምጽና የምስል ቅንብር እንዲኖራቸው መደረጉ)፤ በቂ ነው ባይባልም በተለያዩ የሬዲዮ ፕሮግራሞች አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ተከታታይ ዘገባዎች የሚቀርቡ መሆኑ፤ በቴሌቪዥን ፕሮግራምም ቢሆን መስማት

ለተሳናቸው ራሱን የቻለ ፕሮግራም መኖሩ፣ ወሳኝ ኩነቶች በምልክት ቋንቋ ሚተላለፉበት መሆኑ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከብሮድካስት ባለስልጣን ጋር በመተባበር የሚዲያ ፎረም መመስረት በመቻሉ ከበፊቱ በተሻለ አኳኋን የሚዲያ ተቋማት አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚ የሚያደርጉ ስራዎች በማከናወን ላይ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

121. እንዲሁም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አካል ጉዳተኛ ዜጎች በሚዲያ ተቋማትን ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚዲያ ተቋማትን ከሚያስተዳድረው ከብሮድካስት ባለስልጣን ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ለጋዜጠኞችና ለሚመለከታቸው አካላት በተለያዩ ጊዜያት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን የሰጠ መሆኑን፤ ነገር ግን ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተደጋጋሚ ጊዜ የዕለቱ ዜና ሲተላለፍ በቀን ቢያንስ አንድ ጊዜ በምልክት ቋንቋ እንዲተላለፍ ጥረት የተደረገ ቢሆንም መስሪያ ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ጥረቱ ሳይሳካ መቅረቱ ግንዛቤ እንዲወሰድ እና ዜናዎችን በብሬል ማተምና መሰራጨት ተገቢ ቢሆንም ያለመተግበሩ፤ እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ የተነሱ ጉዳዩች ተግባራዊ እንዲሆኑ በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያለመታከት ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በመሥራት የሚዲያ ተቋማት ማህበራዊ ኃላፊነታቸው በተገቢው መንገድ እንዲወጡ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

122. በመሆኑም የአካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የጉዳት አልባዎች በዕለቱና በወቅቱ የሚተላለፉ መረጃዎች በበቂ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆናቸው፤ አካል ጉዳተኞች ከወቅታዊ መረጃ እንዲርቁ ያደረጋቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን፣ ፊልሞችንና ቲያትሮችን፣ ባህላዊ ክንውኖችን እንዲሁም ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በመዝናኛ፣ በዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና በስፖርት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል ተገቢ እርምጃ ባለመወሰዱ አካል ጉዳተኞች ስለሀገራቸውና ስለዓለም አቀፍ ጉዳዮች ወቅታዊ መረጃ እንዳያገኙና አካላቸውንና መንፈሳቸውን በማዝናናት ብቁ አምራች ዜጎች እንዳይሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ  አካል ጉዳተኞች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ

123. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ አካል ጉዳተኞችና የቤተሰቦቻቸውን ቁጥር እንዲያድግ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

124. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አካል ጉዳተኞች በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስፈላጊ ሙያዊና የቴክኒክ ድጋፍ ፍላጎት ጥናት በመተግበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም የልማቱ ተጠቃሚ ቤተሰቦች ቁጥር የማሣደግ ሥራ  እንዲሰራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ የማድረግ ስራ አለመሰራቱን ለማወቅ ተችላል፡፡

125. የኦሮሚያ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮና አዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከ2006-2008 በጀት ዓመት በአቅም ውስንነት /የሰው ኃይል እና የግብዓት እጥረት/ ምክንያት አካል ጉደተኞችን በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ላይ በቂ ስራ አለመሰራታቸውን ገልፀው ለወደፊት አካል ጉዳተኞችን በሴፍቲኔት ፕሮግራም ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

126. ስለሁኔታው የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት መጠቀም የሚገባቸው አካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቻቸው በኘሮግራሙ ታቅፈው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ የሚገኝ ቢሆንም በቂ አለመሆኑ እና በቅርቡ ተግባራዊ በሚደረገው የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔትም አካል ጉዳተኞች የኘሮግራሙ ተጠቃሚ  እንዲሆኑ ዝግጅት መደረጉን ገልፀዋል፡፡

127. በመሆኑም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰቡ አካል የሆኑት አካል ጉዳተኞች በሴፍቲኔት ታቅፈው በመደራጀት እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን

መደገፍና መርዳት እንዲችሉ እንዲሁም የሴፍቲኔት ፕሮግራም የታቀፉ የቤተሰብ ቁጥሮችን በማሳደግ ከድህነት ወለል በታች የሆኑ አካል ጉዳተኞችን በመርዳት ወደ የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲመጡ ባለመሠራቱ አካል ጉዳተኛ ዜጎች የእኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል ጉዳተኞችን ኮንቬንሽን፣ በሥራ ስምሪት አዋጅና በሌሎች አዋጆች ማስተዋወቃቸውን በተመለከተ

128. ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ በአካል ጉዳተኞች ኮንቬንሽን፣ በአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና በሌሎች አዋጆች፣ ደንቦች አካል ጉዳተኞችን መብቶች በሚያስከብሩ ጉዳዮች ሁሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ሊሰራ እና በህብረተሰቡ ስለአካል ጉዳተኞች ያለውን ግንዛቤ ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተጠቃሚነታቸውን እንዲረጋገጥ በቅንጅት ሊሰራና በግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች የመጡትን ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በማዘጋጀት የመጣውንም ለውጥ ሊገመግሙ ይገባል፡፡

129. በኦዲት ወቅት ጉዳዩን አስመለክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የማስረጃ ክለሳዎች መሠረት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች ላይ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በዕቅድ አየያዙ ተግባራዊ ሲያደርግ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጡት የግንዘቤ ማስጨበጫዎች በተለይም የአካል ጉዳተኞችን እኩል ዕድል ተጠቃሚነትና የስራ ስምሪት መብታቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስለመሰጠቱ ሲገመገም የሚከተሉት ጉዳዮች ታይተዋል፡፡

- አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የሚሰጠው ግንዛቤና ስልጠና በማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ውስጥ በጥቅል የተቀመጡ በመሆናቸው ስለአካል ጉዳተኞች የተሰጡ የግንዛቤ ማስጫበጫዎች፣ የተሰጠበት ርዕስ፣ ምን ያህል አካል ጉዳተኞች እንደተሳተፉ በዝርዝር የሚያሳይ አለመሆኑ፣

- የሚሰጡ ድጋፎች በጥቅል የሚቀመጡ በመሆኑ ለየትኛው ጉዳይ ምን አይነት ድጋፍ እንደተሰጠ እና ድጋፉ ማንን ተጠቃሚ እንዳደረገ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በሚሰጡ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ያስገኙት ውጤት ውጤታማነት ከግቡ አንፃር እየተመዘነ የማይቀመጥ መሆኑ፣
- በሴክተሩ የሚከናወኑ የግንዛቤና የስልጠና ሥራዎችን ስታንዳርድ አውጥቶ ያስገኙትን ውጤት እየመዘኑ የማህበራዊ ችግሮችን በመከላከልና ህብረተሰቡን በማሣተፍ የተፈለገውን ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ ተከታታይ ስራዎች አለመስራታቸው፣
- የማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከል የሚያሰችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫና ስልጠና ለመስጠት የሚታቀደው ከሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ጋር በጅምላ መሆኑ እና አፈፃፀማቸውን ለይተው በቁጥር ቢገልጹም ለአካል ጉዳተኞች ተለይቶ ስለመታቀዱ በዕቅድ ሪፖርቶች ላይ የማያሳዩ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

130. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ በክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት፣ በፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ በአካል ጉዳተኞች የተሃድሶ ማዕከላት የሥራ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቆች በሰጡት መልስ መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞችን በህብረተሰቡ ውስጥ ማካተትና ህብረተሰቡ ስለአካል ጉዳተኞች ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ መመሪያዎችን አውጥቶ ከመላከ ውጪ በተደራጀ መልኩ ስልጠናዎችን በመምራት፣ የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት እና በአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት ላይ ከፌደራል ሚኒስቴር መ/ቤቱና በተዋረድ እስከ ወረዳ ካሉት አስፈፃሚ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር በሚፈለገው ደረጃ አለመሥራታቸው፤

- ስለአካል ጉዳተኞች ለመንግስት ለከፍተኛ የስራ አመራሮች፣ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች ስልጠና የማይሰጡ በመሆኑ በአስፈፃሚ አካላት ላይ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩ፤
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኮንቬንሽኑንና አዋጁን ለማስፈፀም በበቂ መጠን ውጤት ተኮር (focused) የሆነ ለውጥ የሚያመጣ ግንዛቤ በመፍጠር፣ በማስተባበርና ሥልጠና በመስጠት እንዲሁም ተፈፃሚነቱን በመከታተል በማይተገብሩት ላይ

አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ በሚያስችል መልኩ ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑን፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች በዓላት በሚከበርበት ወቅት እና በተወሰነ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ቢሰራም በቂና ተደራሽ አለመሆኑ እንዲሁም በክልል ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ እጥረት መኖሩ የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎችም በተቀናጀና በተጠናከረ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ያልተሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

131. ስለጉዳዩ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ ትምህርታዊ ጽሁፎችን በማዘጋጀት ለአስፈፃሚና ለፈጻሚ ባለሙያዎች በተለያዩ ጊዜያት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን እየሰጠ መሆኑ፣ ስልጠናዎች የሚሰጡትም በአብዛኛው ጊዜ በባለሙያዎች መሆናቸው፣ ስልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ ስራዎች ለፌደራል መ/ቤት ለከፍተኛ አመራሮችና ኃላፊዎች ስልጠናዎች በዕቅድ ተይዘው የተፈጸሙና ስለአፈጻጸማቸው በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የቀረበ መሆኑ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጡ ስልጠናዎች በእቅድ የሚመሩ መሆናቸው እንዲሁም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስልጠና እንዲሰጥ ሲጠየቅም በማንኛውም ቦታና ጊዜ በመገኘት ስልጠና የሚሰጥ መሆኑ እንዲሁም ሁሉም ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት ፍትሃዊ እንዲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ይበልጥ ተቀናጅቶ የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

132. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡት የግንዛቤ ማስጨበጫዎች በአብዛኛው የማህበራዊ ደህንነት ችግሮችን በጥቅል የሚቀርቡበት እንጂ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ እየተለየና (Focused) በሆነ መልኩ ያልቀረቡና በግንዛቤ ማስጨበጫው ምክንያት የመጣውን ውጤት ለመለካት የሚያስችል የአፈፃፀም መለኪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያላዘጋጀና የመጣውን ለውጥ ያልተገመገመ በመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ አጥጋቢ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

133. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዩ ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት

መልስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተፈለገው መጠን በቅንጅትና በትብብር የማይሰራ መሆኑ፤ በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ማስፈፀምን በተመለከተ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንደሚመለከታቸው እያወቁ ለመስራት ፍቃደኛ አለመሆናቸው፤ በየመስሪያ ቤቱ ፎካል ፐርሰን እንዲመድቡ የተደረገ ቢሆንም እንደተጨማሪ ስራ ስለሚሰጣቸው በአግባቡ የማይሰሩ መሆኑ እና የተመደበው ሰራተኛ ሲለቅ ሌላ የማይወከል መሆኑ ገልፀዋል፡፡

134. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኞች በህብረተሰቡ ውስጥ እኩል ዕድል ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ በአካል ጉዳተኞች ኮንቬንሽን፣ በስራ ስምሪት አዋጅና በሌሎች አዋጆችና ደንቦችን ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ባለድርሻ አካላትን በሚፈለገው ደረጃ ያሳተፈና ውጤታማና ሰፊ የግንዛቤ መስጨበጫ ስራዎችን ተጠናክረው አለመሰራቱና የሚሰጡትም የግንዛቤ ማስጨበጫዎች የሚለኩበት መስፈርት ያልተዘጋጀና ስራ ላይ ያልዋለ በመሆኑ አካል ጉዳተኞች በህብረተሰቡ ውስጥ ሊያገኙ የሚገባቸውን የዕኩል ዕድል ተጠቃሚነት ውጤታማ እንዳይሆን ሊያደረግ ይችላል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራት ላይ የሚደረግ ክትትል በተመለከተ

135. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና ማህበራት በተመዘገቡበት አላማ እና ክልል ላይ ሥራዎችን ስለመስራታቸው እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጡት ድጋፎች ተደራሽ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ እና በዚህ መሰረት አፈጻጸማቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

136. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት በአካል ጉዳተኞች በሁሉም በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተስብ ክፍሎችን በተለይም አካል ጉዳተኞን ተጠቃሚ ለማደረግ ከፌድራል በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ፈቃድ የወሰዱ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ፈቃድ በወሰዱባቸው አላማዎች እና ክልሎች በመገኘት ለአካል

ጉዳተኞችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ በመሳሰሉት አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ የተሰማሩ ስለመሆናቸው በበቂ መጠን ቁጥጥር፤ ክትትል እና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑ፣ አፈፃፀማቸውም በተከታታይ በመገምገም ግብረ መልስ የሚሰጥ አለመሆኑ፣ እንዲሁም እያስገኙ ስላሉት ኢኮኖሚያዊ ሆነ ማህበራዊ ጥቅሞች መረጃዎች ያልተደራጁ መሆኑ ታውቋል፡፡

137. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የተሃድሶ ማዕከላት በተገኙ ማስረጃዎች መሰረት በፌዴራል እና በክልሎች በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተው የማይሰሩ መሆኑ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በራሳቸው ፈቃድ በፈለጉት ክልልና አገልግሎት ላይ እየሰሩ መሆኑ ለምሳሌ፡-

- ቮለንተር አክሽን ፎር ኮሚኒቲ ትራንሰፎሜሽን ሰርቪስ ማህበር ከፌድራል በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ኤጀንሲ ምዝገባ ፍቃድ ቁጥር 3247 ተመዝግቦ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተስብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማደረግ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት ምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማ አሰተዳደር እና በደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት በሀዋሳ ከተማ መሰተዳደር እና በሃድያ ዞን፣ ሾኒ ከተማ ለመስራት እውቅና የተሰጠው ቢሆንም በሀዋሳ ከተማ አሰተዳደር ብቻ እየሠራ በመሆኑ፣
- ጃይንት ብላይንድ ኤንድ ፐርስን ዊዝ ዲሴቢሊቲ እና ሪሀብሊቴሽን ማህበር ከፌድራል በጎ አድረጎት ድረጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በምዝገባ ቁጥር 3200 ተመዝግቦ አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ለማደረግ በደቡብ ብሄር ብሄር ሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ሀድያ፣ ጌድዮ፣ ጉራጌ እና ገመጎፋ ዞኖች ለመስራት እውቅና ተሰጥቶት በሀዋሳ ከተማ ብቻ እየሠራ በመሆኑ፣
- ስርቫይቭ ሪከቨሪ ኤንድ ሪሀብልቴሽን ኦርጋናይዜሽን የበጎ አድራጎት ድርጅት ከፌድራል በጎ አድረጎት ድረጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በመዝገብ ፍቃድ ቁጥር 3229 ተመዝግቦ አካል ጉዳተኞችን በሁሉም አገልግሎቶች ተጠቀሚ ለማደረግ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት እና በአዲስ አበባ ከተማ

መሰተዳደር ለመስራት እውቅና የተሰጠው ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር የካ እና አራዳ ክፍለ ከተሞች ብቻ የሚሠራ በመሆኑ፣ ታውቋል፡፡

138. ስለጉዳዩ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ይህ ችግር የመጣው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ባለመሰራቱ መሆኑን ጠቅሰው በሀገሪቱ ከስምንት መቶ የሚሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ አራት መቶ የሚሆኑ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚሰሩ ሲሆኑ ስምንቱ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ውል ተፈራረመው የሚሰሩ ቢሆንም ሌሎች ግን ከክልሎች ጋር እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

139. በመሆኑም በአካል ጉዳተኞች ላይ ለመስራት ፈቃድ ወስደው የገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በትክክል ስለመፈፀማቸው የተቀናጀ ክትትልና ቁጥጥር በለመደረጉ ምክንያት መንግስት ሊደርስባቸው በማይችል ቦታዎች ላይ በመግባት ለአካል ጉዳተኞች ሊሰጡ የሚገቡ አገልግሎቶች እንዲሰጡ የሚጠብቅባቸውን ሃላፊነት ባለመወጣት አካል ጉዳተኞችም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በማድረግ እንዲሁም በክልል፣ በዞንና በወረዳ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች በጐ አድራጐት ድርጅቶቹ ለአካል ጉዳተኞች ሊሰጡ የሚገባውን አገልግሎት በማግኝት ችግሮቻቸው እንዳይቀረፉ፣ አምራችና ውጤታማ ዜጋ ለመሆን እንዳይችሉ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ለአካል ጉዳተኞች መረጃዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የመረጃ በዳታቤዝ ያደራጀ መሆኑን በተመለከተ

140. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ዝርዝር ድጋፍ፣ ስለተቀመጡ መብቶችና አስገዳጅ ህጎች፣ ስለአካል ጉዳት አይነቶችና ተጠቂዎች በፆታና በዕድሜ በመለየት ወዘተ መረጃዎችን በማደራጀት በዳታቤዝ ሊይዝ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጄንሲ ጋር በመሆን በህዝብ ቆጠራ ወቅት ስለአካል ጉዳተኞች ሙሉ መረጃ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃዎች እንዲያዙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

141. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ዝርዝር ድጋፍ፣ ስለተቀመጡ መብቶችና አስገዳጅ ህጎች፣ ስለአካል ጉዳት አይነቶችና ተጠቂዎች በፆታና

በዕድሜ በመለየት ወዘተ መረጃዎችን በማደራጀት በዳታቤዝ ሊይዝ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጋር በመሆን በህዝብ ቆጠራ ወቅት ስለአካል ጉዳተኞች ሙሉ መረጃ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃዎች እንዲያዙ ድጋፍና ክትትል በበቂ ሁኔታ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

142. ስለጉዳዩ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ መሰጡት መልስ አጠቃላይ እንደ አገር ሊደራጁ የሚገባቸው መረጃዎች ማለትም የቤትና የህዝብ ቆጠራን በተመለከተ መረጃዎች የመቁጠርና የማደራጀት ስራ የማዕካላዊ ስታትስቲክስ እንጂ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የስራ ድርሻ አለመሆኑ፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሁሉንም የአካል ጉዳተኞች የተሟላ መረጃ አደራጅቶ ለመያዝ የሚችለው የህዝብና ቤት ቆጠራ ሲካሔድ አካል ጉዳተኞች በተገቢው መንገድ መቆጠር እንዲችሉ ለማድረግ ከተቋሙ ጋር በመተባበርና በመቀናጀት የአካል ጉዳት አይነትና መገለጫዎቹን በዝርዝር በማዘጋጀት በ2010 በሚደረገው ህዝብና ቤት ቆጠራ ትኩረት ተሰቶት ስራው እንዲሰራ የራሱን ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

143. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ዝርዝር ድጋፍ፣ ስለተቀመጡ መብቶችና አስገዳጅ ህጎች፣ ስለአካል ጉዳት አይነቶችና ተጠቂዎች በፆታና በዕድሜ በመለየት ወዘተ መረጃዎችን በማደራጀት በዳታቤዝ ሊይዝ ባለማድረጋቸው መረጃዎቹ በአግባቡ እንዳይሰራጭ፣ ተደራሽ እንዳይሆን እና ለተለያዩ ጥናቶች መነሻ እንዳይሆን ከማድረግ ባሻገር በዘርፉ ያለውን ክፍተቶች ተረድቶ እርምጃ ለመውሰድ ለአስፈፃሚው አካል ግብዓት እንዳይሆን በማድረግ በህግ የተቀመጡ መብቶች ተደራሽነታቸው እንዳይረጋገጥ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው በአካል ጉዳተኞች የተደረገ ክትትልና ድጋፍ አፈፃፀምን በተመለከተ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት፣ በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ፌዴሬሽን፣ በክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና በአካል ጉዳተኞች ተሃድሶ ማዕከላት የታዩት ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሣቦች ላይ ተደርሷል፡፡

144. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማስፈፀም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመራ ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም፣ የኮሚቴው አባል መ/ቤቶች ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ መሰረት በሚመለከታቸው ጉዳይ ለመፈፀም ኃላፊነት የወሰዱ ቢሆንም ይህን ስለመተግበራቸው በተደራጅ ሁኔታ በዓመታዊ ዕቅዳቸው አካትተው ማቀዳቸውን እንዲሁም በዕቅዱ መሰረት ስለመተግበራቸው የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በማድረግ በቅንጅት ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው ክትትልና ድጋፍ ስራ በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑ፣ እንዲሁም ይህን በማይፈፅሙ ተቋሚት የሚጠየቁበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

145. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዘጠኝ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ በጋራ በመሥራት የአካል ጉዳተኞች እኩል እድል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ሠነድ የተፈራረሙ ቢሆንም በሰነዱ መሰረት ለመፈፀም የጋራ ዕቅድ በማውጣት እና በመተግበር አፈፃፀሙን በመገምገም ጥልቀት ያለው ተግባር እየተከናወነ አለመሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደኮሚቴ ሰብሳቢነቱ ቋሚ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት በመወያየት አባል መ/ቤቶች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ድጋፍና ክትትል የማያደርግ መሆኑ፤
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ኮንቬንሽኑን መሰረት አድርገው በአፈፃፀሙ ላይ በጋራ የማይገመግሙ መሆኑን፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኮሚቴውን ከሚቋቋም በዘለለ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በኮንቬንሽኑ አፈፃፀም ዙሪያ ሥራዎችን ሠርተው በየሩብ ዓመቱ ወይም ዓመታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ የሪፖርት ግብረ መልስ በመስጠት ተጠያቂነት እንዲጠናከር ያላደረገ መሆኑ፤ በኮሚቴው አባላት ውስጥ በድርጊት መርሃግብሩ መሰረት በመተግበር ትብብር የማያደርገውን የኮሚቴ አባል መ/ቤቶችን በመለየት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ /በማሳወቅ/ የበኩሉን ኃላፊነት አለመወጣቱን፤
- በተመሳሳይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን አተገባበር ለመከታተል እንዲቻል የክልል ቢሮዎችና በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ ክልላዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ በተጨማሪም በክልል ይህን ጉዳይ የሚከታተል አካል በስራ ላይ ያልተገኙ መሆኑ፤

144. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር  የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የአካል ጉዳተኞችን በኮንቬንሽኑ የተቀመጡ መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ ለማድረግና በማህበራዊ ዘርፍ የተቀመጡ መብቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ያላወጣ መሆኑ፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላትም በኃላፊነታቸው መሰረት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያወጡ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤

145. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በጁን በ2010 ያፀደቀችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን፣ ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለመተግበርና ለማስፈፀም በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንዲደራጅ ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና በማስፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን በቂ ስራ እንዳልተሰራ መሆኑ፤

146. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት የወጣው አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና የአዋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት በማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች አካል ጉዳተኞች በቅጥር ምልመላ፣

ጊዜያዊና ቋሚ ቅጥርን፣ በቋሚ ስራ ላይ መቀጠልን፣ የሙያ እድገትና፤እኩል ዋጋ ላለው ስራ እኩል ዕድሎች ሆነ እኩል ክፍያ የማግኘት፣ ለቅሬታዎች የመፍትሄ ምላሽ ማግኘት፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የስራ ሁኔታዎች መኖሩን፣ ማንኛውም ረዳት ለሚያስፈልገው አካል ጉዳተኛ ሥራውን ለመሥራት ወይም ሥልጠናውን ለመከታተል እንዲችል ረዳት የተመደበለት መሆኑን እና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ከጉዳት አልባዎች ጋር በእኩል ደረጃ ምቹ የስራ ሁኔታ የማግኘት መብት ስለመከበራቸው የሚረጋገጥበት እና አፈፃፀሙንም የሚገመገምበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

147. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር መሰረት ከማህበራት፣ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርና ከክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ አካል ጉዳተኞች ጥቃት ሲደርስባቸው፣ ፍትህ እንዲያገኙ ጥቃት ያደረሰውን አካል ተከታትለው ወደ ህግ በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስችል ምቹ ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም ባለው ሥርዓት መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በግልም ሆነ በቅንጅት ጉዳት ለደረሰባቸው አካል ጉዳተኞች ድጋፍ ስለማድረጉ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሌለ መሆኑ፤

- አካል ጉዳተኞች በስራ ላይ መድልዎ ደርሶባቸው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲያመለክቱ የሥራ ሥምሪት አዋጅ ቁጥር 568/2002ን ጠቅሰው የድጋፍ ደብዳቤ ከመጻፍ ባለፈ በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት ድጋፍና ክትትል የሚያደርጉ አለመሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች በደል ወይም ጥቃት ደርሶባቸው ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲመጡ ወደ አካል ጉዳተኞች ማህበር እንዲሄዱ የሚያደረጉ መሆኑ፤
- አካል ጉዳተኞች በቅጥር፣ በምልመላ እንዲሁም ቁልፍ ቦታዎችን በኃላፊነት ለመያዝ በሚያደረጉት እንቅስቃሴ ውስጥ መድሎ ደረሶባቸው ሲያመለክቱ ጉዳያቸው በህግ አግባብ ታይቶ የሚሰጡ ውሳኔዎች በተለይም መስማት ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች በምልክት ቋንቋ እንዲረዱ የማይደረግ መሆኑ፤

148. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕጋጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል

ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችለው መልኩ ነቅሶ በማውጣት የሚመለከታቸው አካላትን እና አካል ጉዳተኞች ማህበራትን አወያይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችል ሥራዎችን ያልተከናወነ መሆኑ፤

149. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ በገኘው የገንዘብና የሙያ ድጋፍ፣ ከተባበሩት መንግስታት የጤና ድርጅት፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ተሀድሶ ሠራተኞችን ለማሰልጠንና ለመደገፍ የሚያስችል ብሔራዊ አካላዊ ተሃድሶ ስትራቴጂ በ2003 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም ተግባራዊ ለማድረግ በተፈለገው መጠን ስራ ያልተሰራና በስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፤

150. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ፣ ከክልል አካላት ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በስራ ላይ ከሚገኙ ኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት የኦርቶፔዲክ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን ያልተቀረፀ እና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

- የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ ስር የሚገኘው የብሄራዊ ተሀድሶ ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በማስተባበርና በመቀናጀት በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስ ቴክኒሽኖች፣ ኦክዩፔሽናል ቴራፒስቶችና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት በጠቅላላ ስልጠና፣ ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያና የተግባር ስልጠና እንዲያገኙና በስራ ላይ እንዲሰማሩ ጥረት ቢደረግም በሀገሪቱ ያለውን የባለሞያ ፍላጎት ለመሙላት የሚያስችል አለመሆኑ፤
- በተጨማሪም በሀገሪቱ ያሉ 16 ማዕከላት የባለሞያ ችግር ያለባቸው መሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲሰለጥኑ የሚደረጉ ባለሞያዎችን ቁጥር በማሳደግ ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችል በቂ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፤

- እንዲሁም በኦክዬፔሽናል ቴራፒስት የሰለጠነ ሙያተኛ የሌለ መሆኑና ችግሩን ለመፍታት ከማዕከላት እና ከክልል ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት ውጤታማ ስራ እየተሰራ አለመሆኑ፤
- እንዲሁም አንዳንድ ማዕከላት ምርቶችና ግብዓቶች የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ የሚያወጣውን ስታንዳርድ የሚጠቀሙ ቢሆንም መሳሪያዎቹና በመሳሪያዎቹ የሚመረቱ ምርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ስለመሆኑ በየጊዜው የሚፈተሽበት አግባብ /ስታንዳርድ/ የሌለ መሆኑ፤

151. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት የተቋቋመባቸው ክልሎች ሁለቱም ከተማ መስተዳድር ጨምሮ በ5 ክልሎች ሲሆን ማዕከላቱ የሚገኙት በከተማ አካባቢ ላይ በመሆኑ በገጠር የሚኖሩ ዜጎች አገልግሎቱ ተደራሽ አለመሆኑ፤ እንዲሁም ባለው የመንግስት ጤና መዋቅር ማለትም (ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች) ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች(rehabilitation center) በማደራጀትና የሪፈራል (የቅብብሎሽ) ስርዓቶችን በመዘርጋት ተደራሽ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑ፤

152. እንዲሁም የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት፣ ግብዓቶች እና ድጋፎች እንደ የሰው ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ፣ የእንቅስቃሴ መርጃዎች እና የፊዚዮቴራፒ አገልግሎቶችን ውጤታማና ተደራሽ የሆነ የምርትና ስርጭት ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
    - በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ 16 አካላዊ የተሃድሶ ማዕከላት በከተሞች አካባቢ ብቻ የሚገኙ በመሆናቸው በሀገሪቷ ገጠራማ ክፍል የሚኖሩ የአካል ጉዳተኞች ማዕከላቱ ለሚሰጡት አገልግሎት ተደራሽ አለመሆናቸው እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚተገበር ዕቅድ የሌለ መሆኑ፣
    - የተሃድሶ ማዕከላትን ለማስፋፋት ባለው የመንግስት ስርዓትና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመጠቀም ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ እና የተጠናከረ የሪፈራል ቅብብሎሽ ስርዓት በመዘርጋት ችግሮችን ለመቅረፍ ያልቻለ መሆኑ፤
    - በሀገሪቱ ያሉ 16 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ማዕከላት ባላቸው ውስን አቅም ሠው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፎችን በበቂ ሁኔታ የማምረት እና የመጠገን ብቃታቸው ካለው ፍላጎት ጋር ሲነፃፀር እጅግ አነስተኛ መሆኑ፤

- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሃገር ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ወጭ ቆጣቢና ዘላቂ አገልግሎት የሚሰጡ የሠው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፎችን (ኮምፖነንቶችን)፣ ለእንቅስቃሴ አጋዥ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ከብረታብረት ኢንጂነሪንግ ጋር የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሰነድ ቢፈራረምም ወደ ሥራ በመግባት ምርትና ስርጭት ስትራቴጂ ቀርጾ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆኑ፡፡
- በአዲስ አበባ የሚገኘው የአዲስ አበባ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከል በሠራተኛና ማህበራዊ ጉደይ ሚኒስቴር በቦርድ ሰብሳቢነት የሚመራ ሲሆን የማምረቻ ማዕከሉ ህጋዊ አቋም የሌለው ማለትም መንግሥታዊም ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ መሆኑን የሚገልፅ አደረጃጀት የሌለው በመሆኑ፣ እና የማዕከሉ ቋሚ የሆነ ሥራ አስኪያጅ የሌለው በመሆኑ ከማዕከሉ ከተቋቋመ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ቢሆንም ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣት አለመቻሉ፤

153. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤና አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችን የሚቀርብ ስለመሆኑ በእስትራቴጂክ ሆነ በአመታዊ ዕቅድ በማቀድ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

   - ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች እንደ ጉዳታቸው ዓይነት ተስማሚ በሆነ መልኩ ማለትም መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/ በማዘጋጀት በአካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤናና የግንዛቤ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግና በሽታውን

ለመከላከል ስለሚያስችሉ ሁኔታዎች፣ የመተላለፊያ መንገዶችና የመከላከያ ዘዴዎች ተዘጋጅቶ እንዲገነዘቡት የሚያስችል ሁኔታ እየተሠራ ስለመሆኑ በዕቅድ ይዘው ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶን በተመለከተ ተቀናጅቶ የመስራት ክፍተቶች መኖራቸው፤

154. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ የድርጊት መርሀ ግብሩ የተገለፀው የብሬል ትምህርትን የአማራጭ የፅሑፍና እያደጉ የሚሄዱ አማራጭ የመገናኛ ስልቶች፣ ዘዴዎችና ቅርፃችን የማስተዋወቂያ ገለፃና የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እንዲሁም የአቻ ለአቻ እገዛ እና የሥራ ላይ አስተምህሮትን ተግባራዊ እንዲሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ በመሥራት እንዲመቻችላቸው ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፤

155. በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሐ/ ላይ አካል ጉዳተኞች እንደጉዳታቸው አይነት መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/፣ ለሕፃናትና ለሴት አካል ጉዳተኞች ትምህርትን ይበልጥ ተስማሚነት ባለው ቋንቋ፣ የግንኙነት ዓይነትና ዘዴ አማካኝነት የቀለም ትምህርትንና ማህበራዊ እድገትን ከፍ በሚያደርግ ሁኔታ ስለመሰጠቱ በበቂ ሁኔታ ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፤

156. እንዲሁም ማየትና መስማት በጣምራ ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሚያደርግ ካሪኩለም ያልተቀረፀ መሆኑ፤ አካል ጉዳተኞች ወደ ትምህርት በመግባት መማር እንዲችሉ በአስገዳጅ ሁኔታ ወደ ትምህርት ገበታ መምጣት የሚችሉበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ፣ በተጨማሪም የመጣውን የለውጥ ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን በመያዝ የድጋፍና የክትትል ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑ፤

157. በተጨማሪም አካል ጉዳተኞች የሚማሩበት ትምህርት ቤት በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት ምቹ የመማሪያ ህንፃዎችና ክፍሎች፣ የመዝናኛና መፀዳጃ ስፍራዎች፣ ቤተ መፃሕፍት፣ የውሃ መጠጫ ቦታዎች፣ ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ--ተደራሽ አለመሆናቸው፤ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር አካል ጉዳተኞችን በትምህርት አሰጣጥ ተደራሽነት ላይ በቅንጅት ለመስራት የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሠነድ የተፈራረሙ ቢሆንም በሰነዱ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን በአመታዊ በዕቅድ ቢያካትቱም በዕቅዳቸው መሠረት ያልሰሩ መሆኑ፤

158. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. በተቀመጠው መሰረት የሚገነቡ ህንጻዎች ከዲዛይን ጀምሮ፣ በትግበራ ላይ ክትትል በማድረግ እና በርክክብ ወቅት አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ባደረገ መልኩ እየተገነቡ ስለመሆኑ እና ተግባራዊ ስለመደረጉ ቅንጅታዊ የክትትል ስራ የሚከናወንበት ስርዓት ተዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣

- በህንፃ አዋጁና መመሪያው ላይ በሚፈለገው ደረጃ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎች በሰፊውና በበቂ ሁኔታ አለመሰራታቸው፣
- በግንባታ ዙሪያ የተሰማሩ ባለሞያዎች ሁሉም በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መገንባታቸውን ለመከታተልና አዋጁንም ለማስፈፀም የተዘረጋ ስርዓት አለመኖሩ፣ ትኩረት አለመሰጠቱ እና በአዋጁ መሰረት ላልገነቡት ባለቤቶችም ሆነ ለማይተገብሩ ባለሞያዎች ተጠያቂ በማድረግ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ የማያስደርግ መሆኑ፤

159. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽን አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሰረት ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ድርጅቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብተው ተደራሽ ስለመሆናቸው

የሚከታተልበት ሥርዓት ያልዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል በቂና ውጤት የሚያመጣ የግንዛቤ ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ፤

- በፌዴራልም ሆነ በክልሎች በግልና በመንግሥት የተሠሩ ለሕዝብ ክፍት የሆኑ የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ለምሳሌ ባንክ፣ የሕዝብ ማህበራዊ ጉዳዮች መስጫ ቦታዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የማምለኪያ ቦታዎች---ወዘተ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አለመሆናቸው እና ይህን ለማስተካከል ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተቋማቱ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆናቸውን በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮና ተቀናጅቶ የማይሰራ መሆኑ፣

160. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችና መገልገያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሆነ መልኩ መዘጋጀታቸው እና አገልግሎት መስጠታቸው ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ እንዲሆን እንዲሁም ተደራሽ ባልሆኑት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ በቂ የሆነ ድጋፍና ክትትል አለመኖሩ፤
161. የትራንስፖርት ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተፈራረሙት የመግባቢያ ሠነድ መሠረት አካል ጉዳተኞችን በትራንስፖርት መሠረተ ልማት አገልግሎትና አቅርቦት ላይ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ ዕቅድ በማቀድ ተደራሽ እንዲሆኑ የተሰሩ ስራዎች አለመኖራቸው፤
162. የትራንስፖርት ባለስልጣን የህዝብ ትራንስፖርት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የደረጃ መስፈርት ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም የደረጃ መስፈርቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው መዘጋጀታቸው እንደ ደረጃ መስጫ መስፈርት ያልተካተተ መሆኑ እንዲሁም አብዛኛው የትራንስፖርት አቅርቦቶች አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ አለመሆናቸውን፤
163. የአዲስ አበባ ቀላል የከተማ ባቡር አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች በሁሉም ተርሚናሎች አሳንሰር ለመግጠሚያ የሚውሉ ግንባታዎች የተዘጋጁ ቢሆኑም እስከ

ጥር 2009 ዓ.ም. ድረስ አሳንሰሮቹ ተገጥመው አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ አለመሆናቸው፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር ውስጥ የቃልና የፅሁፍ መልክት የሚተላለፍ ሲሆን የፅሁፍ መልዕክቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ የሚፃፍ በመሆኑ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆን ላይ ክፍተት መኖሩ፣

164. በተጨማሪም በሀገር ደረጃ የሚገኙ የሀገር አቋራጭ መናኸሪያ ቦታዎች ከትኬት መቁረጫ ጀምሮ አገልግሎት የሚሰጡ የሀገር አቋራጭ የትራንስፖርት ስምሪት ቦታዎችና እና አውቶቡሶቹ ለአካል ጉዳተኞች በተሟላ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆናቸውን፣

165. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር ጉዳዩን አስመልክቶ የመግባቢያ ሠነድ የተፈራረመ ሲሆን በዚሁ መሠረት ዌብ ሳይቶችን የሚያለማ ሲሆን የለማው ዌብ ሳይት ለአካል ጉዳተኞች ስለመድረሱ ወይም አገልግሎት እየሰጠ ስለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን የማይከታተል መሆኑ፣

166. እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን፣ የእንቅስቃሴ መረጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ መገልገያዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የምርምርና የልማት ስራዎችን እንዲካሄዱ ድጋፍ እና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም የለሙ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ የማስተባበር፣ የማቀናጀት እና የመደገፍ ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑ፤

167. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞችን ከጉዳት አልባ ዜጎች እኩል በሁሉም የሚዲያ አካላት በማካተት የተለያዩ መረጃዎች በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ አለመሆናቸው እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩን አስመልክቶ በቂ ድጋፍና ክትትል እንደማያደርግ መሆኑ፤

168. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግልና የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ፕሮግራሞች ቢሰሩም ለየትኛው አይነት የአካል ጉዳት ምን አይነት አገልግሎት (ፕሮግራም) እንዳላቸው ለምን ያህል የአየር ሰዓት እንደሚሰጡና

ያልተዳሰሱ አካባቢዮችን እንዲያካትቱ ስለመደረጉ እና ይህንም የሚገልፅ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲኖርና አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ እንዳላደረገ መሆኑ፤

169. በተጨማሪም ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እነማን እንደሆኑ ለየትኛው ችግር የት መሄድ እንዳለባቸው መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ የተቀረፁ አለመሆናቸው እና በሚዲያ  የሚነገሩ ማስታወቂያዎችም አካል ጉዳተኞች ሊረዱት በሚችል ቋንቋ በጉዳታቸው ዓይነት ተዘጋጅተው በመቅረብ ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችል የሚድያ ስርዓት የሌለ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህንን አስመልክቶ በሚድያ ተደራሽ መሆን እንዲችሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት  የድጋፍና ክትትል ስራዎች ያልተከናወነ መሆኑ፤

170. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኞች የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን፣ ፊልሞችንና ቲያትሮችንና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖችን በተመቻቸ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆኑ የክትትል ስራ አለመስራቱ እንዲሁም  አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በመዝናኛ፣ በዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና በስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተዘረጋ ሥርዓት እና የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩ፤

171. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አካል ጉዳተኞች በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስፈላጊ ሙያዊና የቴክኒክ ድጋፍ ፍላጎት ጥናት በመተግበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም የልማቱ ተጠቃሚ ቤተሰቦች ቁጥር የማሣደግ ሥራ  እንዲሰራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ የማድረግ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤

172. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች ላይ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በዕቅድ አየያዙ ተግባራዊ ሲያደርግ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጡት የግንዘቤ ማስጨበጫዎች በተለይም የአካል ጉዳተኞችን እኩል ዕድል ተጠቃሚነትና የስራ ስምሪት መብታቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስለመሰጠቱ ሲገመገም የሚከተሉት ጉዳዮች ታይተዋል፡፡

- አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የሚሰጠው ግንዛቤና ስልጠና በማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ውስጥ በጥቅል

የተቀመጡ በመሆናቸው ስለአካል ጉዳተኞች የተሰጡ የግንዛቤ ማስጫበጫዎች፣ የተሰጠበት ርዕስ፣ ምን ያህል አካል ጉዳተኞች እንደተሳተፉ በዝርዝር የሚያሳይ አለመሆኑ፣

- የሚሰጡ ድጋፎች በጥቅል የሚቀመጡ በመሆኑ ለየትኛው ጉዳይ ምን አይነት ድጋፍ እንደተሰጠ እና ድጋፉ ማንን ተጠቃሚ እንዳደረገ ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- በሚሰጡ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ያስገኙት ውጤት ውጤታማነት ከግቡ አንፃር እየተመዘነ የማይቀመጥ መሆኑ፣

- በሴክተሩ የሚከናወኑ የግንዛቤና የስልጠና ሥራዎችን ስታንዳርድ አውጥቶ ያስገኙትን ውጤት እየመዘኑ የማህበራዊ ችግሮችን በመከላከልና ህብረተሰቡን በማሣተፍ  የተፈለገውን ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ ተከታታይ ስራዎች አለመስራታቸው፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኮንቬንሽኑንና አዋጁን ለማስፈፀም በበቂ መጠን ውጤት ተኮር (focused) የሆነ ለውጥ የሚያመጣ ግንዛቤ በመፍጠር፣ በማስተባበርና ሥልጠና በመስጠት እንዲሁም ተፈፃሚነቱን በመከታተል በማይተገብሩት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ በሚያስችል መልኩ ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑን፤

173. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት በአካል ጉዳተኞች በሁሉም በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተስብ ክፍሎችን በተለይም አካል ጉዳተኞን ተጠቃሚ ለማደረግ ከፌድራል በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ፈቃድ የወሰዱ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ፈቃድ በወሰዱባቸው አላማዎች እና ክልሎች በመገኘት ለአካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ በመሳሰሉት አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ የተሰማሩ ስለመሆናቸው በበቂ መጠን ቁጥጥር፤ ክትትል እና ድጋፍ  የማያደርግ መሆኑ፣  አፈፃፀማቸውም በተከታታይ በመገምገም ግብረ መልስ የሚሰጥ አለመሆኑ፣ እንዲሁም እያስገኙ ስላሉት ኢኮኖሚያዊ ሆነ ማህበራዊ ጥቅሞች መረጃዎች ያልተደራጁ መሆኑ፤

174. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ዝርዝር ድጋፍ፣ ስለተቀመጡ መብቶችና አስገዳጅ ህጎች፣ ስለአካል ጉዳት አይነቶችና ተጠቂዎች በፆታና በዕድሜ በመለየት ወዘተ መረጃዎችን በማደራጀት በዳታቤዝ ሊይዝ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትሰቲክስ ኤጀንሲ ጋር በመሆን በህዝብ ቆጠራ ወቅት ስለአካል ጉዳተኞች ሙሉ መረጃ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃዎች እንዲያዙ ድጋፍና ክትትል በበቂ ሁኔታ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለአካል ጉዳተኞች የሚያደርገው ድጋፍና ክትትል የአካል ጉዳተኞችን ችግር ከመቅረፍ አንፃር በሚፈለገው መጠን እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል በኦዲቱ ወቅት የታዩተን የአሠራር ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሣቦች ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት
## የማሻሻያ ሃሣቦች

175. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ለማስፈፀም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመራ ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም፣ የኮሚቴው አባል መ/ቤቶች ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ መሰረት በሚመለከታቸው ጉዳይ ለመፈፀም ኃላፊነት በወሰዱበት ተግባር ላይ በተደራጀ ሁኔታ በዓመታዊ ዕቅዳቸው አካትተው በማቀድ እንዲሁም በዕቅዱ መሰረት ስለመተግበራቸው የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በማድረግ በቅንጅት ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው ክትትልና ድጋፍ ስራ በአግባቡ ሊከናወን፣ እንዲሁም ይህን በማይፈፅሙ ተቋሚት የሚጠየቁበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባሪዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጋራ መግባቢያ ስምምነት ከነድ ከተፈራረማቸው ከዘጠኝ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ በጋራ በመሥራት የአካል ጉዳተኞች እኩል እድል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ናበሰነዱ መሰረት ለመፈፀም የጋራ ዕቅድ በማውጣት እና በመተግበር አፈፃፀሙን በመገምገም ጥልቀት ያለው ተግባር ሊያከናውን ይገባል፡፡

177. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሄራዊ አተገባበር ኮሚቴ ኃላፊነቱን ለመተግበር ቋሚ የመወያያ መድረኮችን  በማዘጋጀት በመወያየት አባል መ/ቤቶች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

178. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ኮንቬንሽኑን መሰረት አድርገው በዕቅድ አካትተው ስለመፈፀማቸው በጋራ ሊገመግሙ ይገባል፡፡

179. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የብሄራዊ አተገባበር ኮሚቴውን ከሚቋቋም በዘለለ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በኮንቬንሽኑ አፈፃፀም ዙሪያ ሥራዎችን ሠርተው በየሩብ ዓመቱ ወይም ዓመታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ የሪፖርት ግብረ መልስ በመስጠት ተጠያቂነት እንዲጠናከር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በኮሚቴው አባላት ውስጥ በድርጊት መርሃግብሩ መሰረት

በመተግበር ትብብር የማያደርገውን የኮሚቴ አባል መ/ቤቶችን በመለየት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ /በማሳወቅ/ የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡

180. በተመሳሳይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን አተገባበር ለመከታተል እንዲቻል የክልል ቢሮዎችና በአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ ክልላዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲቋቋምና በስራ ላይ እንዲሰማሩ ሊደግፍ፣ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

181. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የአካል ጉዳተኞችን በኮንቬንሽኑ የተቀመጡ መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ ለማድረግና በማህበራዊ ዘርፍ የተቀመጡ መብቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ሊያወጣ፣ እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላትም በኃላፊነታቸው መሰረት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያወጡ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

175. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በጁን በ2010 ያፀደቀችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን፣ ስለአካል ጉዳተኞች የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለመተግበርና ለማስፈፀም በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል አካል እንዲደራጅ ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል በማቅረብና በማስፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን በቂ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት የወጣው አዋጅ ቁጥር 568/2000 እና የአዋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ የሚከታተልበትና የሚገመገምበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

177. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር መሰረት ከማህበራት፣ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርና ከክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ አካል ጉዳተኞች ጥቃት ሲደርስባቸው፣ ፍትህ እንዲያገኙ ጥቃት ያደረሰውን አካል ተከታትለው ወደ ህግ በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስችል ምቹ ሥርዓት ያልተዘረጋ እንዲዘረጋ፣ እንዲሁም ባለው ሥርዓት

መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በግልም ሆነ በቅንጅት ጉዳት ለደረሰባቸው አካል ጉዳተኞች ድጋፍ ስለማድረጉ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡

178. አካል ጉዳተኞች በስራ ላይ መድልዎ ደርሶባቸው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲያመለክቱ የሥራ ሥምሪት አዋጅ ቁጥር 568/2002ን ጠቅሰው የድጋፍ ደብዳቤ ከመጻፍ ባለፈ በጉዳዩ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

179. አካል ጉዳተኞች በደል ወይም ጥቃት ደርሶባቸው ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲመጡ ወደ አካል ጉዳተኞች ማህበር ጋር በመተባበር ችግሩን ለመፍታት ሊሰሩ ይገባል፡፡

180. አካል ጉዳተኞች በቅጥር፣ በምልመላ እንዲሁም ቁልፍ ቦታዎችን በኃላፊነት ለመያዝ በሚያደረጉት እንቅስቃሴ ውስጥ መድሎ ደረሰባቸው ሲያመለክቱ ጉዳያቸው በህግ አግባብ ታይቶ የሚሰጡ ውሳኔዎች በተለይም መስማት ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች በምልክት ቋንቋ እንዲረዱ የሚደረግ ስለመሆኑ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችለው መልኩ ነቅሶ በማውጣት የሚመለከታቸው አካላትን እና አካል ጉዳተኞች ማህበራትን አወያይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችል ሥራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡

182. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተባበሩት መንግስታት የጤና ድርጅት፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ተሀድሶ ሠራተኞችን ለማሰልጠንና ለመደገፍ የሚያስችል ብሔራዊ አካላዊ ተሃድሶ ስትራቴጂ በ2003 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

183. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ፣ ከክልል አካላት ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በስራ ላይ ከሚገኙ ኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮትራፒ ማዕከላት የኦርቶፔዲክ አገልግሎት

አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

184. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ ስር የሚገኘው የብሄራዊ ተሀድሶ ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በማስተባበርና በመቀናጀት በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስ ቴክኒሽኖች፣ ኦክዬፔሽናል ቴራፒስቶችና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት በጠቅላላ ስልጠና፣ ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያና የተግባር ስልጠና እንዲያገኙና በስራ ላይ እንዲሰማሩ ጥረት በማድረግ በሀገሪቱ ያለውን የባለሞያ ፍላጎት ለመሙላት የባለሞያዎችን ቁጥር በማሳደግ ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችልድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

185. የተሃድሶ ማዕከላት የአካል ድጋፍ ምርቶችና ግብዓቶች ለማምረት የሚጠቀሙበት መሳሪያዎችና በመሳሪያዎቹ የሚመረቱ ምርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ስለመሆኑ በየጊዜው የሚፈተሽበት አግባብ /ስታንዳርድ/ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

186. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት በተቋቋመባቸው ክልሎች እንዲጠናከሩ ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች እንዲቋቋሙና ማዕከላቱ በገጠር የሚኖሩ ዜጎችንም ጭምር ተደራሽ ማድረግ እንዲቻል ጥናት በማካሄድ፣የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን በመንደፍ ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

187. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኖች ባለው የመንግስት ጤና መዋቅር ማለትም (ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች) ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች (rehabilitation center) በማደራጀትና የሪፈራል (የቅብብሎሽ) ስርዓቶችን በመዘርጋት ተደራሽ እንዲሆኑ ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

188. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት፣ ግብዓቶች እና ድጋፎች እንደ የሰው ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ፣ የእንቅስቃሴ መርጃዎች እና የፊዚዮቴራፒ አገልግሎቶችን ውጤታማና ተደራሽ የሆነ የምርትና ስርጭት ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

189. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሃገር ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ወጭ ቆጣቢና ዘላቂ አገልግሎት የሚሰጡ የሠው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፎችን (ኮምፖነንቶችን)፣ ለእንቅስቃሴ አጋዥ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ከብረታብረት ኢንጂነሪንግ ጋር የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሰነድ በተፈራረመው መሰረት ወደ ሥራ በመግባት ምርትና በጥገና ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ የማስተባበርና የመደገፍ ስራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

190. በአዲስ አበባ የሚገኘው የአዲስ አበባ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከል በሠራተኛና ማህበራዊ ጉደይ ሚኒስቴር በቦርድ ሰብሳቢነት የሚመራ ሲሆን የማምረቻ ማዕከሉ ህጋዊ አቋም እንዲኖረው ሊደረግ፣ ማዕከሉም ቋሚ በሆነ ሥራ አስኪያጅ እንዲመራ በማድረግ የተጠያቂነትን እንዲጠናከር እና በማዕከሉ የሚሰጠው አገልግሎት እንዲሻሻል ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

191. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤና አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችን የሚቀርብ ስለመሆኑ በእስትራቴጂክ ሆነ በአመታዊ ዕቅድ በማካተት ድጋፍና ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

192. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኞች እንደ ጉዳታቸው ዓይነት ተስማሚ በሆነ መልኩ ማለትም መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/ በማዘጋጀት በአካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤናና የግንዛቤ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግና በሽታውን ለመከላከል ስለሚያስችሉ ሁኔታዎች፣ የመተላለፊያ መንገዶችና የመከላከያ ዘዴዎች ተዘጋጅቶ እንዲገነዘቡት የሚያስችል ሁኔታ እየተሠራ ስለመሆኑ በዕቅድ ይዘው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

193. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር  እና ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶን በተመለከተ ተቀናጅቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

194. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ የድርጊት መርሀ ግብሩ የተገለፀው የብሬል ትምህርትን የአማራጭ የፅሑፍና እያደጉ የሚሄዱ አማራጭ የመገናኛ ስልቶች፣ ዘዴዎችና ቅርፆችን የማስተዋወቂያ ገለፃና የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እንዲሁም የአቻ ለአቻ እገዛ እና የሥራ ላይ አስተምህሮትን ተግባራዊ እንዲሆን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ በመሥራት እንዲመቻችላቸው ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

195. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 3/ሐ/ ላይ  አካል ጉዳተኞች እንደጉዳታቸው አይነት መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነ ሥውራን በብሬል፣ መስማትና ማየት በጣምራ ለተሳናቸው በንኪኪ ቋንቋ ዘዴ /በታክታይልስ/፣ ለሕፃናትና ለሴት አካል ጉዳተኞች ትምህርትን ይበልጥ ተስማሚነት ባለው ቋንቋ፣ የግንኙነት ዓይነትና ዘዴ አማካኝነት የቀለም ትምህርትንና ማህበራዊ እድገትን ከፍ በሚያደርግ ሁኔታ ስለመሰጠቱ በበቂ ሁኔታ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

196. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ማየትና መስማት በጣምራ ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች ተደራሽ የሚያደርግ ካሪኩለም እንዲቀርጽ፤ አካል ጉዳተኞች ወደ ትምህርት በመግባት መማር እንዲችሉ በአስገዳጅ ሁኔታ ወደ ትምህርት ገበታ መምጣት የሚችሉበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ፤ በተጨማሪም የመጣውን የለውጥ ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን በመያዝ የድጋፍና የክትትል ሥራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡

197. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አካል ጉዳተኞች የሚማሩበት ትምህርት ቤት በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት ምቹ የመማሪያ ህንፃዎችና ክፍሎች፣ የመዝናኛና መፀዳጃ ስፍራዎች፣ ቤተ መፃሕፍት፣ የውሃ መጠጫ ቦታዎች፣

ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ወዘተ--ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚከታተልበት ስርዓት ሊዘረጋ፣ እንዲሁም ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር አካል ጉዳተኞችን በትምህርት አሰጣጥ ተደራሽነት ላይ በቅንጅት ለመስራት የጋራ መግባቢያ ስምምነት ሠነድ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን በአመታዊ በዕቅድ አካተው ሊተገብሩ ይገባል፡፡

198. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. በተቀመጠው መሰረት የሚገነቡ ህንጻዎች ከዲዛይን ጀምሮ፣ በግንባታ ላይ እና በርክክብ ወቅት ክትትል በማድረግ  አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ባደረገ መልኩ እየተገነቡ ስለመሆኑ እና ተግባራዊ ስለመደረጉ ቅንጅታዊ የክትትል ስራ የሚከናወንበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

199. በህንፃ አዋጁና መመሪያው ላይ  ደረጃ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ሰፊ እና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤና የመራጃ መስጠት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

200. በግንባታ ዙሪያ የተሰማሩ ባለሞያዎች ሁሉም በህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ዓ.ም. መሠረት አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መገንባታቸውን ክትትል በማድረግ በአዋጁ መሰረት ላልገነቡት ባለቤቶችም ሆነ ለማይተገብሩ ባለሞያዎች ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት በመዘርጋት ተጠያቂ ማድረግ እንዲሁም የማስተካከያ/የእርምት/ እርምጃ እንዲወስዱ በማስደረግ ተፈፃሚ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

201. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽን አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/ መሰረት ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ድርጅቶች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት እንዲሆኑ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ አስገብተው ተደራሽ ስለመሆናቸው የሚከታተልበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ፣ እንዲሁም  የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ለማስፈፀም የሚያስችል በቂና ውጤት የሚያመጣ የግንዛቤ ስራዎችን አጠናክሮ በመተግበር ተግባራዊ እንዲሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

202. በፌዴራልም ሆነ በክልሎች በግልና በመንግሥት የተሠሩ ለሕዝብ ክፍት የሆኑ የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ለምሳሌ ባንክ፣ የሕዝብ ማህበራዊ ጉዳዮች መስጫ

ቦታዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የማምለኪያ ቦታዎች---ወዘተ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ስለመሆናቸው ክትትል በማድረግ የእርምት ስራዎች እንዲሰሩ በማስተባበር ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

203. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሸከርካሪዎችና መገልገያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሆነ መልኩ መዘጋጀታቸው እና አገልግሎት መስጠታቸው ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ እንዲሆን እንዲሁም ተደራሽ ባልሆኑት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ በቂ የሆነ ድጋፍና ክትትል ስራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡

204. የትራንስፖርት ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በተፈራረሙት የመግባቢያ ሠነድ መሠረት አካል ጉዳተኞችን በትራንስፖርት መሠረተ ልማት አገልግሎትና አቅርቦት ላይ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ ዕቅድ በማቀድ ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

205. የትራንስፖርት ባለስልጣን የህዝብ ትራንስፖርት ለሚሰጡ ተሸከርካሪዎች የደረጃ መስፈርት ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም የደረጃ መስፈርቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው መዘጋጀታቸው እንደ ደረጃ መስጫ መስፈርት እንዲካተት እንዲሁም አብዛኛው የትራንስፖርት አቅርቦቶች አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደረጉ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

206. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአዲስ አበባ ቀላል የከተማ ባቡር አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች በሁሉም ተርሚናሎች የተገጠሙ አሳንሰር አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የመጠየቅና የመከታተል ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር ውስጥ የቃልና የፅሁፍ መልክት የሚተላለፍ ሲሆን የፅሁፍ መልዕክቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ የሚፃፍ በመሆኑ ለሁሉም ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆን እንዲችል ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

207. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር ደረጃ የሚገኙ የሀገር አቋራጭ መናኸሪያ ቦታዎች ከትኬት መቁረጫ ጀምሮ አገልግሎት የሚሰጡ የሀገር አቋራጭ የትራንስፖርት ስምሪት ቦታዎችና እና አውቶቡሶቹ ለአካል ጉዳተኞች በተሟላ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆኑ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

208. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር አካል ጉዳተኞችን በቴክኖሎጂ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግን አስመልክቶ የመግባቢያ ሠነድ የተፈራረመ ሲሆን በዚሁ መሠረት ዌብ ሳይቶችን የሚያለማ ሲሆን የለማው ዌብ ሳይት ለአካል ጉዳተኞች ስለመድረሱ ወይም አገልግሎት እየሰጠ ስለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

209. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን፣ የእንቅስቃሴ መረጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ መገልገያዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የምርምርና የልማት ስራዎችን እንዲካሄዱ ድጋፍ እና ክትትል ሊያደርግ፣ እንዲሁም የለሙ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ የማስተባበር፣ የማቀናጀት እና የመደገፍ ሥራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡

210. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞችን ከጉዳት አልባ ዜጎች እኩል በሁሉም የሚዲያ አካላት በማካተት የተለያዩ መረጃዎች በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ እንዲሆኑ በቂ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

211. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የግልና የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ፕሮግራሞች ሲሰሩ ለየትኛው አይነት የአካል ጉዳት ምን አይነት አገልግሎት (ፕሮግራም) እንዳላቸው ለምን ያህል የአየር ሰዓት እንደሚሰጡና ያልተዳሰሱ አካባቢዮችን እንዲያካትቱ ለማድረግ በቅንጅት ሊሰሩ እንዲሁም ይህንም የሚገልፅ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በማደራጀት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆን አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

212. በተጨማሪም ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እነማን እንደሆኑ ለየትኛው ችግር የት መሄድ እንዳለባቸው መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ ሊቀረፁ እና በሚዲያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችም አካል ጉዳተኞች ሊረዱት በሚችል ቋንቋ በጉዳታቸው ዓይነት ተዘጋጅተው በመቅረብ ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችል የሚድያ ስርዓት እንዲዘረጋ ሚኒስቴር መ/ቤቱም በሚድያ ተደራሽ መሆን እንዲችሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የድጋፍና ክትትል ስራዎች ሊያከናውን ይገባል፡፡

213. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኞች የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን፣ ፊልሞችንና ቲያትሮችንና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖችን በተመቻቸ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆኑ የክትትል ስራ ሊሰራ እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በመዝናኛ፣ በዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና በስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሥርዓት በመዘርጋት ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

214. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አካል ጉዳተኞች በልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስፈላጊ ሙያዊና የቴክኒክ ድጋፍ ፍላጎት ጥናት በመተግበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም የልማቱ ተጠቃሚ ቤተሰቦች ቁጥር የማሣደግ ሥራ እንዲሰራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍ የማድረግ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

215. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች ላይ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በዕቅድ በመያዝ ተግባራዊ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጡት የግንዘቤ ማስጨበጫዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዲችሉ የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦችን አቅርበናል፡፡

- አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የሚሰጠው ግንዛቤና ስልጠና በማህበራዊ ደህንነት ችግሮችና አገልግሎቶች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ውስጥ በጥቅል ሳይሆን ለአካል ጉዳተኞች የተሰጡ የግንዛቤ ማስጫበጫዎች፣ የተሰጠበት ርዕስ፣ ምን ያህል አካል ጉዳተኞች እንደተሳተፉ ወዘተ በዝርዝር የሚያሳይ መረጃ ሊኖር ይገባል፡፡
- የሚሰጡ ድጋፎች በጥቅል የሚቀመጡ ሳይሆን ለየትኛው ጉዳይ ምን አይነት ድጋፍ እንደተሰጠ እና ድጋፉ ማንን ተጠቃሚ እንዳደረገ ለማረጋገጥ በሚቻል መልኩ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
- በሚሰጡ ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ያስገኙት ውጤት ውጤታማነት ከግቡ አንፃር እየተመዘነ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
- በሴክተሩ የሚከናወኑ የግንዛቤና የስልጠና ሥራዎችን ስታንዳርድ አውጥቶ ያስገኙትን ውጤት እየመዘኑ የማህበራዊ ችግሮችን በመከላከልና ህብረተሰቡን

በማሣተፍ የተፈለገውን ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችሉ ተከታታይ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኮንቬንሽኑንና አዋጁን ለማስፈፀም በበቂ መጠን ውጤት ተኮር (focused) የሆነ ለውጥ የሚያመጣ ግንዛቤ በመፍጠር፣ በማስተባበርና ሥልጠና በመስጠት እንዲሁም ተፈፃሚነቱን በመከታተል በማይተገብሩት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ በሚያስችል መልኩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

216. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት በአካል ጉዳተኞች በሁሉም በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተስብ ክፍሎችን በተለይም አካል ጉዳተኞን ተጠቃሚ ለማደረግ ከፌድራል በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ፈቃድ የወሰዱ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ፈቃድ በወሰዱባቸው አላማዎች እና ክልሎች በመገኘት ለአካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ በመሳሰሉት አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ የተሰማሩ ስለመሆናቸው በበቂ መጠን ቁጥጥር፤ ክትትል እና ድጋፍ ሊደረግባቸው፣ አፈፃፀማቸውም በተከታታይ በመገምገም ግብረ መልስ ሊሰጣቸው፣ እንዲሁም እያስገኙ ስላሉት ኢኮኖሚያዊ ሆነ ማህበራዊ ጥቅሞች መረጃዎች ተደራጅተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡

217. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ዝርዝር ድጋፍ፣ ስለተቀመጡ መብቶችና አስገዳጅ ህጎች፣ ስለአካል ጉዳት አይነቶችና ተጠቂዎች በፆታና በዕድሜ በመለየት ወዘተ መረጃዎችን በማደራጀት በዳታቤዝ ሊይዝ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትሰቲክሰ ኤጄንሲ ጋር በመሆን በህዝብ ቆጠራ ወቅት ስለአካል ጉዳተኞች ሙሉ መረጃ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍ በማድረግ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃዎች እንዲያዝ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

አባሪ 1

| የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫ | የመመዘኛ መስፈርት<br>(Evaluative criteria) |
|---|---|
| የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችለውን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ፤ | 1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ማስፈፀም የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የተዘጋጀ ሲሆን ይህን መርሃ ግብር አፈፃፀም ለመከታተል እንዲቻል የሚመለከታቸው የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችን፣ ኤጀንሲዎችን፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና የግል ሴክተሮችን ያካተተ ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ ሊያቋቁም እና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ላይ አድልዖ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና የቆዩ ልማዶችንን አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማድረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን አተገባበር ለመከታተል እንዲቻል የሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎች፣ ኤጀንሲዎችንን፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግል ሴክተሮችን ያካተተ ክልላዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ በሁሉም ክልሎች ሊያቋቁም ይገባል፡፡ |
| | 4. የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች ሃላፊነት በወሰዱባቸው የብሄራዊ ድርጊት መርሃ ግብሩ አላማዎች፣ ውጤቶችና ተግባራት የየበጀት ዓመቱ ዕቅድ አካል አድርገው እንዲያካትቱ የፖሊሲ መመሪያና የቴክኒክ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው የክልል ቢሮዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ተሀድሶ ሠራተኞችን ለማሰልጠንና ለመደገፍ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ሊቀርፅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ ከሚገኙ ኦርቶፔዲክ እና የፊዚዮራፒ ማዕከላት፣ ከአለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የኦርቶፔዲክ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዜሽን የማስፋፊያና የማጠናከሪያ ስትራቴጂ ሊቀርፅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ የኦርቶፔዲክስና የፊዚዮቴራፒ ሙያተኞችን ቁጥር ለማብዛት በዘርፉ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ሙያተኞች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲያገኙና በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |


| | |
|---|---|
| | 8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሠ.መ.ጉ ቢሮዎች፣ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ውጤታማ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ መሳሪያዎች /ዊልቸር፣ ባለሶስት እግር ሞተር ብስክሌት፣ ባለሶስት እግር ብስክሌት፣ ክራንች፣ ነጭ ብትር/ ምርትና ስርጭት ስትራቴጂ ሊቀርፅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማምረቻ ማዕከላት የተቋቋመባቸውን ክልሎች የሚጠናከሩበት፣ ባልተቋመባቸው ደግሞ ማዕከላቱ እንዲቋቋሙ የማስተባበር ስራዎችን ሊሰራ እና የገንዘብ፣ የቴክኒክና ሙያ ድጋፍም እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል የጤና ቢሮዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የብሄራዊ ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች አካቶ የኤችአይቪ/ ኤድስ፣ የስነተዋልዶ እና የመሳሰሉትን የጤናና የግንዛቤ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ በስትራቴጂና በአመታዊ ዕቅድ በማካተት የሚተገበር መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን አካል ጉዳተኞች ከአጠቃላይ የትምህርት ስርዓትና አስገዳጅ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሆነ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ የሚያገኙበት ሁኔታዎች ያለ መሆኑ እና ከየግለሰቡ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣመና ምክንያታዊ ተቀባይነት ያለው ማስተካከያ የሚቀርብ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ትምህርት ለማግኘት የሚያስችላቸው ድጋፍ የሚቀርብ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 13. ሚኒስቴር መ/ቤቱ መትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን የብሬል ትምህርትን የአማራጭ የፅሑፍና እያደጉ የሚሄዱ አማራጭ የመገናኛ ስልቶች፣ ዘዴዎችና ቅርፆችን የማስተዋወቂያ ገለፃና የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እንዲሁም የአቻ ለአቻ እገዛ እና የሥራ ላይ አስተምህሮትን እንዲመቻቹ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 14. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመተባበር ማየት የተሳናቸው፣ መስማት የተሳናቸው እንዲሁም መስማትና ማየት በጣምራ የተሳናቸው በተመለይም ለሕፃናት ትምህርትን በተመለከተ ለግለሰቡ ይበልጥ ተስማሚነት ባለው ቋንቋ፣ የግንኙነት ዓይነትና ዘዴ አማካኝነት የቀለም ትምህርትንና ማህበራዊ እድገትን ከፍ በሚያደርግ ሁኔታ መሰጠቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 15. ሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ህብረተሰቡን እና የግል ቀጣሪ መ/ቤቶችን እንዲሁም የሲቪል ማህበራትን ስለአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት የወጣው አዋጅ ቁጥር 568/2000 ላይ ላያቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡ |
| | 16. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም አሠሪ የመንግሥት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች ለማንኛውም ረዳት ለሚያስፈልገው አካል ጉዳተኛ ሥራውን ለመሥራት ወይም ሥልጠናውን ለመከታተል እንዲችል ረዳት የሚመከብለትና ደጋፍ የሚደረግለት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 17. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞችን በስራ ቦታ መምራትን በተመለከተ አስተማሪ ፅሁፍ በሀገራዊ ቋንቋዎች ሊያዘጋጅ ና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 18. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አካል |

| | |
|---|---|
| | ጉዳተኞች የቅጥር ምልመላ፣ ጊዜያዊና ቋሚ ቅጥርን፣ በቋሚ ስራላይ መቀጠልን፣ የሙያ እድገትና ጤናማ የስራ ሁኔታዎችን ጨምሮ ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ጨምሮ ያለመድልዎ የሚከናወን መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 19. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሰራተኛና ማህበራሩ ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለአካል ጉዳተኞች እኩል ዋጋ ላለው ስራ እኩል ዕድሎች ሆነ እኩል ክፍያ የማግኝት፣ ለቅሬታዎች የመፍትሄ ምላሽ ማግኝት፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የስራ ሁኔታዎች ከጉዳት አልባዎች ጋር በእኩል ደረጃ ለአካል ጉዳተኞች ትክክለኛና ምቹ የስራ ሁኔታ የማግኝት መብት መኖሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በማንኛውም መ/ቤት የሚሠሩ አካል ጉዳተኞች በሥራ ቦታ የሚደርስባቸውን ጥቃት የመከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ በፈጻሚው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት መሆኑን ሊከታተል እና ተፈጻሚነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 21. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቻቸው የሚዘረጉ የማህበራዊ አቅርቦቶችን ጨምሮ አጠቃላይ የማህበራዊ ደህንነት ጥበቃ ፕሮግራሞች ውጤታማነት ለማረጋገጥ ጥናቶችን ሊያከናውንና ተግባር ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 22. ሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል ቢሮዎች በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ አካል ጉዳተኞችና የቤተሰቦቻቸውን ቁጥር ሊያሳድጉ ይገባል፡ |
| | 23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማንኛውም የህዝብ መገልገያ ህንፃ ውስጥ በተሽከርካሪ ወንበር ለመንቀሳቀስ የሚገደዱትንና መራመድ የሚችሉ ሆኖ ደረጃ መውጣት ለሚሳናቸውን ጨምሮ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የሚመች መዳረሻ መዘጋጀቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የመፀዳጃ ቤት ሊሰራበት በሚገባ በማንኛወም ህንፃ ውስጥ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የሚመቹና ሊደረሱባቸው የሚችሉ በቂ መጠን ያላቸው መፀዳጃ ቤቶች መኖራቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለሕዝብ ክፍት የሆኑ አገልግሎቶችን በማመቻቸትና በማቅረብ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች እነዚህን አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ጭምር ተደራሽነት እንዲኖራቸው አስፈላጊ ጉዳዮችን ሁሉ ግምት ውስጥ ማስገባቻቸውን መከታተል ይገባል፡፡ |
| | 26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለሕዝብ ክፍት በሆኑ ሕንፃዎችና ሌሎች መገልገያ ተቋማት ውስጥ በግልፅ የሚታዩ ምልክቶችን፣ ብሬሎችንና በቀላሉ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ቅፆችን ማስቀመጥ ወይም የሚያቀርቡ ስለመሆናቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 27. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለሕዝብ ክፍት የሆኑ ሕንፃዎችንና ሌሎች መገልገያ ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች የቀጥታ ድጋፍ ዓይነቶችንና መሪዎችን፣ አንባብያንንም ሆነ የምልክት ቋንቋ አጠቃቀም የሰለጠኑ አስተርጓሚዎችን ጨምሮ ሌሎች ተደራሽነትን የሚያመቻቹና |

| | |
|---|---|
| | መረጃዎችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለአካል ጉዳተኞች የፆታና የሥነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅና አህዝቦትን መሰረት ያደረጉ የህዝብ ጤና ፕሮግራሞችን ጨምሮ ከጉዳት አልባዎች በሚሰጠው ደረጃ አንድ ዓይነት፣ ርቀት፣ ጥራትና ደረጃ ያላቸው ነፃና በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራሞችን መቅረቡን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 29. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የጤና አገልግሎቶች ገጠራማ አካባቢዎችን ጨምሮ በተቻለ ቅርበት ህብረተሰቡ በሚገኝበት አካባቢ ማቅረቡን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለአካል ጉዳተኞች ባህላዊ ቁሳቁሶችንና ቅርሶችን፣ የቴሌቪዥን ዝግጅቶችን፣ ፊልሞችንና ቲያትሮችንና ሌሎች ባህላዊ ክንውኖችን በተመቻቸ ሁኔታ ተደራሽ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 31. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባዎች ጋር ባልተናነሰ ደረጃ በመዝናኛ፣ በዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያና በስፖርት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል ተገቢ ዕርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 32. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በሁሉም የሚዲያ አካላት እንዲያካትቱ እና የዕለቱ ዜና በምልክት ቋንቋ እንዲቀርብ ሊያመቻችና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 33. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአካል ጉዳተኞች የተደረገ ያለውን ድጋፍና ክትትል ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| **ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች በቅንጅት የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ለመስራት፣ ስለአካል ጉዳተኞች መረጃዎችን ለመያዝ እና በመረጃ መሳሪያዎችና እኩል እድል ተጠቃሚና ተሳታፊ መሆን የሚያስችል የተቀናጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለመስራት፤ በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ** | 34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞችን በህብረተሰቡ ውስጥ ማካተትና ህብረተሰቡ ስለአካል ጉዳተኞች ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ ከክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ኃላፊነት ከተሰጠው አካላት ጋር በመተባበር ሊመራና የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 35. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች ማህበራት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የአካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ ማሳደጊያ የሬዲዮ ፕሮግራሞችን በመረጃ፣ በሙያና በቁሳቁስ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 36. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በአካል ጉዳተኝነት በሚመለከት እና በሌሎች ጉዳዮች የሚደረገው ወቅታዊ የኢንተርኔት መረጃ ልውውጥን ሊያጠናክር ይገባል፡፡ |
| | 37. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ባለሙያዎች በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ የግንዛቤ ማሳደጊያ ቁሳቁሶች ዝግጅት አደረጃጀትና አተገባበር ላይ የሥራ ላይ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 38. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ግንዛቤ ማሳደጊያ የሚውሉ መረጃ፣ የቴክኒክ ቁሳቁስ ድጋፎችን ለማግኘት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅቱና ከሌሎች አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ድጋፎችን ሊያሰባስብ እና ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል ጉዳተኞች የመረጃን መረብን ጨምሮ በአዳዲስ የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችና ሥርዓቶች የሚጠቀሙበትን ዕድል ሊያመቻችና አፈፃፀሙን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 40. አካል ጉዳተኝነትን የሚመለከቱ በስራ ላይ ያሉ ህጎች፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮችን እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነትን አስመልክቶ መረጃ የሚሰጥ በራሪ ዕሁፍ( ቡክሌት) በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ለህዝብ ተወካይ ምክርቤት፣ ለክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች፣ ለአካል ጉዳተኞች ማህበራትና እና በአካል ጉዳተኞች ዙርያ ለሚሰሩ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም አጠቃላይ ለህብረተሰቡ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 41. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮዎች ጋር በጋር በመሆን የመገናኛ ብዙሀንን ተጠቅሞ የአካል ጉዳተኞችን ዕምቅ ችሎታና ለህብረተሰቡ የሚያበረክቱትን ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያሳ ዓመታዊ የአካል ጉዳተኝነት የመረጃ ዘመቻና ሌሎች መረጃዎችን በማዘጋጀት ለህዝብ ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡ |
| | 42. የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን የእንቅስቃሴ መረጃ መሳሪያዎችንና ድጋፍ ሰጭ መገልገያዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚነት ባላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዙርያ የምርምርና የልማት ስራዎችን ማካሄድና ተደራሽ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 43. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአካል ጉዳተኞች ድጋፍ አሰጣጥ ዙሪያ የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን አፈጻጸማቸውን በመከታተል ገምግሞ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 44. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ አሰጣጥ ተደራሽ ለማደረግ እንዲያስችለው በአገር አቀፍ ደረጃ የአካል ጉዳተኞች ቁጥርን በጉዳት አይነታቸው፣ በፆታና በዕድሜ በመለየት በትክክል መዝግቦ በመረጃነት ለመያዝ ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትሰቲክሰ ኤጄንሲ ጋር በመሆን ቆጠራ ሊያካሄድ ይገባል፡፡ |

# የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ድርጅታዊ መዋቅር



**አባሪ 3**

## የክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች

## ከ2006-2008 በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን

**የፊዚዮ ቴራፒ አገልግሎት እቅድና አፈፃፀም**

- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክ/መ/ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ከ2006-2008 በጀት ዓመት ለ5600 አካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ ለ3917 (70 በመቶ) አካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት ሲያገኙ 1683 (30 በመቶ) የአካል ጉዳተኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
- በትግራይ ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከ2006-2008 በጀት ዓመት ለ2017 አካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ ለ1012 (50 በመቶ) አካል ጉዳተኞች ብቻ አገልግሎቱን ሲያገኙ 1005 (50 በመቶ) አካል ጉዳተኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
- በኦሮሚያ ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከ2006-2008 በጀት ዓመት 10358 አካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ ለ2620 (25 በመቶ) አካል ጉዳተኞች ብቻ አገልግሎቱን ሲያገኙ 7738 (75 በመቶ) አካል ጉዳተኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
- በአማራ ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከ2006-2008 በጀት ዓመት ለ31131 አካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ ለ11964 (38 በመቶ) አካል ጉዳተኞች ብቻ አገልግሎቱን ሲያገኙ 19167 (62 በመቶ) አካል ጉዳተኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣
- በጋምቤላ ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ከ2006-2008 በጀት ዓመት ለአካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ ድጋፍ ባለማድረጉ በክልሉ የሚገኙ የአካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት እያገኙ አለመሆናቸው፣

**በክልል የብሬል ድጋፍን በተመለከተ**

- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ 2007 ዓ.ም ለ80 ዓይነሥውራን የብሬል ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ ለ35 ብቻ ድጋፍ በማድረጉ 45 ዓይነሥውራን ድጋፉን ሲያገኙ 45ቱ የድጋፉ ተጠቃሚዎች አለመሆናቸው ሲታወቅ በ2006 ዓ.ም. እና በ2008 ዓ.ም በማቀድ ድጋፍ አለማድረጋቸው፣
- በኦሮሚያ ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በ2006 ዓ.ም. አቅዶ ያላከናወነ ሲሆን፣ በ2007 ዓ.ም ለ322 ድጋፍ ለማድረግ ቢያቅድም ሙሉ በሙሉ አለመከናወኑ፣ እንዲሁም በ2008 ዓ.ም ለ1,530 ድጋፍ ለማድረግ አቅዶ ለ73 ብቻ ድጋፍ በማድረጉ 1,457 ዓይነ ሥውራን የብሬል ድጋፍ አለማግኘታቸው፣
- በትግራይ እና በጋምቤላ ክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ከ2006-2008 በጀት ዓመት ለዓይነ ሥውራን የብሬል ድጋፍ ለማድረግ አቅደው አለማከናወናቸው፣
- በተመሳሳይም ከላይ የተገለፁት የክልል ቢሮዎች ከ2006-2008 በጀት ዓመት የምልክት ቋንቋ መጽሐፍ ድጋፍ ለማድረግ የማያቅዱና ድጋፍ የማያደርጉ መሆኑን ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርታቸው ቢያሳውቁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ

ለሚመለከተው አካል ቅርቦ የማስተካከያ እርምጃ አለማስወሰዱን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡